ትክክል አልነበረም። በዘመናዊ የጦር ሥልትም፣ በጥንታዊ ባህልም ቦታ የለውም። ከዚሁ ጋር ሊነሳ የሚገባው፣ የጦር በሮች አስቀድሞውኑ አልተጠበቁም። በሰሜን አምባላጌ፣ በምሥራቅ ካራማራ፤ በነፃ ለጠላት ተለቀቁ።

የጦርነቱ ምክር የሚመከረውና ዕቅድ የሚነደፈው በውጭ አገር ሰዎች መሆኑ ታላቅ ድክመት ነበር። ታላቅ ጉዳትም አድርሶአል። ሌላው ለጦሩ ስንቅ አልቀረበለትም። መሣሪያውም በዋሻ እንደታጨቀ መቅረቱን ብዙዎች በምሬት ያስታውሳሉ። በጥቃቅን ሽንገላ ከጠላት ጐን በመቆም፣ ከመሣፍንቱና ከመኳንንቱ ብዙዎቹ የክህደት ሥራ አካሄዱ። በምሥራቅ ጦር ግንባር ነፋሻውን ደጋማ አገር መከላከል ሲገባ ጦሩ ዶሎና ቆራሄ ገብቶ እንዲያልቅ መደረጉ ሳይጠቀስ ሊታለፍ አይገባውም።

ደግ ሥራ የተሠራው በደፕሎማቲክ ረገድ ነው ቢባልም፣ እሱም እንከን አላጣውም። ችግሩን ለዓለም ማህበር ማቅረብ፣ መከራከር፣ ዕርዳታ መጠየቅ ላይ ብቻ መመካት ተገቢ አልነበረም። ሌላው ችግር ንጉሠ ነገሥቱ ከጣልያን ጋር ያካሂዱት የነበረው የምሥጢር ንግግር ነበር። ምንም ንጉሠ ነገሥቱ የተደረገባቸውን ተፅዕኖ በመቋቋም ኢትዮጵያን ከውርደት ቢያድኑ፤ ንግግሩ መደረጉ ራሱ በታሪክ ፊት አሳፋሪ ጉዳይ እንደሆነ ይኖራል። ሌላው ጉድለት ደግሞ ጣልያን ሲባረር አርበኞች አዲስ አበባ እንዳይገቡ መታገዳቸው ነው። በጣልያኖች ላይ ጉዳት ያደርሱ ነበር ከሚለው ክንቱ ወሬ ይልቅ፤ የከተማይቱን ጸጥታ በመርዳት ጠብቀው ሊያቆዩ ይችሉ ነበር ማለቱ የበለጠ እውነትነት አለው። የሚያሳዝና ደግሞ ኢትዮጵያ ፈጥና በጦርነት የወደቀችው በእነዚህ ምክንያቶች መሆኑ ነው።


**<u>ማጣቀሻ ፅሑፎች</u>**

1. ሳጺሶ ጌ. ድሌቦ፣ *የኢትዮጵያ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ*፣ ገጽ 21።
2. እስከ ግንቦት 7 ቀን 1928 ዓ.ም ድረስ ብቻ። ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 150።
3. እስከ ነሐሴ ወር 1928 ዓ.ም ብቻ። ጳውሎስ ኞኞ፣ ገጽ 154።
4. ግንቦት 21 ቀን 1928 ዓ.ም ብቻ፣ ጳውሎስ ኞኞ፣ ገጽ 151። ከመስከረም 30 ቀን 1929 እስከ ሚያዝያ 6 ቀን 1932 ዓ.ም ድረስ።
5. Sabacchii, *Ethiopia under Mussolini,* p.180.
6. Greenfield, *Ethiopia*, p.238.




# ምዕራፍ አርባ
# የአርበኞች የርስበርስ ግንኙነት

የአርበኞች ዓላማ አንድ ነበር፤ ኢትዮጵያን ነፃ ማውጣት። የዚህ ዓላማ ሌላው አማራጭ ሞት፣ ቅኝ መገዛት ነው። በዚህ ጉዳይ የወላወለ ከአርበኛ አልተቆጠረም። በዚህ ዓላማ ጸንተው የዘለቁ እጅግ ብዙ ናቸው። የኢትዮጵያ መንግስት በትግል የሞቱት 78,500 እንደነበሩ ገምቶአል። ሳያንስ አልቀረም። ነገር ግን ሌላ ማስረጃ የለምና፣ በዚሁ መጽናቱ ይሻላል።

በዚህ ዓላማ ጸንተው የአምስቱን ዓመት ተጋድሎ የፈጸሙት 20,000 ይሆን ይሆናል። ሌላው የንጉሠ ነገሥቱን መምጣት ሲረዳ፣ ቃላቸውን ሲሰማ ከጣልያን እየከዳ የገባ ነው። የራሱን ጉዳይ ያካሄደ እንጂ ለሀገር እንደሞተ ለመቁጠር ያዳግታል። ቢሆንም እስከ መጨረሻይቱ የጣልያን ሕቅታ፤ ማለትም የተመደበበት ጦር እስኪፈርስ ሽንጡን ገትሮ ወገኑን ከተዋጋው በብዙ እጅ ይሻላል።

የሞተው 78,500 ከነበረና በሕይወት ቀን የወጣው 20,000 ከሆነ ወደ 100,000 ያህል አርበኛ ተንቀሳቅሶ ነበር ማለት ነው። ይህንን ያህል ሰው በአቀፈ ሠራዊት ውስጥ አንዳንድ የሥነ ሥርዓት ጉድለት ማጋጠሙ አይቀርም። አፍ ከእጅ ይጣላል እንዲሉ፣ በአርበኞች መካከልም እንደዚሁ ሆኗል። መስማማትና መጣላት፣ መረዳዳትና መጋጨት፤ በልዩ ልዩ መልክ፣ በልዩ ልዩ ጊዜና ቦታ ተከስተዋል።

መረዳዳቱ መልካም ነበር። አንዱ በተጠቃ ጊዜ ሌላው ገስግሶ ይደርስለታል። በዚህ ዓይነት የጦር ጓደኞቻቸውን ያዳኑ እጅግ ብዙ ናቸው። ነገር ግን አደጋው ከአለፈ እምብዛም አይታሰብም፤ ይዘነጋል። ቢሆንም አርበኞች እርስበርሳቸው ይረዳዱ እንደነበረ፣ ከሚጋጩበት ጊዜ ይልቅ፣ የሚረዳዱበትና የሚደጋገፉበት ጊዜ ይበዛ እንደነበረ እሙን ነው።

ምንም ሕይወታቸውን ለሀገራቸው ክብርና ለወገናቸው ነፃነት መሥዋዕት ለማድረግ ቢቆሙ፤ ምንም የግል ጉዳያቸውን፣ ሕልውናቸውን ጭምር ወደ ጐን ቢተው፤ አርበኞች አልፎ አልፎ እርስ በርሳቸው መጋጨታቸው አልቀረም። ሥጋ ለባስያን ስለሆኑ የሚያጋጩአቸውም ነገሮች ነበሩ። በሴት ከንፈር፣ በልጅ ነገር፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በመሬት ድንበር ተጋጭተዋል። የጉርስና የልብስ ጉዳይ ያጋጫል። የክብርና የሥልጣን ውድድር፣ የመሣሪያ ቅብብሎሽ ያጣላል። አንድ አርበኛ የቀድሞ አለቃውን ትቶ ከሌላው ጋር ሲሰለፍ ሁለቱን አለቆች ያቃቅራል። የክልል ጉዳይም እንዲሁ፤ ለአንዱ መጥን ከሚወጣበት ቤት፣ ሌላው የጠየቀ እንደሆነ ያቃቅራል። የክፍለ አገር ክልልም እንደዚሁ ነው። አንዱ በደሙ ያስከበረውን አካባቢ፣ አገር ሌላው ልንካ ቢል አይሆንም። ነገረ ሠሪዎችና አሰሪዎችም

አልጠፋም። ስለዚህ ብዙ ዓይነት ግጭቶች ታይተዋል። ለትምህርት ያህል አንዳንዱን እንጠቅሳለን። ሁሉን መዘርዘር አይቻልምና።

በልጅ ወሰን ኃይሉና በደጃዝማች ነጋሽ ወርቅነህ መካከል ለጥቂት ጊዜ መተባበር ታየ። ሁለቱ የጦር አለቆች መሽሐ በተባለው ወንዝ ላይ ተገናኝተው ለመረዳዳት በተስማሙ ጊዜ በሠራዊቱ ዘንድ ታላቅ ደስታ ሆነ። ሕዝቡም ለሀገሩ ለመሞት ቁርጠኝነቱን በመሐል አረጋገጠ። ነገር ግን ምንም ያህል ሳይቆይ የሁለቱ የጦር አለቆች ግንኙነት እየሻከረ ሄደ። ልጅ ወሰን ለደጃዝማች ነጋሽ ጥር 8 ቀን 1932 ዓ.ም አንድ ደብዳቤ ጻፉ። ደብዳቤውም "...በየዳ መጥቼ ልቀመጥ ነኝ። ሣቢ ላይ ቤት አሠርተው፣ የፍጋይን አበል አስገብተው እንዲቆዩኝ። የቆላውም የብረት አለቅነት በፊታውራሪ ካሣ ነአኩቶ ሆኖ እየታዘዙ እንዲቆየኝ ይሁን" የሚል ነበር።

ደጃዝማች ነጋሽ በዚህ ቅር ተሰኙ። ጥር 12 ቀን 1932 ዓ.ም በጻፉት የመልስ ደብዳቤ "...ቤቴን እንዲያሠሩልኝ ሲሉ የጻፉትን አልተቀበልኩትም። ምክንያቱም ...እየተረዳዳን ጠላትን ልንወጋ የተማማልነው መሐላ ቀርቶ አሁን አዲስ ነገር በመፈጠሩ ነው..." አሉ። ስሙ ታውቆ፣ ክብሩ ተጠብቆ የኖረውን ስሜንን ለዋግ ማስገዛት ስለሚሆን እንደማይደረግ ገለጹ። ጠቡ የሰዎች ብቻ ሳይሆን አገርንም ቀላቀለ። ልጅ ወሰን ደጃዝማች ነጋሽን ለመውጋት ተንቀሳቀሱ። ጥር 12 ቀን 1932 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ፊታውራሪ አስፋው ኃይለማርያም የተባለውን የባንዶች አለቃ ትብብር ጠየቁ። ደጃዝማች ነጋሽን እንደርሳቸው ያለውን ባለበት አገር ላይ እንደሚቆሙ ቃል ገቡላቸው። ፊታውራሪ አስፋው የተጻፈለትን ደብዳቤ ለጌታው ለጣልያን ሰጠ። ጣልያን ምሥጢሩን ለደጃዝማች ነጋሽ ገለጸ። ጥር 17 ቀን 1932 ዓ.ም በ6 ሰዓት በሁለቱ አርበኞች መካከል ጦርነት ተከፈተ። እስከ ምሽቱ 3 ሰዓት ቆየ። ከሁለቱም ወገን ብዙ ሰው አለቀ። ልጅ ወሰን ተሸነፉ።[1] የደጃዝማች ነጋሽ አመለካከት በሀገር ነፃነት፤ የልጅ ወሰን አስተያየት በግል ሥልጣንና ክብር ላይ ያተኮረ ነበር። ያሳዝናል።

በዚያው በጐንደር በአቶ ሕይወት ኀደሩና በደጃዝማች ብሬ የተነሣው ቁርሾ፤ አቶ ሕይወትን እስከ መታሠር፣ መሣሪያ እስከ መገፈፍና እስከ መንገላታትም አደረሳቸው። ችግሩ የተፈጠረው በነባሩና በዘመናዊው የጦር ሥልት ላይ በተመሠረተ የአመለካከት ልዩነት ነበር። ደንበኛው የኢትዮጵያ የጦር ሥልት ምሥጢርን ሳይንቁ መደበቅ ሲሆን፤ ዘመናዊው ዘዴ ለዓለም ኅብረተሰብ መግለጽ ነው። አቶ ሕይወት ፎቶግራፍ ማንሳት፣ ማስታወሻ መጻፍ ያዙ። ይህ አሠራር ከእንግሊዝ ቁንሲል ሠራተኛነታቸው ጋር ተያይዞ ስላይ አሰኛቸው። በዚያን ሰዓት ማለትም ከመስከረም እስከ ሰኔ 3 ቀን 1932 ዓ.ም ድረስ እንግሊዝ ከጣልያን ጋር ያላትን የጥቅም ትስስር እያጠናከረች ስለነበረ ይህ ጉዳይ ቀላል አልነበረም። አርበኛውን አስገነገነ።[2] ይህኛው



አለመግባባት ትክክለኛነት ያለው ነበር። በግኝቱ ደም አልፈሰሰም፤ ሕይወት አልጠፋም።

በዚያው በጐንደር በደጃዝማች ዮሐንስ ኢያሱና በአሞራው /ራስ/ ውብነህ መካከል በነሐሴ ወር 1931 ዓ.ም አለመግባባት ተፈጥሮ ነበር። ነገር ግን ክፉ ውጤት እስከሚያስከትልበት ደረጃ አልደረሰም።[3] ከክፉ ያልተደረሰው ደግሞ በደጃዝማች ዮሐንስ ትዕግስት ነው ሊባል ይቻላል። ይህኛው ግጭት ደግሞ በፖለቲካ የተነሳ እንደሆነ በታሪክ ተመዝግቦአል። በንጉሥ ጥያቄ ላይ ይሆን?

በጐጃም አርበኞች መካከል የነበረው አለመግባባት ቀላል አልነበረም። አዛዥ /ደጃዝማች/ ከበደ ተሰማን "...አርበኞችም አንድ ነገር ይጐድላቸዋል። ይኸውም ስምምነትና ፍቅር ነው..." ብለው ለንጉሠ ነገሥቱ ሪፖርት እስከ መስጠት አስመርሮአቸው ነበር። በልጅ /ራስ/ ኃይሉ በለውና /በደጃዝማች/ በላይ ዘለቀ መካከል የነበረው ጠብ ከባድ ነበር። ጠቡ የተነሣው በአገር አገዛዝ ሽሚያ ነበር። እስከ መሣሪያ ግጭት አድርሶአል። ጠቡን ያበረደው የንጉሠ ነገሥቱ መልእክተኛ በነገሩ ስለገቡበት ነው፤ ያውም አንድ ጊዜ ውጊያ ተካሂዶ ብዙ ሰው ከአለቀና ለሌላ ለሁለተኛ ዙር ከተሰላለፉ በኋላ።

በቢትወደድ ነጋሽ በዛብህና በደጃዝማች መንገሻ ጀምበሬ መካከልም እንደዛው ያለ ጠብ ተቀስቅሶ ነበር። እነሱም አንድ ጊዜ ከተዋጉ በኋላ በኅዳር ወር 1933 ዓ.ም የታረቁት፤ በአዛዥ /ደጃዝማች/ ከበደ ተሰማ በኩል የንጉሠ ነገሥቱ ቃል ስለደረሳቸው ነበር። የታረቁትም "...ስለኢትዮጵያና ስለንጉሠ ነገሥቱ ስንል ጠባችን ቀርቷል" በማለት ሆነ። ጠቡ የተቀሰቀሰው በአገር ግዛትና ከአንዱ እየከዱ ለሌላው በሚያብሩ ጭፍሮች ምክንያት ነበር። በደጃዝማች መንገሻ አቦዬና በልጅ አበራ ይማም መካከልም ተመሳሳይ ሁኔታ ታይቶአል።[4] በደጃዝማች ነጋሽና በወይዘሮ ሰብለ ወንጌል መካከልም ቅያሜ ለመፍጠር ነገረ ሠሪዎች ወዲያ ወዲህ ማለታቸው አልቀረም ነበር።[5]

በሸዋ አርበኞች መካከል የነበረው የሃሳብ ልዩነት ደግሞ ይበልጥ የከረረ ነበር። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፣ ንጉሠ ነገሥት መልእክ ፀሐይ በሚያዝያ ወር 1930 ዓ.ም ታላቅ ሹመት ሰጡ። ይህ ሹመት በአርበኞቹ መካከል የቀሰቀሰው ጠብ ሳይበርድ እስከ ጦርነቱ ፍፃሜ ድረስ ቆየ። ብዙ ጉዳትም አደረሰ። ቀኛዝማች ኃይለማርያም ማሞ የተሰጣቸውን የደጃዝማችነት ማዕረግ ሳይቀበሉ ሞቱ። ሹመቱን ከተቀበሉት መካከልም፣ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን መንቀሳቀስ እንደሰሙ ሹመታቸውን ትተው በቀድሞ ማዕረጋቸው መጠራትን የመረጡ አሉ። ለምሣሌ ደጃዝማች ዘውዱ አበኮራን ፊታውራሪ እያሉ ጽፈዋል። በአንጻሩ ደግሞ ፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ ደጃዝማች ባለመሰኘታቸው ብዙዎችን ያስገነገነ ቅሬታ አሳይተዋል። ቢሆንም ይህ ሁኔታ የርስበርስ መቃቃር እንጂ፣ የርስበርስ ሟናቆር አላስከተለም።

በሌላ በኩል በፊታውራሪ ዝቅ አርጋቸውና በፊታውራሪ ሞገሴ መኩሪያ መካከል ድንገተኛ ጠብ ተቀስቅሶ ፊታውራሪ ዝቅ አርጌ ተገደሉ። በጥቂት ቀናት ውስጥ ደግሞ ፊታውራሪ ሞገሴ ተገደሉ። የጠቡ ምክንያት በቤትም፣ በመሣሪያ ንጥቂያም ነው ይባላል። ከመሞታቸው በስተቀር ግን በግልጽ የታወቀ ነገር የለም። ሁለቱ ወጣት የጦር መሪዎች በከንቱ መውደቃቸው እጅግ ያሳዝናል።

በዚህ ከላይ በተገለፀው ሹመት ጠንቅነት ፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ የተወለዱበትና አርበኝነት ያቋቋሙበት አገር ሜጢ፣ ለፊታውራሪ ደባልቄ ተክሌ ተሰጠ። የፊታውራሪ ደባልቄ አስተዳደር አላስፈላጊ ተፅዕኖ አስከተለ። የቆሰለ እንጂ የሞተ ባይኖርም፣ ውሎ አድሮ ግን ሁለቱን ፊታውራሪዎች አዋጋ። በኋላ ያስከተለው ክስና ክርክር ደግሞ ሌላ ጠብ ለማስነሳት ምንም አልቀረውም። በራስ አበበ የአስተዳደር ችሎታ ቀዘቀዘ።

ይህ መዘዘኛ ሹመት ታላቁን ማዕረግ ላገኙት ለራስ አበበ አረጋይም አልተመቻቸውም። እሳቸው የተሰጣቸውን የራስነት ማዕረግ ሲቀበሉ፣ ቀኛዝማች ኃይለ ማርያም ማሞ አልቀበልም ማለታቸው፤ በመልአክ ፀሐይና በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ደጋፊዎች መካከል ውስጥ ውስጡን ይካሄድ የነበረውን ትግል ወደ ገሐድነት አቃረበው። አንዱ ያገኙሁትን ሹመት አለቅም ሲል፣ በአንፃሩ ደግሞ ሌላው ከነጭራሹም አልቀበልም ማለቱ። ሌላው ደግሞ መጀመሪያ ተቀብሎ ቆይቶ መልቀቁ፤ ሌላው ደግሞ ሹመት ሳያገኝ በመቅረቱ ቅሬታ ማሳየቱ የጉዳዩን ፍንጭ አመላከተ። ይህ ሁሉ በሠራዊቱ አመለካከት ላይ የፈጠረውን ምስቅልቅል፣ በአጭር ጽሑፍ ለመግለጽ ያዳግታል። በዚህ ላይ የወጣቱ ንጉሥ የመልአከ ፀሐይ ኢያሱ ሞት ሲጨመር ከናካቴው ዝብርቅርቁ ወጣ።

የሞግዚትነት ሥራቸው በወጣቱ ንጉሥ ሞት ሲያከትም፤ በደጃዝማች ኃይሉ ወልደመድኅን የሚመራው አርበኛ ከሠራዊቱ ጋር፣ በተለይም ከጦር አለቆቹ ጋር መጣጣም አቃተው። ይህ ሠራዊት ከቡልጋ ወጥቶ ወደ ጉራጌ አገር ለመዞር ተንቀሳቀሰ። ሃሳቡ ቢቻል በጉራጌ አገር ካሉ አርበኞች ጋር ተቀላቅሎ ሥራውን ለመቀጠል፣ ይህ ባይቻል ወደ ኬንያ ለመጓዝ ሳይሆን አልቀረም። ነገር ግን ከአንዱም አልደረሰም። የጆሬ ሲደርስ መሪ የነበረው ሰው ከአንድ ከተቃጠለ ግንብ ቤት ከትቶት ዙሪያገቡን ቃኝቼ ልምጣ በሚል ምክንያት ወጣ። ቀን መሽቶ ነበርና አርበኛው መንቀሳቀስ አልቻለም። ቀን ሙሉ ሲጓዝ ስለዋለ ድካም ተጫጫነው። ሌሊቱን በጠላት ተከበበ። የተቻለውን ያህል ተከላከለ፤ ነገር ግን ሰብሮ መውጣት አልቻለም። ሰኔ 15 ቀን 1931 ዓ.ም አለቀ። አንድ ንጋቱ ወልደዮሐንስ ከሚባል ልጅ በስተቀር ምንም ሰው አልተረፈም። ከግንቡ ውስጥ የተረፈረፈውን የሰባ ስምንት ሰው ሬሣ የአካባቢው ገበሬ በማግሥቱ አንስቶ ቀበረ። [6]



ንጉሥ መልአከ ፀሐይ ኢያሱ እንደሞቱ ሠራዊቱ አገነገነ። ደጃዝማች መንገሻና ልጅ /ፊታውራሪ/ ገብረክርስቶስ መኰንን ለጥያቄ ከራስ አበበ ዘንድ እንዲቀርቡ ተጠየቁ። ፈቃደኞች ባለመሆናቸው ተኩስ ተከፍቶ ሦስት አርበኞች ሞቱ። እነሱም ደብረ ብርሃን ገብተው እጃቸውን ሰጡ። ጣልያንም በየርስታቸው እንዲቀመጡ ፈቀደላቸው። በተለይ ከእነዚህ ሰዎች ባገኘው እርግጠኛ ምሥጢር ጀነራል ናዚ መሶቢት ሮርች ለተቀጠረው የእርቅ ንግግር ሳይቀርብ ቀረ፤ እሱን ጠልፎ ለመውሰድ ታስቦ የነበረው ሃሳብ በዛው ከሸፈ።

በነሐሴ ወር 1931 ዓ.ም መካኒሣ፣ ዳዊት አገር በተባለው ቦታ፤ በቀኛዝማች ኃይለማርያም ማሞና በባላምባራስ /በፊታውራሪ/ ተሻገር ሰዎች መካከል ተኩስ ተከፍቶ ሰባት ሰዎች ሞቱ። የቀኛዝማች ኃይለማርያም ሰዎች ሀገሩን ለቀው ወደ ግንደበረት አካባቢ ዞሩ።

በልጅ /ደጃዝማች/ ብዙነሽና በልጅ ገርቢ መካከል የተነሣው ጠብ ለብዙ ጊዜ ሲያስቸግር ቆይቶ ነበር። ችግሩ ሊቃለል የቻለው በእነ ባላምባራስ /በራስ/ አበበና በፊታውራሪ ተሻገር ብርታት ነው።[7]

ከሁሉም የሚያሳዝነው በአንድ በሬ የሽንጥ ሥጋ ዘጠኝ አርበኞች ታህሣሥ 10 ቀን 1933 ዓ.ም በረከት፣ ወዳዲማ ማለቃቸው ነው። ጥንቱኑ ቁርሾ ሳይኖርበት አልቀረም። የዕለቱ ጠብ የተነሣው እንደዚህ ነው። አርበኞች የአንድ ሌላ አርበኛ በሬ ለማረድ ይይዛሉ። ባለበሬው ይቃወማል። የሠራዊቱን መራብ ከአስረዱት በኋላ ለእሱም አንድ ሽንጥ ሥጋ ሊሰጡት ተስማምተው በሬው ታረደ። ሽንጡን ሥጋ ለባለቤቱ ሳይሰጡ ሙልጭ አድርገው ስለበሉት ጠብ ተነሣ። ትኩስ ሥጋ በልተው እንደተንፈራዘዙ አቶ ዝናዬ የተባለው የበሬው ባለቤት በመውዜር ጠመንጃ ዘጠኙን ረፈረፋቸው። ፈርቶ ባይተዋቸው ሌሎቹንም ሊጨርሳቸው ይችል ነበር። አንዳቸውም አልተንፈራገጡም። ከሞቱት ውስጥ ፊታውራሪ አጐናፍር ባዩ፣ ፊታውራሪ ተክለ ሃይማኖትና ባሻ ባዩ ነበሩበት። አቶ ዝናየም ወደ ጣልያን ሳይገባ፣ የሽፍታ ሽፍታ ሆኖ፣ ከሚስትና ከልጅ ጋር አርበኝነቱን ቀጠለ። ሰው አልፈረደበትም። የጨረሳቸው ደም የሚያፈላ ቃል ስለተናገሩት ነበር።[8]

ሌላው አሳዛኝ ነገር በአንድ እንጀራ ምክንያት በተነሣ ጠብ አንድ ልጃገረድ ገድሎ አቶ ላውጋው የተባለውን ገበሬ ስለአቆሰለ በገበሬዎቹ የተገደለው አርበኛ ነው። ይህ የተደረገው ደግሞ ሙገሬ ዛላ፣ ሜጢ ከአለቃ ገብረ መሢህ ቤት ነው። ጠቡን የቀሰቀሱት እመት እግዚኦ ሲረያ የተባሉት የሞተችው ልጅ አያት ናቸው።

አንዳንዱ በዚህ ዓይነት ተበጣብጦ የሸዋ አርበኛ አንዱ ከሌላው ሳይገናኝ እየቀረ፣ በየፈናው ትግሉን የቀጠለበት አጋጣሚ አለ። እንደዛ በሆነ ጊዜ ካህናትና የሀገር ሽማግሌዎች በብርታት የሽምግልና ሥራ ባያካሂዱ ኖሮ፤ በየጊዜው በየቦታው በተነሣው ጠብ ብዙ ሰው ያልቅ ነበር። ምናልባትም አርበኛው ከእነጭራሹ ተፈትቶ ለድል ሳይበቃ ይቀር ነበር። በሽምግልና

የቀዘቀዘውን ጠብና ሊያደርስ ይችል የነበረውን ጉዳት አሁን ለመዘርዘር አይቻልም፡፡ በሌላ በኩል አርበኛውን እርስበርሱ ማበጣበጥን ሥራ አድርገው የያዙ ነበሩ፡፡ ደስ የሚለው ግን፣ አርበኛው ይህንን የመሳሰለውን ችግር ሁሉ ችሎ ለሀገሩ ነፃነትና ለወገኑ ክብር እስከ መጨረሻው መጋደሉ ነው፡፡

## ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. *ገሪማ ታፈረ፣ ጐንደሬ በጋሻው፣* ገጽ 158-159፡፡
2. ሕይወት ኀደሩ፣ *ያቺ ቀን ተረሣች፣* ገጽ 233፡፡
3. ገሪማ ታፈረ፣ ገጽ 144፡፡
4. ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ፣* ገጽ 262፣ 272፣ 283 እና 296፡፡
5. ሙሉ ሰው ምትኩ፣ *የአርበኝነት ትግል ከፋሽስት ጋር፣* ገጽ 43፡፡
6. ከአቶ ንጋቱ ወልደ ዮሐንስ ዘውዴነህ የተነገረኝ፡፡
7. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው፣* ገጽ 425-426፡፡
8. ከአቶ /ሻለቃ/ አሰፋ ወልደፃድቅ የተነገረኝ፡፡



# ምዕራፍ አርባ አንድ
# በአርበኞች ዘንድ የነበረ የፍርድ ሥራ

ብዙ ሰው አርበኝነት የውንብድና የቅሚያ ሥራ ይመስለዋል፡፡ እንደዚህ አስመስለው ለማሳየት የሞከሩም በርካታ ናቸው፡፡ በወቅቱ ሠፊ ልሣን አግኝተው ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ አመለካከት ትክክል አይደለም፡፡ በአርበኝነት ጊዜ ሕግና ፍትሕ ነበር፡፡ ለአብነት ያህል ከተፈጸሙት የፍርድ ሥራዎች ጥቂቶቹን እንገልጻለን፡፡

ሚያዝያ 12 ቀን 1929 ዓ.ም ሰላሌ፣ ጉርጉርቱ በተደረገ ጦርነት 40 ባንዶች ተማረኩ፡፡ ለፍርድ በአርበኛው አደባባይ ቆሙ፡፡ ሀገራቸውን ኢትዮጵያን ክደተው ከወራሪው ከጣልያን ጦር ጐን የተዋጉ ከሀዲያን ስለሆኑ ሊቀጡ ይገባል የሚል ክስ ቀረበባቸው፡፡ እያንዳንዱ የፈፀመው ታወቀ፡፡ ሁለት ቀን የፈጀ ፍርድ ተሰጠ፡፡ ሃያ ሦስቱ በብርታት ለጠላት የተዋጉና ቀደም ብሎም አርበኞችን የገደሉ ስለሆኑ በሞት ተቀጡ፡፡ አሥራ ሰባቱ ከጠላት ጐን ከመቆም በስተቀር ሌላ በደል ስለአልፈፀሙ መሣሪያ ለጥቂት ቀን በመሸከም ተቀጥተው በአመክሮ ተለቀቁ፡፡[1]

ባሻ ጠውቱ የተባሉ አርበኛ አንድ ባንዳ ማረኩ፡፡ ተማራኪው በኅዳር ወር 1930 ዓ.ም ቡልጋ መገዘዝ፣ ጫሬ ከአርበኞች ችሎት ቀረበ፡፡ ከጠላት ወገን ሆኖ እናት ሀገሩን መውጋቱ በማስረጃ ተረጋገጠበት፡፡ ማስረጃውም ከኪሱ የተገኘ እሱ ራሱ የጻፈው ማስታወሻ ሆነ፡፡ አገልግሎቱን ለጌታው ለጣልያን በማቅረብ ሊሾም ሊሸለምበት ያዘጋጀው ነበር፡፡ በጽሑፉ ላይ አቃጠልኩአቸው የሚላቸው የ158 አብያተ ክርስቲያናት ስም ዝርዝር ተገኘ፡፡ ቁጥሩን ሳያጋንነው አልቀረም፡፡ ሆኖም ማቃጠሉ ማቃጠል ነበር፡፡ ተፈረደበት በሞት ተቀጣ፡፡[2]

ደጃዝማች መሸሻ ተወንድ በላይ ተይዘው ጥር 23 ቀን 1929 ዓ.ም ለፍርድ ከአርበኞች አደባባይ ቀረቡ፡፡ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከፍተኛ ባለሥልጣን ሆነው ሣለ ከጠላት መቆማቸው ክህደት መሆኑ ተነገረባቸው፡፡ በወቅቱ ብዙ ሰው ለጠላት የገባ በመሆኑ መግባታቸው የማያስቀጣቸው ሆነ፡፡ ቢጠየቁ ምላሽ ሳይሰጡ ቀረ፡፡ አንዳንድ መልስ ቢሰጡም ሠራዊቱን የሚያበሳጭና ፍርድ የሚያጣምም ሆነ፡፡ ሽምግልናቸውን ከግምት አግብቶ አርበኛው ንግግራቸውን ሳይዘክርባቸው ቀረ፡፡ ሆኖም ተቃዋሚ ስለበዛባቸው ሥራቸው ተመረመረ፡፡ ለሀገሩ የሚጋደለውን አርበኛ ጣልያንን ደስ ለማሰኘት ጅሩ ገበያ ላይ አሰቅለሃል የሚል ማስረጃ ቀረበባቸው፡፡ ስንት ሰው እንደ አሰቀሉ ቁጥሩ በትክክል አልታወቀም፡፡ እስከ ዘጠኝ የሚያደርሱትም አሉ፡፡ ነገር ግን በተለያየ ቀን አርበኛ በገበያ ላይ ማስቀላቸው ተረጋገጠባቸው፡፡ ይህም ሆኖ አርበኛው በሽማግሌው ላይ የሞት ፍርድ አልፈረደባቸውም፡፡ ነገሩ ሳይቆረጥ ታላቅ የጣልያን ጦር መጣ፡፡ ድብልቅልቅ ያለ ጦርነት ተደርጐ ጣልያን ተሸንፎ ሸሸ፡፡ ብዙ አርበኞች ሞቱ፤ ብዙዎች ቆሰሉ፡፡ ጣልያንን

መርቶ ያመጣው የደጃዝማች መሸሻ ተወንድ በላይ ልጅ መሆኑና የመጣውም እሳቸውን ለማስለቀቅ እንደነበረ ታወቀ። አርበኛው ትዕግሥቱ አለቀ። በሕይወት ይኑሩ የሚል አንድ ሰው ጠፋ። በጐራዴ በጣጥሶ ጣላቸው።[3] በትዕግሥት የተያዘው የፍርድ ሥራ በደም ፍላት መፈጸሙ ያሳዝናል። ቢሆንም አርበኛው ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት ያደረገውን ጥረት ማጤን ይገባል።

ንጉሠ ነገሥት መልአክ ፀሐይ ኢያሱ ከትም ወይራ፣ አኩፎ አገር አቶ ቸሬ ቤት በነበሩ ጊዜ፤ አምስት አርበኞች ተከስሰው ከችሎት ነሐሴ 23 ቀን 1930 ዓ.ም ቀረቡ። ክሱም ብር አምጡ እያሉ ሁለት ገበሬዎች በእሳት ጠብሰዋል የሚል ነበር። ሁለቱ መጥበሳቸው፣ አንዱ ዝም ብሎ ቆሞ ማየቱ፣ ቀሪዎች ሁለቱ ጠበሳው ይካሄድበት የነበረውን ቤት ለቀው መውጣታቸው በምስክር ተረጋገጠ። ፍትሐ ነገሥት በመምህር ቀጸላ እጅ ወጣ። ሕግና ማስረጃ ከተሰማ በኋላ የአርበኞች መሪዎች አንድ በአንድ እየተነሱ ተቹ። ቆሞ የተመለከተው አርባ ጅራፍ ተገረፈ። ሁለቱ ቤቱን ጥለው የወጡት በነፃ ተለቀቁ።[4]

ጣልያን የእናቴን የወይዘሮ ፀዳለ አባበለውን አያት የአቶ ተክሌ ቢረሴን፣ ዳዊት አገር የተባለውን መልከኛነት ታደሰ ለተባለ ባንዳው ሰጠው። ጣልያን ይህንን ያደረገው እኔ ለአለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴ ስንቅ አቀባይ መሆኔን በሰላዮቹ አማካኝነት አጣርቶ አምጡ ብሎ ቢጠይቅ፤ ሽማግለዉ ቅድም አያቴ አልሰጥም በማለታቸው ነበር። መልከኝነቱ በአዋጅ ለባንዳው የተዛወረ ስለሆነ ለእኔ በአዋጅ እንዲመለስ አስፈለገ።

ጉዳዩ ለንጉሠ ነገሥት መልአክ ፀሐይ ጭንቅት አቶ ተክለወልድ ቤት በነበሩ ጊዜ በጥር 5 ቀን 1930 ዓ.ም ቀረበ። ቀኛዝማች /ደጃዝማች/ ከበረ ኃይለሥላሴ በመቃወማቸው ክርክር ተነሣ። የቀኛዝማች ከበረ ሃሳብ "ከዚህ ያለነው ለሀገራችን ነፃነት ለመከላከል እንጂ መሬት ለመከፋፈል አይደለም። መሬት መከፋፈል ከተጀመረ ማብቂያ አይኖረውም። ሠራዊቱን ከጥቅም ክፍፍሎሽ ውስጥ ያስገባል" አሉ። "የመሬት ክፍፍሎሽ ይጀመር ቢባልም እንኳን፤ እንዴት በዚህ አንድ ፍሬ ሕፃን ይጀመራል?" ብለው ጠየቁ። የእኔ ቤተሰቦች ደግሞ "ጥያቄው የመሬት ክፍፍሎሽ አይደለም። ጣልያን የነቀለው ይመለስለት የሚል እንጂ" አሉ። የደጃዝማች ኃይሉ ወልደመድኅን ሃሳብ ከቀኛዝማች ከበረ የተለየ ሆነ። "ከሁላችን ነጥሎ መሬቱን ከነቀለው፤ ስለዚህ ልጅ አገልግሎት ጣልያን ያወቀው ነገር አለ ማለት ነው። ሕፃን ነው ተብሎ እንደተነቀለ ይቅር አይገባም። ይመለስለት" አሉ። ክርክሩ ጠነነ። ንጉሠ መልአክ ፀሐይ አኩፎ አገር አቶ ቸሬ ቤት በነበሩ ጊዜ ነሐሴ 24 ቀን 1930 ዓ.ም ለሁለተኛ ጊዜ ቀረበ። ራስ አበበ ለእኔ የመመለሱን ሃሳብ ስለደገፉ ተፈረደልኝ። በጸሐፊ ትዕዛዝ /ኰሎኔል/ ኪዳኔ ወልደጊዮርጊስ የተፃፈ ደብዳቤ ተሰጠኝ።[5]



በኅዳር ወር 1931 ዓ.ም ተድላማርያም፣ ጎርጉ ከፊታውራሪ ወልደፃድቅ ችሎት ቀረበ። ወንጀሉ አርበኞችን አባብሎ የማስከዳት ሥራ አካሄዶአል የሚል ነበር። አረርቲ ከነበረው ጣልያን ለግራዝማች ዳኜና ለባልደረቦቻቸው የተጻፈ ደብዳቤ ከኪሱ፣



ሁለት ጠርሙስ ነጭ አረቄና ፊራንካ ከትክሻው ተገኘበት። ደብዳቤ የተጻፈላቸው ሰዎች ስማችንን ለማጥፋት፣ በጦር ባልደረቦቻችን ዘንድ እምነት ለማሳጣት የተካሄደ ሴራ ነው በማለት በተፈራጅነት ቆሙ። አርበኛው ይሙት በቃ ስለፈረደበት ተሰቀለ።[6]

ቡልጋ፣ ጭቃ ቆላ ሰኔ 21 ቀን 1931 ዓ.ም በተደረገው ጦርነት ብዙ የጠላት ወታደሮች ተማረኩ። ሰኔ 23 ቀን ለፍርድ ከአርበኛው ጉባዔ ቀረቡ። ከሐረርጌ የመጡ ባንዶች ነበሩ። ሁልጊዜም ይደረግ እንደ ነበረው፣ ራስ አበበ አረጋይ "እናንተ ኢትዮጵያውያን ሁናችሁ እንዴት ሀገራችሁንና ሰንደቅ ዓላማችሁን ትወጋላችሁ?" ብለው ጠየቋቸው። በወቅቱ ይኼን ዓይነቱ ጥያቄ በአርበኞች ዘንድ የተለመደ ነው። ለተማራኪዎች አመክሮ ለመስጠትና ይቅርታ እንዲጠይቁ፤ በዚህም አርበኛው ከቁጣ ወደ ትዕግሥት እንዲመለስ ለማድረግ ነው። ተማራኪው ተገድጄ ነው፣ ተሳስቼ ነው፣ ባለማወቅ ነው ይላል። አርበኛው የተለየ ጥፋት ያልተገኘበትን ይለቀዋል። ነገር ግን ያን ዕለት

እንደዚህ ሳይሆን ቀረ። የተለየ ነገር ተፈጠረ። ከተማሪኪዎቹ አንዱ "እናንተ ሌቦች፣ ምን ሰንደቅ ዓላማና ምን ሀገር አላችሁ" አለ። ሌላም ብዙ የስድብ ቃል ተናገረ። ሌሎች ምርኮኞች ዝም አሉ። እነሱ ከመጡበት የምሥራቅ ኢትዮጵያ አካባቢ የሚኖሩ ዜጐች አነጋገር እንደዚህ ግድየለሽ መሆኑን ያጤኑ ማንም የለም። ሰውየው የተናገረው የሁሉንም ሃሳብ እንደ አጠቃለለ ተቆጠረ። ከአርበኞቹም ወገን ይህ የሁላችሁ ቃል ነውን? ብሎ የጠየቀ ወይም አንድ በአንድ እንዲናገሩ ሃሳብ ያቀረበ የለም። በዚሁ ብቻ በደምፍላት ፍርድ ተሰጠ። ሁሉም በጥይት ተደበደቡ።[7] ለነገሩ የተናጋሪው ድፍረት ከባድ ነው፣ እውነትም ሊቀጣ ይገባዋል። ነገር ግን ሌሎች ሃሳባቸውን ሳይጠየቁ መገደላቸው ያሳዝናል።

በወንጀል ተይዘውና በጦር ሜዳ ተማርከው ለሚቀርቡ ሰዎች ትክክለኛ ፍርድ ከመስጠቱም በላይ፣ አርበኛው የመተዳደሪያ ደንብ እያወጣ በሥራ ላይ ያዋለበትም ጊዜና ቦታ አለ። ለምሣሌ ማናቸውም ወንጀል ለጠቅላላው አደባባይ ይቀርባል። አለቃው በሥልጣኑ አንዳች ነገር አያደርግም። አርበኛውም በነፃ ተከራክሮ በድምፅ ይወስናል። ተቃዋሚ ከአለ፣ ፍርድ አይፈጸምም። በመንዝ ልጅ ግዛቸው ኃይሌ ለአርበኞች አንድ የውስጥ ደንብና ሕግ አውጥተው ነበር። የወጣውም ደንብ የሁለት ዕዳ ከፋይ የሆነው ገበሬ ያለ አግባብ እንዳይነካ የሚከለክል ነበር። ደንቡን የተላለፉ ቅጣት ደርሶባቸዋል።[8]

ለባንዶች ጭምር ፍትሕ የታየላቸው፣ እየተማረኩ በምክርና በማስጠንቀቂያ የተለቀቁ እጅግ ብዙ ናቸው። እዚህ ላይ ግን የአንድ ሰው ጉዳይ መጥቀስ እወዳለሁ። ፊታውራሪ ተሰማ ከተማ ይባል ነበር። ቤቱ ቡልጋ የቀር፣ ልዩ ስሙ ከጉንባር ከሚባል ቦታ ነበር። ለጣልያን ዋና ጉዳይ ፈፃሚ ሆነ። በወናና በእመየት አገር በራሱ አዛዥነት በአርበኞች ላይ ዘምቶ ረጅም ጊዜ የወሰደ ውጊያ አካሄደ። ብዙ ሰው አስፈጀ። የተማረከውንም ከተማ እሱ ራሱ ወስዶ እየሠጠ፣ አሥራ ሦስት ሰዎች ቤት ተዘግቶባቸው ተቃጠሉ። አያያዙ አርበኛውን የማያፈናፍን ሆነ። በአርበኞች በኩል ተመከረ። በበቅሎ እየተቀመጠ ወዲያ ወዲህ በሚልበት ጊዜ ላይ፣ እሱን በረጅም መውዜር መዘንጠፉ ብቸኛውና ቀላሉ መፍትሄ ሆነ።

ነገር ግን አርበኛው እንደዚህ ማድረግ አልፈለገም። በንጉሠ ነገሥቱ ጊዜ በልጅ ኢያሱ ምኒልክ ምክንያት ታሥሮ ብዙ መንገላታት የደረሰበት መሆኑንና በዕድሜው አረጋዊ መሆኑን አሰበ። ከሶ ለማሠር ወሰነ። ከጣልያን እጅ እንደሚደርስ ተደርጐ አንድ የሃሰት ወረቀት በስሙ ተጻፈለት።[9] ቃሉም የጻፈው ወረቀትና የላከው ገንዘብ መድረሱን እየገለፀ ምስጋና የሚያቀርብ ነበር። ደግሞም ለአቀረቡልን ጥያቄ መክረን መልስ እንሰጣለን የሚል ቃል ነበረበት። ወረቀቱ ሸዋ ጣልያን እጅ በአንድ በተማረከ ሰው እጅ ደረሰ። ሽማግሌው ቢጠየቅ ሽፍቶቹ እንዲገቡ ለማባበል ብሎ እንደሆነ ስለገለጸ ሌላ



ቅጣት ሳይደርስበት ቀረ። ሆኖም ሰኞ ከተማ በግዞት እንዲቀመጥ ተወሰነበት። ቡልጋ ለአርበኞች እንቅስቃሴ ነፃ ሆነች።

በጐንደርም ተመሳሳይ ፍርድ ተሰጥቶአል። ጐንደር ፀገዴ በምድረ ገበታ ጦርነት ዕለት በ1932 ዓ.ም ብዙ የሽሬ ባንዶች ተማርከው ለአርበኛው ጉባዔ ቀረቡ። በጦርነቱ ብዙ አርበኞች ወድቀው ነበርና የምርኮኞቹ ይቀጣሉ አይቀጡም ጉዳይ እጅግ አከራከረ። እኩሉ ሀገራቸውን ኢትዮጵያን ከድተው ለጠላት ረድተው፣ ወገኖቻቸውን የኢትዮጵያን አርበኞች ወግተዋልና ሞት ይገባቸዋል አለ። እኩሉ ደግሞ መሪ ሆነው ያመጡአቸው ይቀጡ እንጂ፣ ተገድደው የመጡ ገበሬዎች ሊቀጡ አይገባም አለ። ትግራይ ቀደም ብሎ የጠላት ጦር የገባበትና ብዙ ጉዳት የደረሰበት አገር መሆኑ ጭምር ከግምት ውስጥ ገብቶ፣ ምርኮኞቹ ሊቀጡ አይገባም የሚለው ወገን አመዘነ። ተዘዋውረው የአርበኛውን ሁኔታ እንዲያዩና በሽኝ ወደ ሀገራቸው እንዲላኩ ተወሰነ። በአመክሮ ተለቀው አገራቸው እንዲገቡ ተደረገ።[10] ፍርዱ ፖለቲካ ጉረስ ቢሆንም ሊመሰገን ይገባዋል።

በጐንደር ከተካሄዱት የፍርድ ጉዳዮች ሁሉ አርበኛውን እጅግ ያከራከረው ለአስታራቂነት የመጣ አንድ የጣልያኖች ቡድን ጉዳይ ነበር። ጦርነቱ እያየለባቸው ሲሄድ ጣልያኖች የጠሩን ሥራ ወደ ነገር ለማዞር ሞከሩ። ከሮም ለዚሁ ጉዳይ ተብሎ በተላከ የፋሽስት ፓርቲ አባል የተቀነባበረ አንድ ቡድን በጐንደር አሰማሩ። ቡድኑ ሁለት ኰሎኔሎች አንድ ሻለቃና ሁለት መቶ አለቆች ነበሩበት። ይህ ቡድን ኰሎኔል በኒሎና ኰሎኔል አንጀሊኒ በሚባሉ መኰንኖች እየተመራ ወደ በለሳ መጣ። ቡድኑን ወረሐ ላይ ፊታውራሪ ደምስ ተሰማ ተቀብለውት በጉዞ ላይ እንደአለ፣ ተለዋጭ ትዕዛዝ በቀኛዝማች ተስፋ ኃይሉ እጅ ስለደረሰ እጃቸውን በሰንሰለት ታሥረው ከደጃዝማች ዳኜው ተሰማ ችሎት ቀረቡ።

አርበኛው በደጃዝማች ዳኜው ተሰማ ሰብሳቢነት ጉባዔ ሠርቶ ተከራከረባቸው። የጐንደ ተክለ ሃይማኖት ገዳም ካህናትና መነኮሳት ስዕልና መስቀል ይዘው፣ ለእርቅ የመጣ ሰው መነካት የለበትም ብለው ቆሙ። ገሚሱ አርበኛ ጣልያኖቹ የአርበኛውን ኃይል ለመቀነስ የመጡ ስለሆነ ይገደሉ አለ። ከፊሉ ደግሞ ለእርቅ የመጣ ሰው በምን ሕግ ይገደላል አለ። ነገሩ በአንድ ክፍል ብቻ ሊወሰን ስለአልቻለ መላው የበጌምድር አርበኛ አብናት ላይ ጉባዔ አድርጐ እንዲወሰን ጥሪ ተላለፈ። ብዙዎቹ ተሰበሰቡ። አንዳንዶቹም ሰው እየመረጡ ላኩ። ደጀዝማች ብሬ ዘገየ "...የሚገድል ሰው ጠፍቶ እንደሆነ ለኛ ላኩልን..." የሚል ደብዳቤ ጻፉ።

ሆኖም አብናት ላይ ጠቅላላ ጉባዔ ተደረገና እሥረኞቹ ቀረቡ። ቃላቸውን ተጠይቀው የእርቅ ሥራ ለመሥራት መምጣታቸውን አስታወቁ። አርበኛው የግራ ቀኙን ሃሳብ ከመረመረ በኋላ "...ለሰላማዊ ነገር የመጡና በጦርነት ያልማረክናቸው ስለሆነ ሊገደሉ አይገባቸውም" ብሎ በድምፅ ብልጫ

ፈረደ፡፡ ነገር ግን በነፃ አለቀቃቸውም፡፡ እርቅ ከፈለጉ የደብረ ታቦርን፣ የይፋግን፣ የጣራ ገዳምን፣ የደጉማን፣ የአምባ ጊዮርጊስን ጦር አስነስተው እንዲወስዱና በእነዚህ ቦታዎች የሚገኘውን የጦር መሣሪያ ለአርበኛው እንዲያስረክቡ ሲል ወሰነ፡፡ ይህ እስኪፈጸም ጣልያናውያኑ ታስረው እንዲቆዩ ስለ ወሰነባቸው፤ እናም በለሣ፣ ደራ ማርያም ከአለው እሥር ቤት ገቡ፡፡

ይህ ጥያቄ ጐንደር ከተማ ለጣልያኖች ሲደርስ፣ ታላቅ ችግር ፈጠረ፡፡ የሰላም ጥረቱ ተቀባይነት ሲያጣ ለአስታራቂነት ከሮም የመጣው ሹም ዕለቱን ወደ ሀገሩ በአይሮፕላን በረረ፡፡ እጅግ የሚያሳዝነው ከላይ በተዘረዘረው ዓይነት በሕግና በፖለቲካ የተያዘውን ነገር፤ ጠላት በአሥራ ስድስት ረድፍ /እስኳድሪ/ ፈረሰኛ ጦር አሰልፎ፣ አርባ አይሮፕላን አስነስቶ ታላቅ ጦርነት በማካሄድ፣ እሥረኞቹን በጥቂት ወላዋዮች ትብብር ጭምር ነጥቆ ለመውሰድ መቻሉ ነበር፡፡ ምንም የነገሩ ሂደት ተጣምሞ ከሚያስቆጭ ፍፃሜ ላይ ቢደርስ፣ ፍርዱ ትክክል ነበር፡፡[11]

በጐጃም ከተከናወኑት የፍርድ ሥራዎች ሊጠቀስ የሚገባው፤ ተማርካ የታሰረችውን የሻሽ ወርቅ በላይ የተባለችውን ልጃቸውን እናስለቅቃለን በሚል ምክንያት ከደጃዝማች በላይ ዘለቀ ዘንድ የመጡት ባንዶች ጉዳይ ነበር፡፡ የጣልያን ደብዳቤ በአርበኞቹ ጉባዔ ላይ ከተሰማ በኋላ፤ ልጅ በላይ ከጣልያን መንግሥት ጋር መታረቅ ሀገራቸውን መሸጥ መሆኑን ገልጸው፣ በምንም ዓይነት የእርቁን ሃሳብ እንደማይቀበሉ አስታወቁ፡፡ ለእርቁ አማላጅ ሆነው የመጡት ባንዶች በኢትዮጵያ አርበኞች ላይ ይሙት በቃ ይፈርዱ የነበሩት ቀኛዝማች እጅጉ ለማና ቀኛዝማች አደራ ያለው ስለነበሩ፣ በእነሱ ላይ ፍርድ ተያዘ፡፡ አርበኛውም እነዚያ ሁለት ባንዶች በአርበኛ ላይ እየፈረዱ ደም ሲያፈስሱ የኖሩ፤ የጦር ጓደኞቹን ከምድር ገጽ የጠረጉና የጨፈጨፉ ስለሆኑ እና ሞት ይገባቸዋል ብሎ በሙሉ ድምፅ ስለወሰነ በ1930 ዓ.ም በቦከና አደባባይ በስቅላት ተቀጡ፡፡ አብሮአቸው የመጣው አስተርጓሚ ግን በደል ስለአልተገኘበት ተለቀቀ፡፡[12]

በጉራጌ አገር የነበሩ አርበኞች የሚከተሉትም ሥልት ተመሳሳይ ነበር፡፡ ካርቱም ከተባለው ውጊያ በርካታ የወለኔ ታጣቂዎችና የሻንቅላ ባንዳዎች በሐምሌ ወር 1930 ዓ.ም ተማረኩ፡፡ ሀገራቸውን ኢትዮጵያን ከድተው ከጠላት ጐን ቆመው በመዋጋታቸው ቆሌ በተባለው ገበያ በአደባባይ ተሰቀሉ፡፡

የቡልጋን አካባቢ በአስታራቂነት ስም እየተዘዋወረ ለጣልያን ምሥጢር ይሰበስብ የነበረው ሙሴ ቀስተኛ ከደጃዝማች ገረሱዱኪ ዘንድ ደረሰ፡፡ አርበኛው በጉባዔ ተሰብስቦ የመጣበትን ጉዳይ እንዲናገር ፈቀደለት፡፡ የሙሴ ቀስተኛ አመጣጥ ከተሰማ በኋላ የአርበኛው ድምፅ ከሁለት ተከፈለ፡፡ አንደኛው ወገን ለእርቅ ከመጣ ሊቀጣ አይገባም ሲል፤ እኩሉ ደግሞ ሊቀጣ ይገባል አለ፡፡ በክርክሩ ጊዜ የሙሴ ቀስተኛ መሰሪ ተልዕኮ አርበኞች በትውልድ ሀገራቸው የሚያደርጉትን ትግል የሚያዳክም መሆኑ ተነገረ፡፡ ቀድሞ ከራስ



ደስታ ዳምጠውና ከደጃዝማች ገብረ ማርያም ዘንድ ሄዶ እንደነበረ፤ ኋላ ከራስ አበበ አረጋይ ዘንድ ሄዶ ይህንኑ ሥራውን እንደአካሄደ፤ አሁንም የመጣው ይህንኑ የማሳሳትና የስለላ ሥራውን በመቀጠል እንደሆነ ስለተገለጸበት፣ ይቀጣ የሚለው ወገን አመዘነ፡፡ እሱም አቄሮ በተባለው ቦታ መስከረም 19 ቀን 1931 ዓ.ም በጥይት ተደበደበ፡፡ አብረውት የመጡት ሽማግሌዎች ግን በደል ስለአልተገኘባቸው በደህና ተመለሱ፡፡[13]

በአርበኝነት ጊዜ ሕግ ይከበር ነበር፡፡ ወንጀል የሠራ አይለቀቅም፤ ለፍርድ ይቀርባል፡፡ ችሎት በሚገባ ተሰናድቶ፣ ፍርድ ይደረጋል፡፡ ከሳሽ፣ ተከሳሽ ይከራከራል፡፡ ምስክር በወንጌል፣ በመስቀል እየማለ ይመሰክራል፡፡ ተቺ ይተቻል፡፡ በአደባባይ ያለ ሰው ሁሉ በየተራ እየተነሳ ያለ አንዳች ተፅዕኖ «ይፍረድብኝ፤ ሠይፍ ይፍረድ» እያለ ይፈርዳል፡፡[14] የሃሳብ ልዩነት በተፈጠረ ጊዜ ብዙሃኑ የደገፈው ወገን ይጸናል እንጂ፣ አለቃ ባለ ብቻ አይወሰንም፡፡ ስለአርበኞች ሕግ አክባሪነት ብዙ ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል፡፡ ነገር ግን አንባቢ ልቦናው የሚያምን እስከሆነ ይኸው ይበቃል፡፡ ምንም እንኳን በአርበኝነት ጊዜ የተሰጠ ፍርድ ሁሉ ትክክለኛ ነበር ባይባልም፣ ከነፃነት በኋላ የታየውን ያህል ጉስቋላ ግን አልነበረም፡፡

## <u>ማጣቀሻ ፅሑፎች</u>

1. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 38፡፡
2. ከአቶ /ሃምሣ አለቃ/ ወልደ ጊዮርጊስ የተነገረኝ፡፡
3. ሙሉ ሰው ምትኩ፣ *የአርበኞች ትግል ከፋሽስት ጋር*፣ ገጽ 16-17፡፡
4. ጸሐፊው ራሱ ያየው፡፡
5. አባሪ 41.1 ይመልከቱ፡፡
6. ጸሐፊው ራሱ ያየው፡፡
7. ታደሰ ዘወልዴ፣ ገጽ 137፡፡
8. ታደሰ ዘወልዴ፣ ገጽ 248፡፡
9. ደብዳቤ የተጻፈው በአለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴ ነበር፡፡
10. ገሪማ ታፈረ፣ ገጽ 136-137፡፡
11. ገሪማ ታፈረ፣ ገጽ 212-214፡፡
12. ዘውገ ዘገየ፣ *አባ ኮስትር፣የደጃዝማች በላይ ዘለቀ ታሪክ*፣ ገጽ 19-20፡፡
13. ታቦር ዋሚ፣ *አባ ቦራ፣ የደጃዝማች ገረሱ ዱኪና የሌሎችም አርበኞች ታሪክ*፣ ገጽ 57-61፡፡
14. ሠይፍ ይፍረድ የሚባለው "ነፍስ ባልገደለ ሰው ላይ ይሙት በቃ ተፈርዶ፤ የተፈረደበት ሰው በሠይፉ ሲመታ የተመታው ቀርቶ ቆሞ ይመለከት የነበረው ነፍሰገዳይ ጭንቅላት ተቆረጠ" የሚል ጽኑ እምነት ስለአለ ነው፡፡

# ምዕራፍ አርባ ሁለት
# የጣልያን የግፍ ሥራዎች

በዓለም ላይ ብዙ ጦርነቶች ተካሄደዋል። በጦርነት ደግሞ አሸናፊና ተሸናፊ መኖሩ ያለ ነገር ነው። ጣልያኖች ራሳቸው ብዙዎቹን ወግተዋል፣ ድል አድርገዋል፣ ገዝተዋል፤ እንግሊዞችን፣ ግሪኮችን ጭምር። እንደ ኢትዮጵያ የጨከኑበት በታሪክ ውስጥ ያለ አይመስልም።

በመጀመሪያ ደረጃ ለጦርነቱ ከቅኝ ግዛት ፍላጐት በስተቀር ሌላ ምክንያት አልነበራቸውም። የ1888 ዓ.ምቱን ጦርነት የጀመሩት ኢጣሊያኖች እንደ መሆናቸው፣ በዚያኛውም ሆነ በዚህኛው ኢትዮጵያ የበደለቻቸው ምንም ሁኔታ የለም። ጦርነቱንም በራሳቸው ፍላጐት ከከፈቱ በኋላ በሥርዓት አላካሄዱትም። ፍጹም ጭካኔና አረመኔነት አሳይተዋል። ወታደር ብቻ ሳይሆን ልጅ አዋቂ፣ ሴት ሽማግሌ፣ ቄስ መነኩሴ ሳይል በመላ የኢትዮጵያውያንን ዘር ከምድር ገጽ ለማጥፋት፤ ከመሪ እስከ ተራው ሕዝብ ድረስ ተባብረው በሙሉ ኃይላቸው ተጣጥረዋል። ለዚህ አንድና ሁለት የለውም። በዓለም የተከለከለ መርዝ እየረጩ ሰውና አራዊትን አንድ አድርገው ፈጅተዋል። ይህ አፈፃፀም ዓለም የተገረመበት ግፍ ነው። በፈቃዳቸው ራሳቸውን ለሀገራቸው ነፃነት መስዋዕት አድርገው አቅርበዋልና፣ ወደ ጦርነቱ ገብተው ጦርነቱ በተደረገበት ቦታ ላይ በተፈፀመው እልቂት የሞቱትን በግፍ እንደ ተገደሉ አይቆጠርም። በዚህ ምዕራፍ የምንመለከተው፣ በተለይ በሰላማዊው ሰው ላይ የተፈፀመውን ግፍ ነው።

በአምስቱ ዓመታት፡- 17,500 ሴቶችና ሕፃናት እንደሞቱ፣ ተማርከው እንደ ተገደሉ 24,000፣ በእሥር ቤት ደግሞ 35,000 እንደ የሞቱ ተመዝግቦአል። በድምሩ በሦስቱ ዓይነት አሟሟት የሞቱት 76,500 ናቸው ማለት ነውን? ይህ ቁጥር እጅግ አነስተኛ ነው። እንደኔ ከ300,000 ሲያንስ አይታየኝም። ከየካቲት 12 እስከ 14 ቀን በተካሄደው እልቂት የሞቱት ሰዎች ብዛት 30,000 ሊሆን ይችላል። ቢበልጥም ከዚያ በትንሽ ነው። በስደትና በረሃብ የአለቁት 300,000 የሚደርስ ሳይሆን አይቀርም።[1] ስለዚህ በአምስቱ ዓመት ከ600 ሺህ እስከ 700 ሺህ ይደርሳል። በዚህ ላይ ደግሞ 2,000 አብያተ ክርስቲያናትና 525,000 ቤቶችን ጠላት እንደአቃጠለ ተዘግቦአል። ይህ እውነት ሊሆን ይችላል።

የጣልያኖች ጭካኔ የሚለካው በፈጁት ሰው ብዛትና ባቃጠሉት ቤተክርስቲያንና ቤቶች ብቻ አይደለም። ከአገዳደላቸው ጭምር ነው። ቤት እየዘጉ በእሳት ያቃጠሉአቸው ብዙ ናቸው። መርዝ ያርከፈከፉባቸው አያሌ ናቸው። እጅ ወይም እግራቸውን በሽቦ እያሰሩ በመኪና የጐተቱአቸው



በርካታ ናቸው። እጃቸውን ከአንድ መኪና፣ እግራቸውን ከሌላ መኪና ላይ አሥረው መኪናዎቹን ግራና ቀኝ በመንዳት የበጣጠሱአቸውም አሉ። ከእነነፍሳቸው የተቀበሩ አሉ። ምንም እንኳን የመስቀል ቅጣት በጥንት ዘመን የተለመደ ነው ሊባል ቢችልም፣ ይኼኛው በጠቅላላው የኢትዮጵያን ህዝብ ከምድር ገጽ ለማጥፋት ሲሉ ያላደረጉት ነገር የለም። ወንዱ እንዲሰለብ፣ ሴትዋ ጡትዋን እንድትቆረጥ አድርገዋል። የእሥራት ሥርዓታቸው ደግሞ እጅግ የከፋ ነበር።

በአጠቃላይ ስለፋሽስት ጣልያኖች ጭካኔ ይህንን ያህል ከአወሳን በኋላ፣ ለናሙናም እንኳን ቢሆን አንዳንድ ሥራዎቻቸውን ማየት ይገባናል። በአንድ ቦታና ጊዜ ከተካሄዱት እልቂቶች ዋነኛው ከየካቲት 12 እስከ 14 ቀን 1929 ዓ.ም አዲስ አበባ ላይ የተካሄደው ነው። ተደጋግሞ እንደተገለፀው ያለቀው ሕዝብ ከ30,000 ቢበልጥ እንጂ አያንስም። በአገዳደሉም ረገድ ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት የጭካኔ ሥራዎች አብዛኞቹ ተፈጽመዋል። ለግርግሩ በቂ ምክንያት ነበር። ይህ አይካድም። ከ8-10 ያህል ቦምቦች ተጥለዋል። ሠላሳ ያህል ጣልያኖች ቆስለዋል። ሁሉም ሹማምንት ነበሩ። የተጣለው አደጋ ቀላል አይደለም። ሲሻኝ ጢስ ወጋኝ ባይሆን ኖሮ ጣልያኖች በመላ ከተማዋ ሦስት ቀን ሙሉ እልቂት ባላካሄዱም ነበር። ምንም ለጣልያኖች ጩኸትና ግርግር ባሕርያቸው ቢሆን፤ ከሁለትና ሦስት ሰዓት የበለጠ ሊሸበሩ፣ ከስድስትና አራት ኪሎ ያለፈ እልቂት ሊያካሂዱ ባልተገባቸውም ነበር። ሆን ተብሎ የተካሄደ ጭካኔ ነው። በድጋሚ ሌላ አንዳች አደጋ አልደረሰም ነበርና።

ከደብረ ሊባኖስ ገዳም ከ350 የማያንሱ መነኮሳት ገደሉ። የቀሩትን ደግሞ ወደ ደብረ ብርሃን ወስደው ከዚያ ሲደርሱ 42 ገደሉ። ከዝቋላ ገዳም 100፣ ጐንደር ከማኅበረ ሥላሴ በየጊዜው ባካሄዱት ግድያ ከ150 ያላነሱ መነኮሳት ፈጁ። ሰበቡ ሕዝብ አነሳስታችኋል፣ መሣሪያ ደብቃችኋል ነበር። የጣልያኖቹ ጥርጣሬ ሙሉ በሙሉ ውሸት ነው ወይም እውነት ነው ለማለት ያስቸግራል። አሳዛኙ ነገር ከዳኛ ፊት ሳይቀርቡ፣ ጥፋታቸው ሳይረጋገጥ በጥርጣሬ ብቻ ማለቃቸው።

በጦር ሜዳ የተማረከ ሰው አይገደልም። ጣልያኖች ግን የማረኩትን አለቀቁም፣ ገደሉ። ከሥራቸው ሁሉ የከፋው ደግሞ «አንነካህም፣ ግባ» እያሉ፣ በቄስ መነኩሴ እያባበሉ አስገብተው፣ ብዙ ሰው ፈጁ። ለዚህ የክህደት ግብራቸው በመርሐ ቤቴ የደጃዝማች አበራና ደጃዝማች አስፋው አገዳደል ማስረጃ ነው። እንደዚሁም በቡልጋ የሸለኄውን ፊታውራሪ መኩሪያን አስገብተው ደብረ ብርሃን ወስደው በነሐሴ 1928 ዓ.ም 42 ራሳቸውን ገደሉአቸው።

የብዙ አርበኞችን ራስ እየቆረጡ በአደባባይ ጊጤ ተጫውተውበታል። በቡልጋ ይህ ሥራ የተጀመረው በፊታውራሪ መኰንን ወልደጊዮርጊስ መሆኑን ጠቅሻለሁ። ከዚያ በኋላ አርበኛውም የጣልያንን ጭንቅላት እየቆረጠ በየገበያው ያዞረው ጀመር። ለምሣሌ ያህል ፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ አራጊቻ ብዙ መኪና ሰብረው ከፈጁአቸው ጣልያኖች ውስጥ የአንዱን ጭንቅላት ቆርጠው ጌጥ አጫውተውበታል።

ጐጃም፣ ባህር ዳር አንዲት ሴት በአንድ ልጅ ምክንያት አንድ ሰው ከስሳ ከአገረ ገዥው ዘንድ አቀረበች። ቀለብ ሥፈር ለማለት ነበር። ሕግ አዋቂው ጣልያን ልጁን በሸጉጥ ገድሎ እንዲካፈሉት አዘዛቸው። በጌምድር ውስጥ ደግሞ አባ ተስፋማርያም የተባሉትን መነኩሴ ሳይሞቱ ከነነፍሳቸው ቀበሩቸው። [2]

ቡልጋ፣ ሙገሬ ዛላ፣ ምስለኔ አገር አቶ አብሬ የተባለው ሰው አንድ ካርታ የመውዜር ጥይት ስለተገኘበት፣ ከግንድ ጋር አሥሮ፣ እንጨት ከላዩ ቆልሎ እሳት ለቀቀበት።[3]

አቶ እንግዳ ዘውዴ የተባሉትን ጐንደር የዱርጠ ሰው፣ ያለ አንዳች ጥፋት ይዞ ሆዳቸውን በካራ ቀደዳቸው። ይህም የማይበቃው ሆኖ ቁርበታቸውን ገፍፎ ከራስ ቅላቸው ሲደርስ፤ እንደ ፍየል ዘቅዝቆ ሰቀላቸው።

አንድ የጣልያን የጦር መኮንን በጦርነት ሞተ። የእሱን ደም ለመመለስ ከ150 ያላነሱ የአገሩ ሰዎች ተገደሉ። ከእነዚህ አሥራ ስድስቱን አንድ ቤት አጉሮ እሳት ለቀቀባቸው። ሦስት ሰዎችና አንድ ሕፃን ሰብረው ከቤቱ ወጡ። ሰዎቹ ሲያመልጡ ሕፃኑ ተያዘ። እንደገና መልሶ ከእሳቱ ጨምሮ አቃጠለው።[4]

ቡልጋ፣ በረከት የአንድ ጣልያን ጭንቅላት ተቆርጦ ከወደቀበት ወሬኛ አንስቶ ሰጠው። ሦስት መቶ የአገሩን ሰዎች በገመድ አሥሮ ሦስት ቀን ሙሉ በረሃብና በውሃ ጥም ከአሰቃያቸው በኋላ፤ ሜንሶ ወንዝ ላይ በመትረየስ ደበደባቸው። ይህም አልበቃህ ብሎ ጋዝ አርከፍክፎ አነደዳቸው።

የጣልያኖች የግፍ ሥራ ተነግሮ አያልቅም። ለማስረጃ ያህል ለምን እንዲህ እንደሆነ ብንመለከት ይሻላል። ሦስት ምክንያቶች አሉት። አንደኛው ጣልያናውያን በኢትዮጵያውያን ላይ ያላቸው ቂም ሲሆን፤ ሁለተኛው የሞሶሊኒ ጨካኝነት ነው። ሦስተኛው በወቅቱ የነበረው የርዕዮተ ዓለም ሁኔታ ነው። እነዚህን ሦስት ነጥቦች አብስሎ ማየት በኢትዮጵያ ላይ ለተፈፀመው ግፍ ምንጩ ምን እንደሆነ ፍንጭ ይሰጣል።







ሬሳዎችን ለማቃጠል ቤንዚን በበርሜል ቀረበ



በመርዝ የተቃጠለ የኢትዮጲያዊ እግር





ሬሳዎችን ለማቃጠል ቤንዚን በበርሜል ቀረበ



በመርዝ የተቃጠለ የኢትዮጲያዊ እግር



በመርዝ የተቃጠለ የኢትዮጲያዊ እጅ።

በመጨረሻው ነጥብ መጀመር ይሻላል። በዚያን ዘመን በኢጣልያ የፋሽስት፣ በጀርመን የናዚ፣ በራሺያ የኰሚኒስት ፓርቲዎች ሰፍነው ነበር። እነዚህ ሦስት የፖለቲካ ፓርቲዎች የየራሳቸው የሆነ ርዕዮተ ዓለም ነበራቸው። አመለካከታቸው ለዓለሙ ለውጥ ስለሚያስፈልገው አዲስ ዓይነት የአስተዳደር ሥነ ሥርዓትና የአመራር ሥልት እንዲቀየስ የሚያምኑ ነበሩ። በርዕዮተ ዓለም ይለያያሉ። ነገር ግን በአንድ ነገር ይስማማሉ። ይህም ሃሳባቸውን በኃይል የማስፈፀም ጉዳይ ነው። በኃይል መጠቀም እንደማይቀርና እንደሚያስፈልግ በመጀመሪያ ያመኑ ፋሽስቶች ነበሩ። እውነት በመናገራቸው ሊመሰገኑ ይገባቸዋል። የናዚና የኮሚኒስት ርዕዮተ ዓለም አራማጆች የልባቸውን ሳይገልጹ፤ ሰላማዊ በሆነ መንገድ ሃሳባቸውን በሥራ ላይ እንደሚያውሉ ልፈፋቸውን ቀጠሉ። በግብር ሦስቱም አንድ መሆናቸው በኋላ ተገለጸ። ፋሽስቶች ኢትዮጵያውያንን፤ ናዚስቶች አይሁዶችንና ከቁጥጥራቸው ሥር ያስገቡአቸውን የአውሮፓ ሕዝቦች፤ ራሺያዎች በራሳቸው ሕዝብ ላይ የአረመኔነት ሥራ ፈጸሙ። በወቅቱ የፋሺስቶችን የግፍ ሥራ ገፈት በመቅመስ ረገድ ኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ ሀገር ነበረች። ከዚሁ የግፍ ሥራ ለመገላገልም የመጀመሪያዋ እርስዋው ሆነች።

ኢጣልያ ከፋሽስት ፓርቲ ርዕዮተ ዓለም ጋር አብሮ የተፈተለ የቂም ሸማ ተጐናጽፋ ነበር። ይህም ቂም በኢትዮጵያ ላይ ሆነ። ተደጋግሞ እንደተገለጸው የቂሙ መነሥዔ የአድዋ ጦርነት በኢትዮጵያ ድል አድራጊነት መጠናቀቁ ሆነ። የክብር፣ የሞገስ፣ የኢኮኖሚ ጥያቄዎች አብረው ተፈተሉ። ሞሶሊኒ ለሥልጣን የበቃበት ርዕዮተ ዓለም የጣልያንን ሕዝብ ችግር የማይፈታለት ሲሆን፣ የኢጣልያ ሕዝብ ኢትዮጵያ ላይ




እንዲያተኩር አደረገው። ለሕልውናው አስተማማኝነት በአለው ሁኔታ ውስጥ ገብቶ እንዲሰዋ፣ የኢጣልያን አገር ለመገንባት ኢትዮጵያውያንን ከምድረ ገጽ ማጥፋት አስፈላጊ እንደሆነ አድርጐ አሳየው። ሂትለር የአይሁዶችን ጥፋት፣ ስታሊን የቀድሞዎቹን ነገሥታት ወገኖች ማውደም ለአዲስ እርምጃ አስፈላጊ መሆኑን እንደ አሳዩአቸው ዓይነት ማለት ነው።

ከዚህ በተጨማሪ ሞሶሊኒ በተፈጥሮው ጨካኝ ሰው ነበር። የቀድሞዎቹን ጓደኞቹንና በኋላም የተነሱበትን ተቀናቃኞቹን በጭካኔ አጥፍቶአቸዋል። ዓለምን ለማንቀጥቀጥ የበቃውም በጭካኔው እንጂ በፖለቲካ ጥበቡ፣ በአስተዳደር ችሎታው አልነበረም። በዚህ የተፈጥሮ ጨካኝነቱ ላይ የጭካኔ ሥራ ለማካሄድ ቆርጦ የተነሣው የፋሽስት ፓርቲ መሪ ሆነ። ስለዚህ በአለው የተፈጥሮ ስሜትና ከፓርቲው በሚደረግለት ድጋፍ አንድ ላይ ተደምሮ፣ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ተነግሮ የማያልቅ የግፍ በረዶ አዘነመበት።

በኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩ ጣልያኖች በኢትዮጵያውያን ላይ የወደዱትን የማድረግ ሥልጣን ነበራቸው። የጦር መሪዎቹም በቀረበላቸው መሣሪያ ሁሉ እንዲጠቀሙ ተፈቅዶላቸው ነበር። ለዚሁ ሲባል ልዩ ልዩ ዓይነት ቦምብና መርዝ ተሠርቷል። ይኼን የሚጠራጠር ካለ፣ መርዙን የመርጫው መኪና ተሠርቶ አይሮፕላኖች ላይ የተገጠመው ኋላ ምን ሊደረግበት ነው? ኢትዮጵያ ላይ እንዲጣል፣ ኢትዮጵያውያንን እንዲፈጅ አልነበረም? ብሎ ራሱን ይጠይቅ። በመሆኑም ጣልያናውያን የሠለጠኑበትን፣ የታዘዙትን ሠሩ። ከሠለጠኑበት፣ ከታዘዙት የጭካኔ ሥራ አንዳች አላጐደሉም። በትክክል ያንኑ ፈጸሙ። የተዘጋጀውም መሣሪያ እጅግ በጣም ጥቂቱ ይክሸፍ፣ አንዳንዱ ይሳት እንጂ ለተዘጋጀበት ሥራ አገልግሎት ላይ ዋለ።

ይህ አባባል ታሪክን ማጉምዘዝ የሚመስላቸው የዋሆች አይጠፉም። የዚህ ዓይነት ስሜት ያደረባቸውን ወገኖች፣ ከየዋህ አመለካከታቸው ለመመለስ፣ እንዲሁም ለማገዝ ሲባል አንዳንድ ዘገባዎችን መጥቀስ ይገባል። ጄነራል ደቦና ተሸሮ ጄነራል ባዶሊዮ የተተካው ደቦኖ መርዝ መርጨት፣ ቦምብ መጣል አያስፈልግም በማለቱ ነው።[5] ሞሶሊኒ ለባዶሊዮ ከሮም ወደ አሥመራ በቁጥር 1070 ጥር 17 ቀን 1928 ዓ.ም /ጃንዋሪ 26 ቀን 1936/ ባስተላለፈለት የምሥጢር ቴሌግራም "...ወደፊት ለምታደርገው ጦርነት በእጅህ በሚገኘው በማናቸውም ዓይነት የጦር መሣሪያ እንድትዋጋ ሙሉ ሥልጣን ሰጥቼሀለሁ።..." ብሎታል። በምሥጢር ቁጥር 144 ባስተላለፈለት በሌላ ቴሌግራም ደግሞ እንዳለው "...ጦርነቱንም በቀረበልህ በማንኛውም የጦር መሣሪያ እንድታደርግ



በመርዝ የተቃጠለ የኢትዮጲያዊ እጅ።

ስፈቅድልህ ድሉ የኛ መሆኑን በማረጋገጥ ተስፋ እያደረግሁ ነው።" ማርሻል ባዶሊዮ ደግሞ ለጄነራል ግራዚያኒ በምሥጢር ቁጥር 1897 ባስተላለፈለት ሌላ ቴሌግራም "…በእጅህ በሚገኘው በማንኛውም ዓይነት መሣሪያ፣ በቦምብ በመርዝም፣ በሚቀርብልህ ዓይነት መዋጋት አለብህ…" ብሎታል። የማይጨውን ጦርነት ድል ካደረገ በኋላም ግድያው እንዲቀጥል ሞሶሊኒ ትዕዛዙን አንቆረቆረ። በምሥጢር ቁጥር 5007 ለባዶሊዮ ከሮም ወደ ደሴ ባስተላለፈው ቴሌግራም "…ማናቸውም ኢትዮጵያውያን የጦር መሣሪያ በእጃቸው ይዘው የሚገኙት ሁሉ ያለፍርድ እተያዙበት ሥፍራ በጥይት እንዲደበደቡ…" አዘዘ።

ጣልያን ኢትዮጵያን እንደያዘች ጄነራል ባዶሊዮ ተሽሮ ጄነራል ግራዚያኒ ከግንቦት 24 ቀን 1928 ዓ.ም /ጁን 1 ቀን 1936/ ጀምሮ የኢትዮጵያ ገዥ ሆኖ ተሾመ። የተሾመውም ግራዚያኒ በጭካኔ ሥርዓት የአስተዳደር ሥራዎችን መሥራት እንደሚችል የሊቢያ ገዥ በነበረበት ጊዜ በግብር አረጋግጦ ስለነበር ነው። እሱም የጭካኔ ሥራውን ወዲያው ጀመረ። በፕሮቶኮል መዝገብ ቁጥር 3386 ከአዲስ አበባ ለሥራ ኃላፊዎች ሁሉ ቅጂ በመስጠት ነሐሴ 26 ቀን 1928 ዓ.ም /ሰፕቴምበር 1 ቀን 1936/ በጻፈው ደብዳቤ፣ "…ካህናት የሚአመጡትን ማናቸውንም የመማለጃ ቃል ሳይቀበሉ በሚገባ የመበቀል ሥራ በሳስታ አውራጃ ሕዝብ ላይ ያለአንዳች ርህራሄ እንዲፈጸምበት ደጋግሜ አረጋግጣለሁ።…" የሚል መግለጫ ሰጠ። ከዚህም በስተቀር የላሊበላና የበልበላ ቀበሌዎች በኤፕሪት ጋዝ እንዲመርዙት ማድረጉን፣ በዝቋላ ተራራና ግርጌ አየር ኃይል የጭካኔ ሥራ እንዲሠራ ማዘዙን በሪፖርት ገልጿል። እንደዚሁም አዝማሪዎች፣ ቃሊቾች፣ ሺካዎች፣ ሰባኪዎች፣ ደብተሮች እየተያዙ በጥይት እንዲደበደቡ ትዕዛዝ መስጠቱን አረጋግጦአል። ሞሶሊኒ በፕሮቶኮል መዝገብ ቁጥር 19960 በጻፈው ደብዳቤ "…በተናጋሪዎችና በሰባኪዎች ላይ የተደረገው የሞት ፍርድ መፈፀም የሚገባው ነው…" ሲል አሠራሩን አጽድቆታል። የደብረ ሊባኖስን መነኮሳት ትንሽ፣ ትልቅ፣ ሴት፣ ወንድ ሳይባል ከገዳሙ መሪ ጭምር በጥይት እንዲደበድቧቸው አዞአል።

የሞሶሊኒን አመራር፣ የባዶሊዮን የጦር ሥልት፣ የግራዚያኒን የአስተዳደር ሥርዓት በፊርማቸው ከአስተላለፉአቸው ጽሑፎች ተመልክተናል። ሁሉም የበቀልና የጭካኔ ናቸው። ይህንን በአንድ ወይም በሌላ አመለካከት ማደብዘዝ ወይም ማጋነን አያስፈልግም። ማተኮር የሚያስፈልገው ዓላማቸው ምን ነበር ከሚለው ጥያቄ ላይ ነው። ዓላማቸውን ሁሉም ገልጸዋል። በእኔ አመለካከት በተሻለ ሁኔታ የገለጸው ጄነራል ግራዚያኒ ነው። እሱም "…የሲቪል ሠራተኛም ሆነ ወይም የጦር



አስተዳደር ሹማምንቶች አንዳችም ሰብአዊ ርኅራኄ ማድረግ የለባቸውም። እኛ በፊታችን ልናገኘው የሚገባን አንድ መነሻ ብቻ ነው። ይኸውም የኢትዮጵያን ግዛት በእጃችን ልንጨብጠውና ልንመራው የተነሳንበትን ብቻ ነው" አለ። እነሱ ይመሩበት የነበረው ትክክለኛው ነገር ይህ ነው። እናሠለጥናለን የተባለው ሃሰት ነው።[6] ለወደፊቱም ቢሆን ይህን ነጥብ መሳት፣ ትልቅ መሳሳት ነው።

## ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦርነት*፣ ገጽ 225።
2. ሞገስ ክፍሌ፣ *የሙሶሊኒ ምሥጢር*፣ ገጽ 145።
3. ፀሐፊው ራሱ የሚያውቀው።
4. *ገሪማ ታፈረ*፣ *ጐንደሬ በጋሻው*፣ ገጽ 38 እና 176።
5. ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ 1ኛ መጽሐፍ*፣ ገጽ 213።
6. ሞገስ ክፍሌ፣ ገጽ 71-134።

# ምዕራፍ አርባ ሶስት
# የእሥረኞችና የእሥር ቤቶች ሁኔታ

ኢትዮጵያውያን ከጣልያኖች እጅ ከተቀበሉአቸው የግፍ ሥራዎች አንዱ እሥራት ነው። እሱንም ለይቶ መመልከት ትምህርት ይገኝበታል። ስለዚህ ዋና ዋናውን ከዚህ እንደሚከተለው እንቃኛለን።

የእሥራቱ ሥርዓት እንደሌሎቹ የጣልያን ሥርዓቶች ሁሉ ግፍ የሞላበት ነበር። ምን ያህል ሰው እንደታሠረ ቁጥሩ በትክክል አልታወቀም። ብዙ አይደሉም እንጂ፣ ታሥረው የተፈቱም አሉ። የአንድና የሁለት ወር እሥራት እንደ አመክሮ ቢቆጠር ቅር አያሰኝም። ሦስት ወርና ከዚያ በላይ የታሠረው ግን ሁኔታው ሊጤንለት ይገባል። ስለዚህ ከሦስት ወር በላይ የቆየው እሥረኛ ብዛት ከ50,000 እስከ 60,000 እንደሚደርስ ቢገመት እምብዛም ስህተት አይሆንም።በእሥር ቤት የሞቱት ሰዎች ብዛት 3,500 እንደሆነ ተመዝግቦአል።[1]

ጉዳዩ (ዋናው ነጥብ) ያለው ከእሥር ቤቶቹ ሁኔታና ከአስተሳሰሩ ሥርዓት ጭምር እንጂ፣ ከእሥረኛው ብዛት ብቻ አይደለም። ኢትዮጵያውያን የታሠሩት ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻም አልነበረም። ጣልያን በዚያን ጊዜ ትገዛቸው በነበሩ አገሮች፦ በሶማልያ፣ በኤርትራ፣ በጣልያን ጭምር ብዙ ኢትዮጵያውያን ታሥረዋል። ቢሆንም አብዛኞች የታሠሩት ኢትዮጵያ ውስጥ ነው።

በዋና ከተሞች ሁሉ እሥር ቤቶች ነበሩ። የአዲስ አበባው፣ አፍንጮ በር ባሻገር የነበረው ዘብጠያ፣ ዋናው ነበር። በወቅቱ በተለይ ጐንደር፣ ደብረ ታቦር፣ መተማ፣ አሥመራ፣ ለጐሐይቅ፣ ደሴ፣ ደብረ ብርሃን፣ አዲስ ዓለም፣ ሐረር፣ ድሬዳዋና ጂማ የነበሩት በጣም ሥራ በዝቶባቸው ነበር። በተለይ በገጠር እስር ቤቶች የሚካሄደው ግፍ በከተማ እሥር ቤቶች ከሚካሄደውም የባሰ ነበር። በገጠር፣ በከተማና በውጭ ሐገር እስር ቤቶች ከተፈጸሙት የግፍ ሥራዎች፣ አንዳንዶቹን ከዚህ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

ጐንደር፣ ጠገዴ አቶ መብራቱ ወንዲያ የተባለ ሰው እግሩን ወደላይ ራሱን ወደታች ተደርጐ ተዘቅዝቆ ታሥሮ አደረ። ጥዋት ሲወጣ ከጓደኛው ጋር ሲነጋገር ስለታየ፤ ምሥጢር አወጣ በሚል ጥርጣሬ በጥይት ተገድሎ በእሳት ተቃጠለ። ቀኛዝማች ዘለቀ ደስታ በጅራፍ እንደተገረፉ ቀኑ መሽቶ፣ እንደተገረፉ ሌሊቱ ነጋ። አቶ ሽርብ ተኮላ በድብደባ ሞተ። አቶ ወልደ ገፊን ሽፍታ አሳድረሃል በሚል ምክንያት አሥራ ሁለት ራሱን እጅና እግራቸውን በሰንሰለት ታሥረው በእሳት ተቃጠሉ። ምርመራ የሚካሄደው በዱላ ነው። በድብደባ የሞተው ሰው እጅግ ብዙ ነው። ሥቃዩ እጅግ መራር ስለሆነ ላልሞተው ስሜቱ ለዕድሜ ልክ የማይረሳ ነው።



ጣልያኖች የምርመራ ወጥመዳቸው የተዘረጋው በሥጋ ላይ ብቻ አልነበረም። ምስክር አቁሞ ከነፍስ አባቱ ፊት ተናዘዝ ይለዋል። የነፍሱን ጉዳይ አስቦ እውነቱን ይናገራል። በዚያው አምኖአል ተብሎ ይገለጻል። ለእሱ ታማኝ የሆኑትን ቄሶች አቅርቦ እሥረኞቹን እንዲያናዝዙ ያዛቸዋል። እነሱም "...ሳትናዘዙ ብትሞቱ ኃጢአት ነው። ብትናዘዙ ግን የኢጣልያ መንግሥት መሐሪ ነው ይምራችኋል።..." እያለ ይቀለምዳል። ቢቻል ለመማር፣ ካልሆነም ለመጽደቅ እውነቱን ይናገራሉ። ሃሰትም ቢሆን የተጠየቀውን የሚነግር ሲኖር ይችላል። እውነትና ሀሰት በጣልያኖች ዘንድ ልዩነት የለውም። የሁሉም ፍጻሜው ያው ሞት ነው። በደብረ ታቦር ወህኒ ቤት በየቀኑ ከአሥር ያላነሰ ሰው ይገደል ነበር።

የአንዱ እሥር ቤት ሁኔታ ስለሌሎችም እሥር ቤቶች ሀሳብ ይሰጣል። የጐንደር እሥር ቤት ዙሪያውን በሽክ የታጠረ ነበር። ቤቱ ግድግዳ እንጂ ጣራ አልነበረውም፤መውጫ መግቢያ ደጃፍ የለውም። እሥረኛ ከለበሰው ኮትና ሱሪ በስተቀር ሌላ የለውም። ዝናም ሲዘንም እሥረኛው እርስ በርሱ ይጠጋጋል። ፀሐይም ሲበረታ እንደዚሁ መጠጋጋትና የበረታው ለደከመው ከለላ መሆን ነው። ሰው በብዛት ይሞታል። ሬሣውን እሥረኞቹ በአጥር አዘልለው ይጥሉታል። ሬሣ አንሺዎች ወዲያው ያነሱታል። በዚህ እሥር ቤት የታሠረው ከጐጃምና ከጐንደር የተሰበሰበ ነበር። ከሥቃዩ ብዛት የተነሣ ግደሉን እያለ ይጮሀል።

ጣልያን ለሥቃዩ ተጨማሪ እንዲሆን በዚሁ ዓይነት እንግልት እንዲሞቱ ያደርጋል። ጐንደር፣ ቁስቋም ዛኒ ገደል ላይ የነበረው እሥር የበለጠ አስቸጋሪ ነበር። ከዚህ ሁሉ ችግር አንዳንድ እሥረኞች አጥሩን በመዝለል ያመልጡ ነበር። ጣልያኖች እሥረኞች ምሕረት እንዳያገኙ በሚሰጡት አጣዳፊ ትዕዛዝ በስም መሳሳት የተገደሉም አሉ። ለምሣሌ ጐንደር ከተማ በአልታወቀ ቦታ በሥውር የታሠሩ አለቃ ወልደቂርቆስ መርሻ የተባሉ ሰው ምሕረት ቢደረግላቸው፤ ትዕዛዙ ከመድረሱ በፊት በተወሰደው አስቸኳይ እርምጃ በእሳቸው ፈንታ አለቃ ማርቆስ የተባሉ ጐጃሜ ተገደሉ። በራሳቸው ሥራ ጥፋት ሳይገኝባቸው ልጅህ፣ ወንድምህ በመንግሥት ላይ አምጾአል በመባል በጣልያን እየታሠሩ የተንገላቱ እጅግ ብዙ ናቸው። የተገደሉም አሉ።[2]

በአዲስ አበባ ከየካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም ግርግርና አረመኔያዊ ጭፍጨፋ በኋላ፤ ጣልያኖች ከሞት የተረፈውን ሰው እየሰበሰቡ በፈረስ ቤት፣ በአቃቂና ከደጃዝማች ውቤ ሠፈር ከነበረው እሥር ቤት አጎሩት። ራስ ደስታና ደጃዝማች በየነ መርድ ሲሞቱ ከጉራጌ አገር የተማረከውን፤ ራስ እምሩ ኃይለሥላሴ እጅ ሲሠጡ ጐጀብ እጅ የሰጠውን ጨመሩበት። እንደ አለቃ ዓለሙ ያለ የከተማ ቀልደኛ ሳይቀር ሰበሰበ። ጠንቋዩን፣ ሰባኪውን፣ ቃልቻውን፣ ባሕታዊውን፣ ካህናቱን አከሉበት። እንደዚህ አድርገው ከሰበሰቡት እሥረኛ ከፊሉን ወደ ሞቃዲሾ፣ ከፊሉን ወደ ኤርትራ፣ ከፊሉን ወደ ኢጣልያ

ወሰዱት። የእያንዳንዱን እሥረኞች ቡድን ሁኔታ ማየት አጠቃላይ ግንዛቤ ሊሰጥ ይችላል።

ወደሞቃድሾ የተወሰደው ቡድን መጋቢት 12 ቀን 1929 ዓ.ም ከየቦታው ተሰብስቦ ነፋስ ሥልክ ተከማች። በማግስቱ መጋቢት 13 ቀን 120 ካሚዮን አቅርበው በአርባ በአርባ እየቆጠሩ አሳፈሩት። በጠቅላላው ከ4,800 እስከ 5,000 እሥረኛ መሆኑ ነው። ወንድና ሴት፣ ልጅና አዋቂ፣ ሕመምተኛና ሽማግሌ አልተመረጠም። ጠባቂ ዘበኞች አብረው ተሳፍረው ጉዞው ቀጠለ። መንገዱ ከአዲስ አበባ ድሬዳዋ፣ ከዚያ ሐረር። ከሐረር በጅጅጋ፣ በቀበሪ ደሐር፣ በሞያሌ በኩል አልፎ ሞቃድሾ መግባት ነው። በመንገድ ላይ የነበረው አበሳ እጅግ ከባድ ነበር። ልጁዋ በክንድዋ ላይ ሙቶ የቀኑ ጉዞው እስኪያበቃ ድረስ ሬሣ ታቅፋ የተጓዘች ሴት ነበረች። በየመንገዱ ያለቀው ሰው ብዙ ነው። እሥረኛ በዚህ ዓይነት ተጉዞ ሚያዝያ 30 ቀን 1929 ዓ.ም ደረሰ።

በዚያ የነበረው ቆይታ ደግሞ በመንገድ ላይ ከታየው አበሳ የበረታ ሆነ። ሀገሩ ቆላማ ከመሆኑ ጋር ከህንድ ውቅያኖስ ባህር ጠርዝ ላይ ስለሆነ፤ እርጥበት የቀላቀለ ከባድ ሙቀት አለው። እንደ መቀቀል ያለ ሆነ። እንጨት ሰብሮ፣ ውሃ ቀድቶ ተሸክሞ ማምጣት፤ በሐሩር ፀሐይ ቂጣ ጠፍጥፎ መብላት ትንሽና ትልቅ አላለም። በዚህ ላይ ደግሞ በየምክንያቱ በሱማሌ ዘበኛ መረገጥ መደብደብ አለ። ከአንድ ዓመት በኋላ ደግሞ የትኩሣትና የተስቦ፣ የተቅማጥ በሽታ ገብቶ በአራት ወር ውስጥ 1,000 ሰው ገደለ። መግደል ብቻ ሳይቀር እያቃዠ፣ እያስከዳ አሰቃየው።

ከአንድ ዓመት ተኩል ቆይታ በኋላ ጣልያኖች አዲስ ፈሊጥ አመጡ። ለአንድ ሰው ለመተኛ አንድ ሰሌን፣ ለመብሊያ አንድ ሣህን፣ ለውሃ መጠጫ አንድ ኩባያ መስጠታቸውና የበቆሎ ዱቄት ለቀለብ በነፃ መሥፈራቸው ቆጫቸው። እሥረኛው ሠርቶ ይብላ አሉ። እሥረኞቹ ጀናሌ ወደሚባለው አንድ መቶ አሥራ ሰባት የእርሻ ሁዳድ /ኮንሴሲዮን/ ወደ አለበት ቦታ ተወሰዱ። ለእያንዳንዱ ሁዳድ እንደፍላጎቱ አርባም አምሳም ሰው ተደለደለለት። ሥራው በዶማ መቆፈር ሙዝ መትከል ነው። በኮንትራት የተሰጠውን ሥራ ከጨረሰ ጥቂት ገንዘብ ስለሚሰጠው ራቱን ይበላል። ያለዚያ ጦሙን ያድራል።[3]

በዚህ ዓይነት መከራቸውን ከአዩ በኋላ፤ የሞተው ሞቶ የተረፉት እሥረኞች ተለቀቁ። የተለቀቁትም ጣልያን ከአርበኞች ጋር ለመታረቅ ድርድር በጀመረ ጊዜ፤ ከአርበኞች ወገን ከቀረቡለት ጥያቄዎች አንዱ እሥረኞች እንዲለቀቁ የሚል ስለነሆነበት ነበር። በዚህ ምክንያት በ1932 ዓ.ም ስለፈታቸው ተመልሰው አገራቸው ገቡ።

ሁለተኛው በርካታ ቡድን የተላከው ወደ ኤርትራ ነበር። በኤርትራ የታሠሩት ናኩሩ፣ ናቅፋ ነበር። የተወሰዱት በየጊዜው ከየቦታው ስለነበር



ቁጥራቸው በትክክል አልታወቀም። እስከ አንድ ሺህ ሳይደርሱ አልቀሩም። ሆኖም እዚህም ሥፍራ እሥራቱ ችግርና መከራ የሞላበት ነበር። እንግሊዞች ሀገሩን ከያዙ በኋላ ልዑል መኰንን ኃይለሥላሴ ከንጉሠ ነገሥቱ ታዝዘው በየእሥር ቤቱ እየዞሩ በመርመር፤ ኢትዮጵያውያንንም ኤርትራውያንንም በብዛት እንዳስፈቱ በ1949 ዓ.ም ልዑልነታቸው በሞቱ ጊዜ አብረው የተፈቱ ኤርትራውያን እያዘኑና እያለቀሱ ነግረውኛል።

ሌላው የእሥረኛ ቡድን የተወሰደው ወደ ጣልያን ሀገር ነው። ወደዚያ የተወሰዱት እንደነራስ እምሩ፣ ራስ ኃይሉና ራስ ሥዩም ያሉ መሣፍንት፤ እንደነልጅ ይልማ ዴሬሣና አቶ ሐዲስ ዓለማየሁ ያሉ የተማሩ ወጣቶች፤ እንደነልዕልት ሮማነ ወርቅ ኃይለሥላሴ የመሳሰሉ ንጉሣውያን ቤተሰቦችና እንደነዘርዓይ ደረስና ሻምበል አብዲሣ አጋ የመሳሰሉ የጦር ሰዎች ነበሩ። የታሠሩትም አዚናራ፣ ፖንዛ፣ ሊፓሪ፣ ሎንጉቡክ፣ በመሳሰሉት ቦታዎች ነበር። አንዳንዶችም ሮም ቆይተዋል። እሥራቱም በሌሎች ቦታዎች የታየውን ያህል የሚያሰቃይ አልነበረም።[4]

ችግሩ መገደሉ መታሠሩ ብቻ አልነበረም። ሥርዓታቸው ቅጥ ያጣ መሆኑ ጭምር እንጂ። አንዳንድ ሁኔታዎችን ለማስረጃ እንጠቅሳለን። ጐንደር አቶ ንጋቱ ረታ የተባለ ሰው ልብስህ ለምን አደፈ ተብሎ በጥይት ተደብድቦ ሞተ። ሌላ ልብስ አለኝም ለማጠብም አልተመቸኝም ማለቱ አላዳነውም። ሌላው ዘለቀ ኃይሉ የተባለ ቆፍጣና ወጣት ደግሞ ያማረበት መስሎት ነጭ ሱሪ ታጥቆ፣ ነጭ እጀ ጠባብ አጥልቆ፣ ነጭ ኩታ ለብሶ ከተማ ቢወጣ ተደበደበ። እሱ በጫማ፣ ልብሱም ከጭቃ ጋር ተረጋገጠ።[5]

በኅዳር ወር 1933 ዓ.ም ቡልጋ መገዘዝ፣ ጌራ በተደረገው ጦርነት፤ ገብረፃድቅ ደመና የተባለ የ14 ዓመት አርበኛ ተማረከ። ዕድሜው 14 ወይም 15 ዓመት ቢሆነው ነው። በምርመራ አሳብበው በድብደባ ብቻ ገደሉት።[6]

ጣልያኖች የፈጸሙትን የግፍ ሥራ የሚያጣራ አንድ ኮሚሽን አዲስ አበባ ላይ ተቋቋመ። ለዚህ ኮሚሽን ቃል ከሰጡት ሰዎች አንዱ ብላታ በቀለ ሀብተሚካኤል፤ ደናኔ እሥር ቤት በነበሩ ጊዜ የሚሰጣቸው ምግብ ብዙ ትላትሎች የሚታዩበት ደረቅ ቂጣና ሻይ እንደነበር፤ በምግብ ብላሽነት ምክንያት በየቀኑ አራትና አምስት ሰው ይሞት እንደነበር አስረድተዋል። ሌላው ምስክር አቶ ሚካኤል ተሰማ ደግሞ የሚሰጣቸው ደረቅ ጋሌጣ እንደነበርና በውሃ ጥም ምክንያት የጨው ውሃ መጠጣት ግድ ስለነበረ፤ በጠቅላላው ከ6,500 እሥረኞች ውስጥ 3,175 ሰው ማለቁን አስረድተዋል። ከዚህ በስተቀር በሥራ ቦታ ድካም የሚያሳዩ ሰዎች፤ እጆቻቸውን የኋሊት እየታሠሩ እስከ ሰባት ቀን ከቤት ጣሪያ ላይ ይንጠለጠሉ እንደነበር አመልክተዋል።[7]

በአጠቃላይ ሲታይ ኢትዮጵያውያንና ጣልያናውያን ተጻራሪ ባሕርያት አሉአቸው። ኢትዮጵያዊ ዱተኛ፣ ጣልያናዊ ችኩል ነው። በኢትዮጵያውያን

ዘንድ ጭምትነት፣ በጣልያናውያን ልፍለፋ ያበዛል። ኢትዮጵያዊ ትዕግስተኛ ሲሆን፣ ጣልያናዊ ቁጡ ነው። እነዚህ ሁኔታዎች በሁሉም ኢትዮጵያውያንና በሁሉም ጣልያናውያን ላይ ሁልጊዜ ባይታዩም፣ በአብዛኛው ሁኔታው እንደዛ ነው። ሁለቱ ወገኖች በተጋጠሙ ጊዜ፣ እነዚህ ተጻራሪ ስሜቶች፣ ባሕርያት ሳይከሰቱ አልቀሩም። ያም ቢሆን ግን ለጣልያኖች ጭካኔ በቂ ምክንያት አይገኝለትም።

<u>ማጣቀሻ ፅሑፎች</u>


1. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 225።
2. *ገሪማ ታፈረ*፣ *ጐንደሬ በጋሻው*፣ ገጽ 28-35፣ 153-172 208-211።
3. ተክለ ጻድቅ *መኩሪያ*፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ*፣ ገጽ 279-284።
4. ሐዲስ ዓለማየሁ፣ *ትዝታ*፣ ገጽ 204-252።
5. *ገሪማ ታፈረ*፣ ገጽ 29 እና 211።
6. እኔ ራሴ የማውቀው።
7. ጳውሎስ ኞኞ፣ ገጽ 159-160።




# ምዕራፍ አርባ አራት
# የድርጅት ጥያቄ በአርበኞች ዘንድ

ኢትዮጵያውያን ከአለባቸው ችግር፣ በድርጅት ተባብሮ *መሥራት* ነው። ሁሉም የወደደውን *ሥራ* በወደደው ዓይነት፣ ለእሱ ባሰኘው ጊዜና ቦታ *መሥራት ይፈልጋል*። የቻለውን ሠርቶ ለራሱ ስም ማውጣት፣ ክብር ማግኘት ይፈልጋል። ለድርጅት ደንታ የለውም። ሕግ የሚያከብረው፣ *ሥርዓት* የሚጠብቀው፣ ትክክል መስሎ እስከታየውና መብቱ እስከ ተከበረለት ድረስ ነው። ማዘዝ እንጂ መታዘዝ አይወድም። የበላይ እንጂ የበታች መሆንን አይቀበልም። በዚህ ውስጣዊ ባሕርይ የተነሣ፣ በሕግ ሳይሆን ለሰው ሲገዛ ይኖራል።

ለሰው የሚገዛው ደግሞ ለማንም አይደለም፤ እሱ ለወደደው ነው። ሰውን የሚወድና የሚጠላባቸው *መሥፈርቶች* አሉት። ከቦታ ቦታ ቢለያዩም *መሥፈርቶቹ* አንድ ዓይነት ናቸው። አንድ ሰው በኢትዮጵያውያን ዘንድ ክብርና ሞገስ ለማግኘት በኃይማኖቱ ጽኑዕ መሆን አለበት። ብርቱና ጀግና መሆን ያስፈልጋል። ቸር፣ ትሁት፣ ሰው አክባሪ፣ ሕግ አዋቂ፣ *ሥነ ሥርዓት* አጥባቂ መሆን አለበት። እውነተኛና ትዕግስተኛ መሆን ያስፈልገዋል። እነዚህን ያምዋላ፣ የቅርብ የሕዝብ አመኔታ ያገኛል። በአንጻሩ ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚጠላና የሚጠየፋቸው ነገሮች፣ ከዚህ በላይ ከተገለጹት ባሕርያት ውጭ የሆኑትን ነው። በኃይማኖት ጽንአት የሌለው ሰው ለምንም ጉዳይ አይታመንም። ፍቅረንዋይ የተጠናወተው ሰው እምነት አይጣልበትም። ትዕቢተኛ፣ እብሪተኛ አይወደድም። ፈሪ አይከበርም። ችኩልና ቆጭባራ፣ ቁጡ፣ ለመሪነት አይመረጥም። የጭዋና የባለጌ መለያ *መሥፈርቶች* እነዚህ ናቸው። መልክና ሙስና (ማለትም፡- የሚስብ ገፅታ) ተደራቢ ጸጋዎች ናቸው።

በአርበኝነት *ሥራ* ውስጥ በሰው አመራረጥ ረገድ እነዚህ *መሥፈርቶች* እውን ነበሩ። ከሌላው ተለይቶ ለአንዱ የሚያብረው፣ በአብዛኛው በእነዚህ መለኪያዎች መሠረት ነው። በግል ጠብ ወይም ግጭት ካልሆነ በስተቀር፤ በሌላ ምክንያት ከአለቃው አይለይም። አንዳንድ ነገረ ሠሪዎች በአካሄዱአቸው ተንኮሎች የተነሣ ካልሆነ በስተቀር፤ ከዚህ ውጭ በሆነ ምክንያት የተለያዩ አርበኞች አላየሁም።

ጣልያን ኢትዮጵያን በወረረች ጊዜ በንጉሠ ነገሥቱ ከሚመራው ማዕከላዊ መንግሥት በቀር ሌላ ምንም ጠንካራ፣ ሀገር አቀፍ ድርጅት አልነበረም። እሳቸው አገር ጥለው በሄዱ ጊዜ፣ ያው አንዱ ማዕከል ጠፋ። በየግል ጥረታቸው የሕዝብ አመኔታ አግኝተው የነበሩት ታላላቅ የጦር መሪዎች ቀደም ብሎ በተካሄደው የሥልጣን ሹኩቻ ረግፈው ስለነበር፣ አልተገኙም። አዲስ የተኮለኮሉት ሹማምንት ደግሞ የሕዝብ አክብሮት

ስለአልነበራቸው ለመሪነት ብቁ ሳይሆኑ ቀሩ። ስለዚህ አመራርን በተመለከተ ሀገር ባዶ ሆነች።

አርበኞች አዲስ መሪ ለማውጣት ተፍጨረጨሩ። የገጠሩ ሕዝብ ከንጉሥ በስተቀር የሚያውቀው ነገር የለም። የተማረው ወጣት በበኩሉ ድርጅት ማቋቋም ፈለገ። የቀዳማዊ ኃይለሥላሴም ወገኖች ሌላ መሪ እንዳይመጣ ውስጥ ውስጡን ነገር ማካሄድ ያዙ። ሁኔታው ፋታ የሚሰጥ አልሆነም። ጣልያን የነበረውን ባህላዊ አቅዋም በፍጥነት ማፈራረስ ያዘ። ሁሉም በየበኩሉ የሚሻል የመሰለውን አደረገ።

የቀድሞውን የፊውዳሉን ሀገር በአዲስ ሕዝባዊ አስተዳደር ለመተካት በማሰብ፣ አቶ /ብላታ/ ታከለ ወልደሐዋርያት ሪፓብሊክ መንግሥት ለማቋቋም ሞከሩ። ነገር ግን ጉዳዩ በሀገሪቱ ላይ የጥፋት ጥላ በአንዣበበት ጊዜ ሊፈፀም የሚችል አልሆነም። በሀገር ውስጥም፣ በሱዳንና በኬንያ በነበሩ ስደተኞች ዘንድም ተደጋግሞ ቢሞከር፣ ውጤት ሳያስገኝ ቀረ። የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት መሞከር በሰላም ጊዜ እንጂ በጦርነት ጊዜ አይደለም። በጦርነት ጊዜ የሚሻለው፣ ቀድሞ በነባሩና ሕዝብ በለመደው ሥርዓት መሥራት መሆኑ ታዬ።

ይህ ማለት የአቶ /ብላታ/ ታከለ አመለካከት ስህተት ነበር ማለት አይደለም። ጣልያን ኢትዮጵያን ለመውረር ምክንያት ያደረገችው "ኋላቀር ናት፤ ባሪያ ይሸጥባታል፤ ጭቆና ይካሄድበታል። እኔ ላሠለጥናት ይገባኛል" በሚል ምክንያት ነበር። በሀገር ውስጥ ጉዳይ ደግሞ በአማራውም ሆነ በተቀረው ክፍለ አገር የገባር፣ የጉልት፣ የጭሰኛ ሥርዓት ባለመሻሻሉ ችግር ነበር። ከዚህም በስተቀር በንግሥ ምክንያት በሸዋ፣ በጐንደር፣ በትግሬ መሣፍንት መካከል የነበረው የግለሰብና የቡድን ትንንቅ ሳይቀዘቀዝ፤ የጐጃምና የወሎ ተጨምሮ በየጊዜው ጠብ እየተቀሰቀሰ ያስከተለው ጠንቅ ሕዝቡን አስቸግሮት ነበር። በደቡብ ደግሞ የነፍጠኛው ሥርዓት ሠፍኖ አፍላ ደረጃ ላይ ደርሶአል። የባሪያ ሽያጭና የዛው ንግድ ሥራ በወረቀት ደረጃ እንደቀረ ቢቆጠርም፣ በሕይወት ውስጥ ገና ሕያው ነበር። በቤተክህነትና በቤተመንግሥት መካከል የነበረው ትሥሥር በመላላት ፈንታ ጠበቀ። የአድባራት አለቆች የሚሾሙት በንጉሠ ነገሥቱ ሆነ።

የሪፐብሊክ መንግሥት አቋቋም እነዚህን ሁኔታዎች መለወጥ ታላቅ ጠቀሜታ ነበረው። በአንድ በኩል የአውሮፓ አገሮች ስለኢትዮጵያ የነበራቸውን ዝቅተኛ አመለካከት ለውጦ በአዲስ አመለካከት ለመተካት ያስችላል። በሌላ በኩል በሀገር ውስጥ የነበረውን ጠንካራ ባሕላዊ አገዛዝ ያስወግዳል። እንዲሁም ከአዲሱ ሥልጣኔ ጋር ተጣምሮ በማቆጥቆጥ ላይ ያለውን ብዝበዛ በእንጭጩ ይቀጫል። ባርነትንና ጭቆናንና ያስቀራል። ንጉሠ ነገሥቱን በሀገር ክህደት ተጠያቂ አድርጐ ዘውድን ይገረስሳል። በዘውድ ሽሚያ ምክንያት በሚቀሰቀሱ ጦርነቶች የሚያልቀውን ሕዝብ ያድናል።



ከጣልያን ጋር በመዋጋት ለሀገር የመከላከሉ ጉዳይ የአማራው ብቻ መሆኑ ቀርቶ የጠቅላላው ሕዝብ እንዲሆን ያደርገዋል። የአቶ /ብላታ/ ታከለ ወልደሐዋርያት ሃሳብ ለብዙ ጊዜ ሲያነጋግር፣ ሲያመካክር የቆየው በዚህ ሁሉ ምክንያት ነበር። ግን በወቅቱ ሊፈፀም አልቻለም።

አርበኛው በነሐሴ ወር 1928 ዓ.ም አምቦ አካባቢ ባደረገው ስብሰባ ከውስጡ መሪዎችን መረጠ። ባላምባራስ /ራስ/ አበበ አረጋይን ጠቅላይ የጦር አዛዥ አደረገ። ግራዝማች /ደጃዝማች/ ዘውዴ አስፋውና መቶ አለቃ /ጄነራል/፣ ኢሣያስ ገብረሥላሴ ደግሞ ሕዝብ አስተባባሪ ሆኑ። አቶ /ብላታ/ ታከለ ወልደሐዋርያት የጸሐፊነቱን ሥራ በደስታ ተቀበሉ። የምክር ቤት አባላትም አብረው ተመረጡ። በዚህ ውስጥ ደግሞ መቶ አለቃ /ጄነራል/ ዓብይ አበበና መቶ አለቃ /ጄነራል/ መርዕድ መንገሻ ነበሩበት።[1] ይህኛውም ድርጅት ውጤት አልሰጠም።

የድርጅትን አስፈላጊነት በወቅቱ የተረዱት ሌሎቹ ሰዎች፣ የሆለታ ጦር ትምሕርት ቤት ምሩቃን ነበሩ። ከሆለታ የጦር ትምህርት ቤት የተንቀሳቀሱት በሌተና ኮሎኔል ክፍሌ ነሲቡ መሪነት ነበር። ኮሎኔሉም በፈረንሣይ አገር የጦር ትምህርት የተማሩ ስለነበሩ፤ ወጣቶቹ መኮንኖች እምነት ጣሉባቸው። እሳቸውም በጦር ትምህርት ቤቱ ኃላፊነት ላይ የነበሩ መኮንኖች በዚያው ሥራቸው እንዲቀጥሉ በማድረግ፤ ጦሩን መርተው ለቀምት አገቡት። ከዚያም በየጊዜው ስብሰባ እየተደረገ ይመከር ነበርና አንድ ምክር ቤት ተመርጦ ተሰየመ። የጦሩም ስያሜ ጥቁር አንበሳ ተባለ። ሰኔ 29 ቀን 1928 ዓ.ም በተደረገው ስብሰባ የጥቁር አንበሳ አርማና መተዳደሪያ ሕግ ወጣ። ድንጋጌው ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴና ከወራሾቻቸው ሌላ ላለማወቅ ወሰነ። ዶክተር ዓለመወርቅ በየነ የአርማው ፕሬዝዳንት ሆኑ። ሌሎች ሃያ ሰባት የምክር ቤት አባላትም አብረው ተመረጡ። ለጦር አሠልጣኝነት ደግሞ ሌሎች አሥራ ዘጠኝ ተመረጡ። የሥልጠናው ሥራ የበላይ አለቃ በላይ ኃይለአብ ሆኑ።[2] ይህ ጦር በዚህ ዓርማ ሥር ጸንቶ ቆየ። ጐጀብ እጁን እስከሰጠበት ቀን ድረስ በጥንካሬ ለሀገር ተከላከለ።

ራስ እምሩ ከሰሜን ጦር ግንባር ተመልሰው ጐንደር እንደገቡ፣ ጀግኖች ጥቂት በጥቂት እያሉ አበሩላቸው። ከጐጃምም መጠነኛ ሰው ተከተላቸው። የወለጋና የኢሉባቡር ሰራዊት አበረላቸው። ጐሬ በገቡ ጊዜ በቂ ድርጅት ነበራቸው። ንጉሠ ነገሥቱ የእንደራሴነቱን ሥልጣን ሰጡአቸው። ራስ እምሩም መደበኛውን ሠራዊታቸውን በአንድ ወገን፤ የጥቁር አንበሳን ጦር በአንድ ወገን በመምራት፤ ተከትለዋቸው የነበረውን ሰላማዊ ሕዝብ ለማዳን ሲሉ በታህሣሥ ወር 1929 ዓ.ም ጐጀብ ላይ እጃቸውን እስከ ሰጡበት ጊዜ ድረስ በታላቅ ችሎታ አመራር ሰጡ።

ሌላው ድርጅታዊ እንቅስቃሴ የተካሄደው በቡልጋ ነው። በወቅቱ ከተደረጉት ሙከራዎች ሁሉ የተሻለ ውጤት ያስገኘው እሱ ስለሆነ በቀረቤታ

መመልከት ይገባል። በቡልጋ ውስጥ አርበኞች እርስ በርሳቸው በመመራረጥ የመጣውን ጠላት በመከላከል ንጉሠ ነገሥቱን ለመጠባበቅ ሞከሩ። የበረከቱን ፊታውራሪ ኃይለሥላሴን መረጡ። በእሳቸው መሪነት በወና፣ በእመየት ሀገር፣ በበረከት ታላላቅ ጦርነቶች ከአካሄዱ በኋላ፤ እሳቸው ጥር 2 ቀን 1929 ዓ.ም ከጠላት እጅ ወደቁ። መጀመሪያ ወደ ደብረ ብርሃን፣ ከዚያም ወደ አንኮበር በከፍተኛ መንገላታት ከተወሰዱ በኋላ፣ ጥር 10 ቀን 1929 ዓ.ም ከጦር ጓደኞቻቸው ከእነባላምባራስ ይልማ ወልደኢየሱስ ጋር በጠላት እጀ ተገደሉ። ጦሩም ተበተነ። በዚህ ጊዜ አለቃ ወልደፃድቅ ዘውዴ ብቻ ከሁለት ወታደሮቻቸው ከአቶ /ቀኛዝማች/ ገብረመስቀል ኃይሌና ከአቶ ጨፍቂ ይገዙ ጋር ቀሩ። አሽከራቸው እንድሪስና አቶ ዘለቀ ወልደ ጻድቅም አብሮ ነበር። ጨፍቄም ከድቶ ለጣልያን ገባ።

አለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴ ከጥር 2 እስከ ሰኔ 30 ቀን 1929 ዓ.ም ያለውን ጊዜ ሦስት ራሳቸውን ሲታገሉ ከቆዩ በኋላ፤ ክረምቱ ሲገባ ጓደኞቻቸውን አሰባሰቡ። እነ /ቀኛዝማች/ ስንቅነህ፣ እነ ግራዝማች /ፊታውራሪ/ አጕናፍር ባዩ አበሩላቸው። ሐምሌ 21 ቀን 1929 ዓ.ም ጭቃ ቆላ የተደረገውን ጦርነት መርተው ድል አገኙ። በዛ ውጊያ ከስድስት መቶ በላይ ደረቅ ብረት ተማረከ። በርካታ ሠራዊት አበረላቸው። ከመኪና መንገድ በስተምሥራቅ ያለውን አገር ሕዝብ አስተባበሩ።

ይህ ድል በጠላት ፊት ብዙም እንደማይቆይ ቀደም ብሎ በእነ ፊታውራሪ ኃይለሥላሴ ላይ በደረሰው ሁኔታ ታይቶ ነበርና፤ በተገኘው ድል ከመኩራራት ይልቅ አንድ ድርጅት ማቋቋም እንደሚሻል ታወቀ። በአርበኛው መሪዎች መካከል በረከት አካባቢ ልዩ ልዩ ስብሰባዎች ተካሄዱ። መስከረም ሲጠባ ጣልያን በአዲስ ኃይል እንደሚመጣ የታወቀ ነው። ይህ ከሆነ የገበሬው ተሳትፎ ይቀንሳል፤ ሠራዊቱም ለጥቃት ይጋለጣል። ከአርበኛው መካከል አንዱን መሪ ማድረግ፣ አድናቂ እንጂ ደጋፊ አላስገኘም። ንጉሠ ነገሥቱ ዕርዳታ ይዘው ይመጣሉ የሚለው ተስፋ ከአንድ ዓመት ከሦስት ወር ትግል በኋላ እየሻከረ ሄደ። አንድ ሕዝብ የሚከተለው መሪ ማውጣት ግድ ሆነ።

ነሐሴ 20 ቀን 1929 ዓ.ም ቅዳሜ፣ ወክፊሌ በተደረገ የአርበኛ መሪዎች ጉባዔ ላይ ይህ ጉዳይ ለንግግር ቀረበ።

አለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴ አዲስ ሃሳብ አቀረቡ። እሱም "የልጅ ኢያሱን ልጅ እናንግስ" የሚል ነበር። እጅግ አከራከረ። የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ደጋፊዎች ተቃወሙ። በንጉሥ ላይ ንጉሥ እንዴት ይሆናል አሉ። በጭንቅ ጊዜ አገር ጥሎ ለሄደ ንጉሥ መከራከር የሚያስከብራቸው አልሆነም። ሌላ ንጉሥ መንገሡ ሲሰማ፣ ጣልያን ሊያጠፋን ይነሳል ያሉም ነበሩ። መልሱ አሁን ምን እያደረገን ነው? ሆነ። ክርክሩ ጠነነ። አለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴ "ንሱ ሰዎች፣ አንድ ሰው ስለሸሸ ሁላችን እናልቃለን?" አሉ። ይህቺ ጥያቄ ለተነሣው ክርክር መዝጊያ ሆነች።



ለአርበኝነትም፣ ለእሳቸው ለራሳቸው ሕይወትም ወሣኝ ሆነች። ክርክሩ አከተመ። አርበኛው በሃሳቡ ተስማማ።

አለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃደቅ ዘውዴ ይህንን ሃሳብ ያቀረቡት፤ እንግዳ እሸት ኃይሌ በሚል ስም ይታወቅ የነበረውን የልጅ ኢያሱ ምኒልክን ልጅ በአብዬ ገዳም ከአባ ይርዳው እጅ ወስደው ስለነበር፣ ነጋሢውን የማግኘቱ ጉዳይ አላስቸገረም። ስለዚህ ወጣቱ እንግዳእሸት ነሐሴ 21 ቀን 1929 ዓ.ም መልአከ ፀሐይ ኢያሱ ምኒልክ ተብሎ ነገሠ።

ንጉሠ ነገሥት መልአከ ፀሐይ ኢያሱ ምኒልክ ከነሐሴ 21 ቀን 1929 ዓ.ም ጀምሮ በተከታታይ ሹመት ሰጡ። አለቃ ወልደ ፃደቅም ፊታውራሪ ተባሉ። ከተሰጡት ሹመቶች ታላቁ ለባላምባራስ አበበ ሚያዝያ ወር 1930 ዓ.ም ጀሉ አገረ ማርያም የተሰጠው ነበር። ምንም ንጉሡ መስከረም 27 ቀን 1931 ዓ.ም አንኮበር፣ ቆቦ ቢሞቱም፣ ሥራቸው ሕያው ሆነ።[3] የሾሙአቸው ሹማምንት የአቋቋሙት ሠራዊት ሃሳቡን ሳይለውጥ፣ ዓላማውን ሳያጥፍ እስከ መጨረሻው ተዋጋ። ኢትዮጵያንም በዓለም አሳወቃት፤ ለድል አበቃት።

ነገሩ ተሸፋፍኖ ይቅር እንጂ በጐንደርና በወሎም ልጅ ዮሐንስ ኢያሱ ምኒልክን ለማንገሥ ሙከራ እንደ ተደረገ አንዳንድ የታሪክ ማስረጃዎች አሉ። ሰኔ 8 ቀን 1930 ዓ.ም ላስታ፣ አብጣ ተክለሃይማኖት ተገናኝተው በልጅ ዮሐንስ አመራር ለመጠቃለል ተስማሙ። ስብሰባውን ያቀነባበሩት ደጃዝማች ገብሬ ነበሩ። ብላታ ታከለ ወልደሐዋርያትና ብላታ ደሬሣ ግብጽ አገር ዘውድ እስከ ማሠራት ደርሰዋል።[4] በመሥፍኑ ድንገተኛ ሞት ቀዘቀዘ እንጂ፣ በውጪ አገር በነበሩ ስደተኞችም መካከል የልጅ ግርማ ኢያሱ ሁኔታ ልዩነት መፍጠሩ አልቀረም።

የበጌምድር አርበኞች በየአሉበት ከመከሩ በኋላ አጠቃላይ ስብሰባ አደረጉ። በጠቅላላው ጉባዔ ላይ በሦስት ነጥቦች ላይ ስምምነት ተደረገ። ስምምነት የተደረገውም አንደኛ በመራራ ተጋድሎ ንጉሠ ነገሥቱን ለመጠበቅ ተስማሙ። ይህ አባባል በጉዳዩ የንጉሠ ነገሥቱ እጅ እንደነበረበት ያመለክታል። ሁለተኛው ነጥብ እርስበርስ ለመረዳዳት ተስማሙ። ሦስተኛው ጀግንነታቸውን በግብር ላረጋገጡ አርበኞች የማዕረግ ስም እንዲሰጥ ተደረገ። በዚሁ ስምምነት መሠረት ግራዝማች አሞራው ውብነህ ራስ ተብለው ጠቅላይ የጦር አዛዥ ሆኑ።[5] ይህ አካሄድ አርበኛውን ለጊዜው ያጠናከረው ቢሆንም፣ የተጠበቀውን ያህል ድርጅቱ ጽንአት አላገኘም።

ሕዝብ በበኩሉ ማኅበር እያቋቋመ ለሀገሩ ተከላከለ። በየቦታው የጐበዝ አለቃ እየመረጠ ተዘጋጀ። በጐጃም የዲማ ጊዮርጊስ፣ የደብረ ወርቅ ማርያም ማኅበር አቋቋመ። እንደዚሁም ጕታ፣ ገበርማ ከተባለ ሥፍራ ሕዝባዊ ማኅበር አቋቋመ። በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ወጣቶች የተስፋ ማኅበር የሚል ተቋቁሞ፣ ስደተኞችን የተቻለውን ያህል ረድቶአል።[6]

አብዛኞቹ የአርበኛ ቡድኖች በሠራዊቱ የሚመረጡ፣ ወይም ከኮር አለቆች የተውጣጡ የጦር ምክር ቤቶች ነበሩአቸው። በንጉሠ ነገሥት መልአከ ፀሐይ ኢያሱና በራስ እምሩ የሚመሩት ሠራዊቶች ጠንካራ ምክር ቤቶች ነበሩአቸው። ነገር ግን ምክር ቤቶቹ መልአከ ፀሐይን ከሞት፣ ራስ እምሩን እጅ ከመስጠት አላዳኑም። እስከ መጨረሻው ድረስ ሠራዊታቸውን በመምራት ለድል ከአበቁት ምክር ቤቶች አንዱ በበላይ ዘለቀ የተመራው የአርበኛ ምክር ቤት ነው።[7]

ከማኅበራት ሁሉ የተሻለ ውጤት ያስገኘው ጥቅምት 23 ቀን 1931 ዓ.ም ተጉለት፣ ሣሲት ላይ የተመሠረተው ማኅበር ነው። ውጤቱ የተሻለ መሆኑ ደግሞ አመሠራረቱ እንደምን እንደ ነበር እንድንመረምር ይጠይቀናል።

ንጉሠ ነገሥት መልአከ ፀሐይ ኢያሱ ምኒልክ መስከረም 27 ቀን 1931 ዓ.ም አርፈው በሸዋ አርበኞች መካከል መናጋት እንዳይደርስ አስግቶ ነበር። በንጉሡ ህልፈት የተፈጠረው ስሜት፣ በወቅቱ በቡልጋና በመንዝ እንደጋለ ቆየ። ጠላትም በዚህ አመች ሁኔታ ለመጠቀም፣ በዛ አካባቢ አርበኞችን ከምድር ገጽ ለማጥፋት ተንቀሳቅሶአል። ከዚህ ችግር ገለልተኛ የነበረውና ቀዝቃዛ ስሜት የነበረው በተጉለት አካባቢ ሆነ። ስለዚህ የአርበኛ መሪዎች በዚያ ተሰብስበው ስለወደፊቱ የትግል አቅጣጫ መከሩ፤ አዲስ ማኅበርም አቋቋሙ።

የማኅበሩ ዋነኛ ዓላማ በአርበኛው መካከል የመረዳዳትና የመተባበር፣ የመደጋገፍ ስሜት ማዳበር ሆነ። "ወገንህን ጠብቅ" በሚል ሃሳብ ላይ የተመሠረተ ነው። አንድ አርበኛ ሌላውን አርበኛ እንደ እናቱ ልጅ እንዲያየው፣ በአደጋ ጊዜ ጥሎት እንዳይሄድ፣ በሰልፍም ውስጥ ጥሎት እንዳይሸሽ አባላቱን ቃል ያስገባል። የማኅበሩ ስም "የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች ማኅበር" እንዲሆን፤ አንድ የክብር አለቃ፣ አንድ ዋና አለቃ፣ አንድ ዋና ፀሐፊ፣ አንድ ዋና ገንዘብ ያዥ፣ ከሦስት እስከ ሰባት አማካሪዎች እንዲኖሩት መተዳደሪያ ደንቡ ይደነግጋል። በሃያ ሁለት አንቀጽ የተቀመረው የማኅበሩ ደንብ እያንዳንዱን አባል በመሐላ የመተማመኛ ቃል እንዲገባ ያደርጋል። ዋስ ያስጠራል። የመተማመኛ ቃሉ፣

1ኛ. ምንም ቢቸግረን ወንድሞቻችንና ጓደኞቻችንን አንከዳም።

2ኛ. የሀገራችንን ነፃነትና ክብርዋን የሚጎዳ ሥራ በማናቸውም ምክንያት አንሠራም።

3ኛ. የንጉሠ ነገሥቱን መንግሥት መቃወም የለብንም። የሚሉ ፍሬ ነገሮች የያዘ ነው። ቀደም ብዬ እንደጠቆምሁትና እንደሚታመነው፣ የንጉሠ ነገሥቱ እጅ ሳይኖርበት አልቀረም። ይህም በሦስተኛ ተራ ቁጥር ከተነገረው ላይ ይታያል። ጥቅምት 23 ቀን መደንገጉም አንዱ ምልክት ነው።[8]



በጊዜ ሂደት እንደታየው፣ ይህ ማኅበር ከሌሎቹ የተሻለ ውጤት አስገኘ። ለማኅበሩ ጽንአት ከሰጡት ነገሮች ዋነኛው፣ አከራካሪ ከሆኑ የፖለቲካ ጉዳዮች ራሱን ማራቁ ይመስላል። ለምሣሌ መንግሥትን በተመለከተ ሕግ እንደሚያከብር ከመግለጽ በስተቀር፣ ስም ጠርቶ የእገሌን መንግሥት አላለም። ማኅበሩ ጥቅምት 23 ቀን 1931 ዓ.ም ቆመ ቢባልም፤ ደንቡ እስከ ጥር 1 ቀን ድረስ በጽሑፍ ተቀርጾ አልወጣም። ይህም በደንቡ አጻጻፍ ላይ ጥንቃቄ እንደተደረገበት ያመለክታል። ይህንን ማኅበር ያቋቋሙ ሰዎች ምስጋና ይገባቸዋል። ማኅበሩ ጦርነቱን በአሸናፊነት ከመወጣቱም በላይ፤ እስከ ዛሬም ድረስ መንገላታት ለበዛበት አርበኛ መጠለያ ሆኖአል።

<u>ማጣቀሻ ፅሑፎች</u>


1. Richard Greenfield, *Ethiopia*, p.243.
2. ታደሰ ሜጫ፣ *ጥቁር አንበሳ*፣ ገጽ 25-28።
3. እኔ ራሴ የማውቀው።
4. ሕይወት ኀደሩ፣ *ያቺ ቀን ተረሣች*፣ ገጽ 237-240።
5. ገሪማ ታፈረ፣ *ጐንደሬ በጋሻው*፣ ገጽ 137-140።
6. ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ*፣ ገጽ 254፣ 335 እና 195።
7. ዘውገ ዘገየ፣ *አባ ኮስትር*፣ ገጽ 16።
8. ከ1 ኢትዮጵያዊ፣ *የአርበኞች ትግል ከፋሺስት ጋር* ፣ገጽ 13-19።

# ምዕራፍ አርባ አምስት
## ጤናና ምግብ

በጦርነቱ ጊዜ እጅግ አስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች አንዱ የጤናና የሕክምና ጉዳይ ነው። በኢትዮጵያና በጣልያን ጦርነት፣ ጤናና የሕክምና ችግር በኢትዮጵያ ወገን እጅግ ከባድ እንደሚሆን ቀደም ብሎም ተገምቶ ነበር።

በንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር ሐምሌ 1 ቀን 1927 ዓ.ም አዲስ አበባ ተቋቋመ። ለማኅበሩ እንቅስቃሴ መጀመሪያ፣ ሁለት መቶ ሺህ ብር ተሰጠው። እሱም በዓለም የቀይ መስቀል ማኅበር በኩል የእርዳታ ጥያቄ ለልዩ ልዩ አገሮች አስተላለፈ። የእንግሊዝ፣ የስዊድን፣ የሆላንድ፣ የኖርዌ፣ የግብፅ የቀይ መስቀል ማኅበሮች ሐኪሞች፣ መድኃኒት፣ የሕክምና መሣሪያ፣ አምቡላንስ፣ ድንኳን ላኩ። የፈረንሣይ፣ የጀርመን፣ የጃፓን፣ የቱርክ፣ የአሜሪካን፣ የመስኮብ፣ የግሪክ፣ የአውስትራልያና የሌሎችም ሀገሮች የቀይ መስቀል ማኅበራት በገንዘብም፣ በመድኃኒትም የተቻላቸውን ያህል ረዱ።

የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል እነዚህን ዕርዳታዎች የማስተባበርና ለጦሩ የሕክምና ሥራ መስጠቱን ጀመረ። ሐኪሞችን በሰሜንና በምሥራቅ፣ በደቡብ የጦር ግንባሮች አሠማራ። የስዊድን አምቡላንስ ቡድን በቦረና በኩል፣ የእንግሊዝና የሆላንድ በማይጨው ጦር ግንባር ተደለደሉ። የግብፅ፣ በጅጅጋ በኩል ገባ። የተቻላቸውን ያህል የኢትዮጵያን ሠራዊት ረዱ።[1] ጣልያኖች የቀይ መስቀል ቡድኖቹን አስመርሮ ለማባረር፣ እግረ መንገዳቸውን በጦርነቱ ላይ ለሚፈጽሙት ግፍ ምስክር እንዳይኖር ለማድረግ፤ ሆን እያሉ በብዙ ቦታ በአይሮፕላን ደበደቡአቸው።

የስዊድን አምቡላንስ ቡድን አይሮፕላን ከራሱ መንግስት አገኘ። መድኃኒት በእሱ እየተጓጓዘ እንዲደርስለት ተደረገ። ከአይሮፕላን ነጂዎቹ ዋነኛው ሻምበል ጉስታፍ የተባሉት የስዊድን መሥፍን ነበሩ። እሳቸውም በበጐ ፈቃደኝነት ኅዳር 27 ቀን 1928 ዓ.ም ከጅቡቲ በድሬዳዋ በኩል አዲስ አበባ ገብተው፤ ከረዳታቸው ከአቶ ተስፋዬ ኃይሌ ጋር በድምሩ ሰባ አምስት በረራ በማድረግ የቀይ መስቀል እርዳታ ለገሱ። በኋላ፣ አይሮፕላኑ ኮረም አርፎ በምድር ላይ እንዳለ፣ ጣልያኖቹ በቦምብ አቃጠሉት። አብራሪዎቹ ለጊዜው ከአይሮፕላኑ ውጭ ስለነበሩ ከሞት ተረፉ። መሥፍኑ እንደገና ወደ አዲስ አበባ በመመለስ የዕርዳታ ሥራቸውን ቀጠሉ። የመጨረሻ በረራ ያደረጉት በጥቅምት ወር 1929 ዓ.ም ጐሬ ድረስ በመብረር ነበር።

ወይዘሪት ስንዱ ገብሩና ወይዘሪት ጽጌ መንገሻ ከጐሬ ሐኪም ቤት የቻሉትን ያህል መድኃኒት በመውሰድ፤ በራስ እምሩ ይመራ የነበረውን ጦር በእጅጉ ረድተዋል።[2]



ጣልያኖች አሸንፈው አዲስ አበባ ሲገቡ የዓለም ቀይ መስቀል ማኅበር ከሀገር ወጣ። የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር ፈረሰ። የሚገርመው ደግሞ አንዳንድ ጣልያናውያን ሀኪሞች ለጊዜው ኢትዮጵያውያን የጦር ቁስለኞችን እየተቀበሉ አከሙ።

ለዚህ አባባል እንደ ማስረጃነት የሚጠቀሰው የደሴ ሀኪም ቤትና አዲስ አበባ እቴጌ መነን ትምህርት ቤት የነበሩት ሀኪሞች ናቸው። ለማስረጃ ያህል ባሻ ደምሴ ወልደማርያም የተባሉ የአዲስ አበባ ሰው በማይጨው ጦርነት ቆስለው ሳስታ፣ ኩል መስክ ከአንድ ገበሬ ቤት ቆይተው ደሴ ገቡ። ደሴ ሲደርሱ ጣልያኑ እንደሚያክማቸው ስለተረዱ ወደ ሐኪሙጋ ሄደው መታከም ይይዛሉ። ከሐኪሙ ጋር ከመለማመዳቸው የተነሣ ከዕለታት አንድ ቀን ጣልያኑ "ለመሆኑ የት ነው የቆሰልከው?" ይላቸዋል። እሳቸውም ያደረገውን ያድርገኝ ብለው ማይጨው መሆኑን ነገሩት። እሱም መልሶ "ከየትኛው ወገን ሆነህ?" ደግሞ ጠየቀ። እሳቸውም አንድ ጊዜ ቆርጠዋልና "ከኢትዮጵያ" ብለው መለሱ። ቀጥሎ የነበረው ጥያቄ "የት ጋ ነበርክ"? እሳቸውም የተሰለፉበትን ጐራ ቢነግሩ "ከዚያማ እኔ ነበርኩ። እንዴት አልተገናኘንም ታዲያ" አላቸው። እሳቸውም ብንገናኝማ አንዳችን አልነበርንም በማለት ቁጭታቸውን ገለጹለት። እሱም ቁስላቸው እስኪድን አክሞ፣ ገንዘብ ሰጥቶ ወደ አዲስ አበባ ላካቸው።[3]

ከዚህ ዓይነቱ አስገራሚ አጋጣሚ ባለፈ፣ አርበኛው በጣልያኖች የመታከም ዕድል አልነበረውም። ቁስለኛ ለሕክምና ቢቀርብ፣ በማሰቃየት መርምረው ይገድሉታል እንጂ አያክሙትም። እንዲያውም አባቱ አርበኛ የሆነ ሰው ልጅ ቢታመም፣ ወደ ሐኪም ቤት አይሄድም ነበር። ከዚህ የተነሣ የቡልጋው አርበኛ የደጃዝማች ኃይሉ ወልደመድኅን ልጅ ከራሱ ላይ ቢፈነክት መታከም ባለመቻሉ፣ ብዙ ጊዜ ሊሰቃይ ችሏል። ስለሆነም፦ ሐኪሞቹ መሐላቸው ለዜጎቻቸው ብቻ ነበር ወይ? ያስብላል።

በአርበኛው ላይ የደረሰው የጤና ችግር ብዙ ነው። በመርዝ ጋዝ ይለበለባል፣ በጥይት ይመታል፣ በሣንጃና በጩቤ ይወጋል፣ በቦምብ ፍንጣሪ ይቆስላል። ሲሸሽ ወይም ሲያበር ይወድቃል፣ ጭር ይዘረዋል፣ ይሠበራል፣ እሾህ ይወጋዋል፣ ጋሬጣ ይገሽልጠዋል። ጫማ የለውም። በረሀብ ሰውነቱ ይካክማል፣ ባልተስማማ ምግብ ምክንያት የትውከትና የተቅማጥ ሕመም ይይዘዋል። ወባ ያመዋል። እንደተስቦ፣ ፈንጣጣ፣ ኩፍኝ ያለ ተላላፊ በሽታ ደግሞ ልጆችን ይፈጃል። ቂጥኝና ጨብጥም አለ።

ለኢትዮጵያውያን የነበረው ህክምና የሀገር ባህል ነው፤ ሌላ አልነበረም። በመርዝ ጋዝ ለለበለበው ሰው ቁስሉን ጨቃሚ በሚባል እንጨት ፍሬ ቶሎ ቶሎ ማጠብ ነው።[4] ይበልጥ እንዳይገሸላለጥ በጨርቅ ሳያስሩ አየር እንዲያገኝ ማድረግ ያስፈልጋል። ታላቁ ጥንቃቄ ዝንብ እንዳይነካው ከማድረጉ ላይ ነው።

በጥይት ለተመታ፣ በሣንጀ ለተወጋ፣ በጩቤ ለተሰለበ፣ በቦምብ ለቆሰለ መጀመሪያ ደሙን ማቆም ነው። ደሙን ለማቆም የተረፈውን ሥጋውን ከግራና ከቀኝ ጐትቶ ማሠር፤ የሚያውቅ ሰው ከተገኘ ደም የሚያቆም ቅጠል በጥሶ ከቁስሉ ላይ መጭመቅ ነው። ከዚያ በኋላ የአጠፋሪስ ፍሬ እያሣረሩ፣ እየወቀጡ መደምደም ነው። ከሁሉም ይበልጥ የሚያስቸግረው የተሰለቡ ሰዎችን ማስታመም ነው።

ብረት የሆነ ነገር ያልነካውን ቁስል፣ ማለትም እንቅፋት የመታውን፣ ጋሬጣ የገሸለጠውን የሚያድነው የተጠቃሹ የራሱ ሽንት ነው። ለወለምታና ለሥር መዞር በቅባት መታሸት ነው። በሩጫ ብዛት ቡቃ የሚወርዳት ሴትም ካለች፣ ለእሷም እንደዚሁ ነው። በክረምት ወራት እግርን በሞቀ ውሃ አዘውትሮ መታጠብ ነው። ያለዚያ ጮቅ ይይዛል፤ ጭቃው እግርን ይቆራርጣል። እንደ ጥቅምት ባለ የብርድ ወራት በጥዋት ደጋ ከተወጣ የእግር ንቃቃት ያጋጥማል። ለእሱ ደግሞ የሚሻለው የዶሮ ስብ ከማር፣ ከቅቤ ጋር ተለውሶ በእሳት በማቀጣጠል ፍላቱ እንዲወርድበት ማድረግ ነው። ፍላቱ ከጤናማው አካል ላይ እንዳያርፍ ቁርበት ወይም ሌጦ በቁስሉ ልክ በስቶ ማልበስ ነው። እሾህ ውስጥ እግሩን ለወጋውም መድኃኒቱ ይኸው ነው። ለስብራት ይጠቀሙበት የነበረው በተቻለ መጠን ሁለቱን ወገን አገጣጥሞ ማሠር ነው። ይህ የተለየ ችሎታ ያለው ወጌሻ ይጠይቃል።

በልዩ ልዩ ምክንያት የተቅማጥ ተውሳክ ይነሳል። ቡና መጠጣት ያስታግሰዋል ብለው የሚያምኑ አሉ። ህመምተኛው አቅም ካለው ኮሶ መጠጣትም ይረዳዋል። ለወባ ሽምብራና ነጭ ሽንኩርት ከተጣራ ቅቤ ውስጥ ተዘፍዝፎ ሲረጋ ያንኑ ጥዋት፣ ጥዋት መብላት ኩክ እንዳትሠራበት ይከለክላል ተብሎ ይታመናል።

የተጠማ ሠራዊት ውሃ ጆው አድርጐ እንዳይጠጣ፣ ቀስ ብሎ ጉንጭ በጉንጭ እንዲጠጣ፤ እርቦት ጠኔ የጣለው ወይም በረሃብ የተጐዳ ሰው ምግብ ጥቂት በጥቂት መብላቱ እንዲያገግም ይረደል። ለትንታ ቶሎ ከተቀመጡበት መነሳት ያስፈልጋል። ቶሎ በሽታ የለውም፣ ንፍሮ ግን አያጣውም። ለአደረ ንፍሮ መድኃኒቱ እንደገና መቀቀል ወይም ማገንፈል ነው። እርጐ መጠጣት አደገኛ ነው። ማርም በመጠኑ ካልሆነ ሆድ ይቀበትታል፤ በቀበተተ ጊዜ መድኃኒቱ የሞቀ ነገር መጠጣት ወይም ሆድን እሳት ማስመታት ነው።

ሌላው የምግብ ጉዳይ ነው። ከዱር፣ ከጫካ የሚለቀም ፍራፍሬ፣ ሥራ ሥር በሚሆን ጊዜ የሾላ፣ የአጋም፣ የቀጋ ፍሬዎች ደህና ናቸው። በደቡብ አገሮች ቦይና፣ ጐደሬ የሚባሉ አሉ። በገናሌ ወንዝ ከውጊያ የተመለሰው ጦር ቆኒ እና ቀጭ ቀጭ የተባሉ ፍሬዎች መብላት ነበረበት። ዋናው የአርበኛው ምግብ የከብትና የአውሬ ሥጋ ሆኖ ነበር። ቆቅ፣ ጅግራ፣ ድኩላ የመሳሰሉት አራዊት በጣም ረድተዋል።[5]



በአርበኛው ላይ የወረደ አንድ ቸነፈር በተለይ መጠቀስ ይገባዋል። አርበኛው እንቅጥቅጥ ይለው ነበር። የቡልጋን አርበኛ የፈጀ፣ የተረፈውንም ያቀጨጨና አቅመ ቢስ ያደረገ እሱ ነው። ባህርዩ እንደ ወባ ያለ ነው። ጊዜ እየለየ ያንቀጠቅጣል። ከአንቀጠቀጠ በኋላ በኃይል ያተኩሣል፤ ከመጠን በላይ ያልባል። የዚህ ደዌ መፈራረቅ ሰውየውን ያከረፋዋል። ያስርበዋል፤ በልቶ ግን አይጠግብም። ወይም አላስበላ ብሎ ይደብተዋል። በአገር የሌለ ምግብ አምጡ ያሰኘዋል። ያቃዠዋል፤ አንዳንዱንም ያሳብደዋል። አፋቸውን ያጣመመባቸው አሉ። አንዳንዶች ከዚህ በሽታ በጠበል ድነዋል። እንደ ልክፍት መስሎ የታየበትም ጊዜ አለ። ህመሙ እየቆየ የሚቀሰቀስ ከሆነ ህመምተኛው የመዳን ተስፋ አለው። እየፈጠነ ከተነሣበት ተስፋ የለውም። የገደለውን ገድሎ ከሞት የዳነውን ቀጫጫ፣ አቅመ ቢስ ያደርጋል።

ሌላው በሰው የተጫወተው ቁስል፣ ጫጉየ ነው። የቆላ ቁስልም ይሉታል። አንድ ጊዜ ከያዘ ደጋም ቢወጡ አይለቅም። ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፈው በዝንብ ነው። በትንሹ ይጀምርና ቁስሉ መሀሉ ይጐደጉዳል። እዥም፣ ደምም አይወጣውም። ሥጋን ይበላል፣ አጥንትን ይፈረፍራል። ፋታ አይሰጥም፤ በመዓልትና በሌሊት ያሰቃያል። ያገኙና የቻሉ ክብረ ሰማይ ደምድመውበታል። ጥዋት ጥዋት መታጠብ ያስታግሰዋል። አጥንት የሰበረበት፣ በጣጥሶ የገደለበት ሁኔታ ታይቶአል። አቶ ኃይለ ገብርኤል የተባለውን አርበኛ ለሞት ከአቃረበው በኋላ፤ በእርቅ ጊዜ ጣልያን አሥመራ ወስዶ አክሞ ከዚህ ደዌ አዳነው። ስለዚህ በህክምና ረገድ መድኃኒት አለው ማለት ነው። በሀበሻ ግን አንዳች አልተገኘለትም።

ከአራዊት ጅብ እና ክፋቱ ሊነገርለት ይገባል። በተለይ በ1932 ዓ.ም ቡልጋን ጅብ አጥለቀለቀው። በአሥርና በአሥራ አምስት መንጋ፣ በቡድን እየሆነ አገሩን አነጠነጠበት። ብዙ ሰው በላ። በተለይ ሙገሬ ዛላ በሚባለው፣ ጭንቂት ጥቂቶችን ከጀመራቸው በኋላ በመትረየስ ተኩሶ ማስለቀቅ ተችሎአል። ጀሎ አገር ግን በአንድ ሌሊት ሃምሣ ሁለት ህመምተኞች ጨርሶ በላ። ጥይት ሲተኮስበት መሬት ላይ በመንደባለል የተመታ በመምሰል ያስካካና ሲቀርቡት ጠልፎ ይዞ ይሄዳል። በዚያን ጊዜ በታየው ዓይነት ብዛት፣ ከዚያ በፊትና ከዚያም ወዲህ ታይቶ አይታወቅም።

## ማጣቀሻ ፅሑፎች


1. ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ፣ 1ኛ መጽሐፍ*፣ ገጽ 175-176።
2. ታደሰ ሜጫ፣ *ጥቁር አንበሳ*፣ ገጽ 66-67 እና 106።
3. ባሻ ደምሴ ወልደ ማርያም ያጫወቱኝ።
4. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 192-193።
5. ሰይፉ አምበሉ፣ *የታሪክ ቅርስ*፣ ገጽ 83-85።

# ምዕራፍ አርባ ስድስት
# ከሀዲዎችና የክህደት ሥራቸው

በኢትዮጵያና በጣልያን ጦርነት ታሪክ ውስጥ እንደ ኮሶ የሚመረው ክፍል፣ የከሀዲዎችንና የክህደት ሥራቸውን የሚመለከተው ነው። ኮሶን ካልጠጡት በስተቀር እንደማያሽር፣ ይህንንም ነገር በደንብ ካልመረመሩትና ካልተገነዘቡት፣ ከሀገር አይጠፉም። ወደፊትም እየተደጋገመ ሊደርስ ይችላል። ስለዚህ የቱንም ያህል መራር ቢሆን፣ ታሪክ ነውና መመልከት አለብን።

ማናቸውም ክህደት፣ ምንግዜም ያው ክህደት ነው። ቢሆንም ደረጃው ይለያያል። በአንድ ሰው ላይ ከተፈፀመ ክህደት፣ በብዙ ሰው ላይ የተፈፀመ ክህደት ይለያል። በንጉሥና በሀገር መሪ ላይ የተፈፀመ ደግሞ በብዙ ሰው ከተፈፀመውም ይበልጣል። በሕዝብ መካከል ብጥብጥና እልቂት ያስከትላልና፣ በሀገር ላይ የሚፈፀም ክህደት ግን ከሁሉም በላይ ነው። ከጠቅላላ ጥፋትም ያደርሳል፣ በዓይነቱም ከሁሉም ይልቃል። የከሀዲው እውቀትና ደረጃም ከግምት መግባት አለበት። ተራ ሰው ቢክድ ይቀላል። በአንድ መንግሥት የተሾመና የተሸለመ፣ የተማረ ሰው ሲክድ ያስገርማል። ያስደንቃል። የሚያደርሰውም ጉዳት በዚያው መጠን ይሆናል።

በጦርነቱ ጊዜ በኢትዮጵያ ላይ የደረሰው ክህደት ከባድ ነበር። የጀመረውም ጦርነቱ ከመከፈቱ አስቀድሞ ነበር። በአጠቃላይ ቢታይ ዋነኞቹ የክህደት ተዋናዮች የንጉሠ ነገሥቱ ባለሟሎችና ከፍተኛ ሹማምንቶች ነበሩ። የሚያፍሩት፣ የሚፈሩት እንዳልነበረ ይገመታል። ገና በአገር ደህና አዲስ አበባ ከነበረው የጣልያን ሌጋሲዮን ጋር ግንኙነት የፈጠሩም ነበሩ። አበል የተቆረጠላቸው ወይም ድጐማ ይሰጣቸው የነበሩ እንደማይታጡ ብዙ ማስረጃ ጭምር ነበር።

የክህደቱን በር የከፈተው የትግሬው መሥፍን ደጃዝማች ኃይለሥላሴ ጉግሣ ነው። ከእሱ ቀድመው ለጣልያን የረዱ አልነበሩም ማለት አይደለም። በገሀድ ከኢትዮጵያ ወጥቶ አሥመራ በመሄድ፣ ጥቅምት 1 ቀን 1928 ዓ.ም ከጣልያን ጦር ጐን ለመቆም የመጀመሪያው ሰው ሆነ። የእሱ ክህደት የጦርነቱን ሚዛን በአንድ ጊዜ ወደ ጣልያን አዞረው። በኢትዮጵያ ወገን የነበረውን ማንኛውንም ምሥጢር ሰጠላት ሰጠ። ከ1200 ጠመንጃና ከ8 ያላነሰ መትረየስ አስረከበ።[1] ከአዲስ አበባ እስከ ኮረም የተሠራውን መንገድ ፕላን ሰጠ። የትግሬን ልቡና ከፋፈለ። ለሌሎች ከሀድያን በር ከፈተ።



ከደጃዝማች ኃይለሥላሴ ጉግሣ ቀጥሎ የክህደት ሥራ ያካሄደው የጉጃሙ ደጃዝማች ገሠሠ በለው ነው። እሱ ወደ ጣልያን አልገባም። ነገር ግን እነ ፊታውራሪ ታምራትን፣ እነ ፊታውራሪ ገሠሠ ጉግሣን፣ እነፊታውራሪ ዘለቀ ካሣን፣ እነ ፊታውራሪ ዘለቀ ወሌን አሳብሮ ወደ ኋላው በመመለስ ጎጃም ገባ።[2] የንጉሠ ነገሥቱ አዋጅ፣ የጳጳሱ ግዝት አላገደውም። እነዚህ ሹማምንት ከጦር ግንባር መመለስን እንደ ሽሽት፣ እንደ ክህደት አልቆጠሩትም። ነገር ግን የሀገሪቱን የጦር ግንባር ሰበሩት። ሞሶሊኒ "...የመርዙንና የጢሱን፣ የቦምቡንም ነጐድጓድ እየተመረሩ የካዱ ይመስላል..." ብሎ እስከ መፎከር አደረሰው።[3] እነሱ የተመለሱት ግን አንዳች ደርሶባቸው አልነበረም። ንጉሠ ነገሥቱ ቢቸግራቸው ለሠራዊቱ ምሕረት አድርገው፣ አለቆቹ ታድነው እንዲያዙ አዘዙ። ሌላ ትግል ተፈጠረ። እነሱም ሳይያዙ ቀሩ።

ጣልያኖች የሬዲዮ መልእክት መጥለፊያ መሣሪያ አበጅተው፣ በአማርኛ ቋንቋ የሚተላለፉ መልእክቶችን ወደ ጣልያንኛ የሚተረጉሙ ሰዎች ቀጥረው፣ በቁጥር የሚተላለፉ የምስጢር መልእክቶችን የሚፈቱ ሰዎች መድበው፣ ከኢትዮጵያ ጦር ግንባሮችና ከአዲስ አበባ የሚተላለፉ መልእክቶችን ይወስዱ ነበር። ከዚህም በስተቀር የሬዲዮ ቴሌግራፉን ሥራ የሚመራው ሲቢሊንስኪ የተባለ ፈረንጅ ነበር፣ በመሆኑም ማንኛውም ምሥጢር በእጃቸው እንደገባ የሚቆጠር ነው። ኢትዮጵያውያን ስልከኞችም በገንዘብ እየተገዙ ሆነ ብለው ምሥጢር እያሳለፉ ይሰጡ ነበር። ጣልያኖች በተለይ ከጥር 10 ቀን 1928 ዓ.ም በኋላ ማንኛውንም የሬዲዮ ግንኙነት መቆጣጠር ችለው ነበር። በዚህ ሁኔታ የተጠራጠረው ንጹሁ ኢትዮጵያዊ የስልክ ሠራተኛ፣ አቶ ሙሴ ብርሃኔ በትኩሱ ለሥራው ኃላፊ፣ ለአቶ ወርቁ ይታጠቁ ነገሩን አስታወቀ። የቃሉ አስተላላፍ አመታት የጣልያኖች እጅ እንደ አለበት አስረዳ። ነገር ግን አንዳች አልተደረገም።[4] ስለዚህ በክህደቱ ሥራ አቶ ወርቁም አለበት ማለት ነው።

ጣልያኖች የማርትሬዛ ብር አሰርተው ለኢትዮጵያ መሣፍንትና መኳንንት እየከፈሉ፣ በጦርነቱ እንዲተባበሩአቸው ልቡናቸውን ይሰልቡ ነበር። ለማስረጃ ያህል አንድ ሁኔታን እጠቅሳለሁ። በአንድ ወቅት ጣልያኖች ኤርትራ ላይ አንድ ወታደራዊ ትርእይት አድርገው ለሕዝብ አሳዩ። ትርእይቱን የተመለከቱ የኤርትራ ሽማግሌዎች ዝም አሉ። ጣልያናዊው አገረ ገዥ "የማሽነፍ ዕድላችን ምን ይመስላችሁአል?" ብሎ ጠየቃቸው። ሽማግሌዎቹ "የኢትዮጵያ ወታደር ልባም ነው" ቢሉት፣ "ለእሱም 46 ሚሊዮን ሊሬ አዘጋጅተናል" አላቸው።[5]

ጣልያኖች በዚህ ዓይነት የሚያካሂዱትን ሥራ ንጉሠ ነገሥቱም ሳያውቁ አልቀሩም። በአንድ ወቅት አንድ በጣልያን ሌጋሲዮን የሚሠራ አንድ ሀገር ወዳድ፤ አበል የሚከፈላቸውን ኢትዮጵያውያን ዝርዝር አቀረበላቸው። ከጥቂት ቀን በኋላ ጣልያኑ ሲፈልገው ከቤቱ ሄደ፤ ከውሃ ጉድጓድ ተደብቆ ቆይቶ፣ ቡልጋ በመግባት ሕይወቱን አዳነ። አሥመራ የነበሩት የኢትዮጵያ ቆንሲል፣ አቶ ወዳጆ አሊ በበኩላቸው አዲስ አበባ ድረስ መጥተው፣ ደጃዝማች ኃይለሥላሴ ጉግሳ ከጣልያኖች ደመወዝ እንደሚከፈለው ቢገልጹ፣ ንጉሠ ነገሥቱ የሰጡት መልስ "…የኢትዮጵያ መኳንንት አብዛኛው ከጣልያን ገንዘብ ይቀበላል። ይህም የጣልያንን ኢኮኖሚ ለመጉዳት እንጂ እኛን ለመክዳት አይደለም…" የሚል እንደነበር በታሪክ ተመዝግቦአል።[6]

መጋቢት 21 ቀን 1928 ዓ.ም ፊታውራሪ ተድላ የተባለ የማይጨው ሰው፤ ለጦሩ መንገድ ከንጉሠ ነገሥቱ ከራሳቸው ተጠየቀ። እሱ ግን እሽ በማለት ፈንታ ገንዘብና መሣሪያ እንዲሰጠው ጠየቀ። ተሰጠው። የጠየቀው ከተሰጠው በኋላ ደግሞ "…ዛሬ ነው የምታውቀው" ከነጭራሹ እምቢ አለ። በዚህ ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ "አይ እግዚአብሔር ከእንደዚህ ያሉ ሰዎች ጋር ያኖርከኝ" ብለው አማረሩ።[7] ጣልያን ለኢትዮጵያውያን ገንዘብ መስጠቱ የእሱን የራሱን ኢኮኖሚ የሚጐዳ እንጂ፣ ሕዝብ ከእኛ የሚያስከዳ አይሆንም ብለው ያመኑት አመለካከት ስሕተት እንደነበር በዚያች ሰዓት ሳይረዱት አልቀሩም።

ሌላው ታላቅ ስሕተት የተፈፀመው በልዑል ራስ ኃይሉ ተክለሃይማኖት ነው። የእሱ ክህደት ቀደም ብሎ የታወቀ ስለነበር እንግዳ ነገር አልሆነም። ጣልያኖችን ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት የሚቻለውን ሁሉ አድርጓል። ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ስደት ሲሄዱ እሱንና ራስ ገብረ ሕይወትን ድሬዳዋ ድረስ ወስደው ለቀቁአቸው። ራስ ኃይሉም ባለፈው ሥራው ተጸጽቶ ለወደፊት በሚቻለው ሁሉ የኢትዮጵያን ነፃነት ለመጠበቅ የመሐላ ቃል ሰጥቶ ነበር።[8] ሆኖም ግን አንዳች መሻሻል አላደረገም። ሸንጡን ገትሮ እስከ መጨረሻው ድረስ ለጣልያን መንግሥት ተዋጋ። ንጉሠ ነገሥቱ ለንግግር ቢጋብዙት የሰጠው መልስ "…ከዚያ መከራ አውጥቶ ከሞት አትርፎ፣ ሀገሬን ሰጥቶ፣ ለዚህ ላበቃኝ ለጣልያን መንግሥት ምን ውለታ ልመልስለት?…" የሚል ነበር።[9] በጣልያን በመጋዙ፣ ሮም ድረስ ተወስዶ እዛ በመቆየቱ ቅር አላለውም።

ሌላው ከሀዲ ቀኛዝማች ተክለማርቆስ ወልደገብርኤል ነበር። ሹመቱ በአዋጅ አይሰጠው እንጂ፤ የጸሐፌ ትዕዛዝነቱን ሥራ ያካሂድ የነበረ፣ የንጉሠ ነገሥቱ ባለምዋል ነበር። ጥዑመልሣን ከመሆኑ የተነሣ



በንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ከፍተኛ ተደማጭነት ነበረው። ጣልያኖች ኢትዮጵያን በያዙ ጊዜ ዋና ባለምዋል ሆነ። የሰላሌ ገዥነት ተሰጠው። በአርበኞች እጅ ግንቦት 25 ቀን 1929 ዓ.ም ቢቆስልም፣ ከጉዳት ሳይቆጥረው አገልግሎቱን ለጠላት ቀጠለ።[10]

በሀገር ውስጥ የተሰገሰገው ፈረንጅ ለጣልያን መሣሪያ ሆኖ በኢትዮጵያ ላይ ያደረሰው ጉዳት እጅግ ነው። እርግጥ አንዳንድ የውጭ አገር ሰዎች ለኢትዮጵያ ረድተዋል። በሱዳን ኪጂ ኃይሉ ከዚህ ላይ መጠቀስ ይገባቸዋል።[11] የዲፕሎማቲክ ሹማምንት ሳይቀሩ፣ አብዛኛው የውጪ ዜጋ ግን ቀጥ ብሎ ለጣልያን ረዳ። ለምሣሌ የፈረንሣይ አምባሳደር ከሥራው ውጭ ለጣልያኖች መረጃ ይሰጥ ነበር። ትምህርት ቤት እየከፈቱ፣ ለስም ያህል ክሊኒክ እየከፈቱ በኢትዮጵያ ይኖሩ የነበሩ የውጭ አገር ሚስዮኖች፣ ለጣልያን አገልግሎታቸውን በብቃት ሠጡ። በተለይም የካቶሊክ እምነት ተከታዮች፣ ጣልያን ድል አድርጐ በገባም ጊዜ ሥራቸውን ቀጠሉ። አንዳቸውም ቅሬታ አላሳዩም። የስዊድን ወንጌላዊት ሚስዮን ብቻ ለግቶ ወጣ። የሚያስገርመው የውጭ አገር ሰዎች ይህንን መሥራታቸው አይደለም። እዚህ የነበሩት የውጪ ዜጎች ይህንን ሁሉ ሲያደርጉ፣ ከልካይ ቀርቶ ታዛቢ እንኳን አልነበረባቸውም። በንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ተቀባይነት አለማግኘቱ እንጂ፣ የውጭ አገር ሰዎች ይውጡ እየተባለ በየጊዜው፣ በገሀድ ጥያቄ ቀርቧል።[12]

በኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት ዘንድ ወትሮ ምክር የሚመከረው ከኢትዮጵያውያን ነበር። በተለይም በዳግማዊ ምኒልክ። ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘንድ ግን እንዲህ አልነበረም። ጦርነቱን መቋቋም የሚቻለው በዘመናዊ ዘዴ ነው ብለው ስላመኑ፤ ብዙ የውጭ አገር አማካሪዎች በዙሪያቸው ኮለኮሉ። የሚሰሙትም የእነሱን ምክር ብቻ ስለሆነ፤ የተማሩ ኢትዮጵያውያን ሃሳባቸውን የእነሱ ሃሳብ አስመስለው እንዲያቀርቡላቸው እስከ መለማመጥ ደርሰው ነበር። ከእነዚህ ነጭ አማካሪዎች ዋነኛው ኰሎኔል ኮኖቨሌቭ የተባለው ራሺያዊ ነበር። ሌላው የንጉሠ ነገሥቱ ባለምዋልና ምሥጢረኛ ፖሊአሉግ የተባለው ነው። እነዚህና ሌሎችም ፈረንጆች ምሥጢራችንን ሙልጭ አድርገው ስለሰጡአት፣ ጣልያን ልታሸንፍ በቃች።[12]

እነዚህ የውጭ አገር ሰዎች ለጣልያኖች የረዱበት መንገድ ባለብዙ ፈርጅ ነበር። እኩሎች ለጣልያን ወሬ በማቀበል፤ እኩሎቹ ለንጉሠ ነገሥቱ አሳሳች ምክር በመስጠት ጉዳት አደረሱ። ከዚህ ላይ ሳይጠቀስ የማይታለፈው፡- ከአዲስ አበባ እስከ ኮረም የተሠራው የመኪና መንገድ ጉዳይ ነው። መንገዱ የተሠራው በአሳሳች የፈረንጅ ምክር እንደነበር

አስማመን መታለል ነው። እኩሎቹ ደግሞ በየመኳንንቱ ቤት እየዞሩ የጣልያንን ትልቅነት በማውራትና የሰውን ልብ በመስለብ ብዙ ጉዳት አደረሱ። ምሳሌ:- ሙሴ ቀስተኛው ነው።

በወቅቱ የዋጅራትና ሌሎችም የአካባቢው ዜጐች ከማይጨው በሚመላለሰው ሠራዊት ላይ የግፍ ሥራ ፈፀሙበት። መሣሪያውን ቀሙት፤ ልብሱን ገፈፉት፤ ጨፈጨፉት።[13] ከጣልያን ገንዘብ እየተቀበሉ፣ በጠላት ስብከት እየተደለሉ የፈፀሙት ሥራ ቢሆንም፣ ለእነሱ ግን እንደ ክህደት መስሎ አልታያቸውም። የልጅ ኢያሱን ደም የተበቀሉ መሰላቸው። ታላቅ መታለል። ከወገናቸው የገፈፉትን መሣሪያ እየታሠሩ፣ እየተደበደቡ ለጣልያን አስረከቡ።

ጣልያኖች አዲስ አበባ ሲገቡ በምሥጢር ተይዞ የነበረው የክህደት ሥራ በገሀድ ወጣ። የዛን ጊዜ ደግሞ ቀጣዮቹ ከሀዲዎች ደጃዝማች አበራ ካሣና ደጃዝማች አስፋው ወሰን ሆኑ። ከወንድሞቻቸው ከእነ ሻለቃ /ራስ/ መሥፍን ስለሺ ምክር ይልቅ፣ የጠላታቸውን የግራዚያኒን ቃል አምነው ከሠራዊታቸው ተለይተው ገቡለት። እሱም ሳያውል ሳያሳድር፣ ዕለቱን በመግደል ዋጋቸውን ከፈላቸው። በአገዳደል ቢያዋርዳቸውም በጦር ሜዳ እንደ ሞቱ አድርጐ በማውራት አከበራቸው። ነገር ግን ዓለሙን ማታለል አልቻለም።

የደቡቡን የኢትዮጵያ ጦር ከአስጠቁት ነገሮች አንዱ መንገሻ ያለው እና ባዩ የተባሉት ሁለት ከሀዲዎች ለጠላት በሰጡት ምሥጢር ነው።

በራስ ደስታ ዳምጠው የሚመራው አርበኛ የጣልያንን ጦር ቀስፎ በመያዝ ከአቆየው በኋላ፣ አቅም እያነሰው ስለሄደ ወደ ኬንያ ለመውጣት አሰበ። ሁለት ሰዎች መንገድ ለመምራት ተስማምተው፣ ሰባ ብር ተቀብለው፤ ጦሩን የአንድ ቀን መንገድ ከመሩት በኋላ ሌሊቱን ተመሣጥረው፣ ጠላት መርተው አመጡበት። ሠራዊቱም አለቀ። ራስ ደስታ ዳምጠውም ሞቱ።[14] ከእነዚህ ከሀዲዎች እሸታ፣ የፊታውራሪ ተድላ እምቢታ ይሻላል።

አቡነ አብርሃም የተባለው የጐንደርና የጐጃም ጳጳስ በወቅቱ ጐንደር ነበር። ደሙ ከኢትዮጵያ ቢሆንም፣ ልቡ ከጣልያን ነበርና ወደ ዘመቻው ለመሄድ ንቅንቅ አላለም። ከጦር ሜዳ ስተመለሰው ሠራዊት ልብስ መግዣ እንዲሆን የተላከውን እና በአደራ እንዲያስቀምጥ የተሰጠውን ሠላሳ ሺህ ብር እንዲመልስ ቢጠየቅ፤ ጣልያን ድል አድርጐ ሲገባ "...አንተ ዘንድ የተቀመጠውን ገንዘብ አምጣ ቢለኝስ?" በማለት ከለከለ።[15] እውነትም ለእጅ መንሻ ሆነው፤ ጣልያን ሲገባ የኢጣልያ ምሥራቅ አፍሪካ ሊቀ ጳጳስ አደረገው። እሱም "...ታላቁ የኢጣልያ



መንግሥት በረቂቅ እውቀት፣ በሰፊ ቸርነቱ የተዋህዶ ሃይማኖትን ...የወንጌልን ቤተሰብ በክርስቶስ እያበዛ እንዲሄድ ነፃነትን ለሰጠ ለዚህ ታላቅ መንግሥት፤ ሰላማዊ ሆኖ መገዛት የሚገባ መሆኑን አሳስባችኋለሁ..." እያለ በየአደባባዩ ሰበከለት።[16] በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ካህናት፣ መነኮሳት ማለቃቸው፣ ከ2000 በላይ አብያተ ክርስቲያናት መቃጠላቸው፣ ለእሱ አንዳች ጉዳዩ አይደለም። ነፃነት የሚለው እሱ ከእስክንድርያ መላቀቁን ሆኑ።

ጣልያን አዲስ አበባ እንደገባ ከሀድያን በዙሪያው ተኮለኮሉ። ስድስት ራሶች፣ አንድ ጳጳስ፣ ሦስት ሡልጣኖች፣ አንድ ሼህ፣ አራት ደጃዝማቾች ያለአንዳች ችግር ገቡለት። በየአደባባዩ እያቆመ ቃላቸውን በመሐላ ተቀበላቸው። አስፈረማቸው። ደመወዛቸውንም እንደ አገልግሎታቸው እያየ ቆረጠላቸው። ከፍተኛው ደመወዝ፣ የዋና ታማኝ የራስ ኃይሉ ተክለሃይማኖት፤ ትንሹ ደግሞ፣ የደጃዝማች ታዬ ጉልላት ነበር።[17] ግራዚያኒ እንደዚህ ሲያደርግ፣ ናዚም በበኩሉ በጎንደር ለታማኞቹ የወር ምንዳ ቆረጠላቸው። በእሱ በኩል ደግሞ ታላቁ አረጋይ በክር ሲሆን አነስተኛው አጋጂ ፀሐይ ነበር። በሌሎች አራት ግዛቶች የነበረው አልታወቀም። መታየት ያለበት እነዚህ ሰዎችና መሰሎቻቸው ሀገራቸውን ኢትዮጵያ መሸጣቸው ነው።

በገጠር ስለነበረው ሁኔታ ደግሞ ለመጻፍ ይከብዳል። ደጃዝማች መሸሻ ተወንድ በላይ በጅሩ፣ ደጃዝማች ማሞ ኃይለ ሚካኤል በጐጃም፣ ደጃዝማች ሃብተ ማርያም በነቀምት፣ አባ ጆቢር አባጅፋር በጂማ፣ ደጃዝማች ዓመዴ በወሎ፣ ደጃዝማች አያሌው ብሩና አናዛዡ መነኩሴ አባ ተክለማርያም በጐንደር፣ ፊታውራሪ ተሰማ ከተማ በቡልጋ፣ ወሩ በላይነህና አሊ ዑመር በበረከት፣ ፊታውራሪ ሣህሉ ወልደገብርኤል በመንዝ፣ አቶ አበበ ዘገዮ እና አቶ ሰሙ በደብረ ብርሃን፤ በመርሐቤቴ ደግሞ ንዳው ጭንቅሎ፣ አፈቂሣር አፈወርቅ ሳይጠቀሱ አይታለፉም። ግብረ አበሮቻቸውም አሉ። እነዚህ ሰዎች የፈፀሙትን በደል ለመዘርዘር እጅግ ያስቸግራል። ሆኖም የአንዳንዶቹን አንዳንድ ሥራ እጠቃቅሳለሁ።

ደጃዝማች መሸሻ ዘጠኝ አርበኞች በገበያ ላይ አሰቀሏል። ደጃዝማች ማሞ ኃይለ ሚካኤል ራሱ ለጣልያን የጦር አዝማች በመሆን አዋግቷል። የእነዚህና የመሰሎቻቸው ደጃዝማችነት፣ ጣልያን የሰጣቸው ማዕረግ ነው። የጥቁር አንበሳ ጦር ተንከራትቶ ከምርኮ የወደቀው ደጃዝማች ሀብተማርያም ከወለጋ ሳለአስወጣው ነው። ሌላ በደል አልፈፀመበትምና፣ የእሱ ይቀላል።

አባ ጆቢር የአማራ ጭንቅላት በሠላሳ ብር እየገዛ ብዙ ሰው አስፈጅቶአል። ደጃዝማች አመዴ ሕዝብ እያነሳሳ፣ ከማይጨው በሚመለሰው ጦር ላይ አዝማች እየሆነ በሰጠው አገልግሎት፣ ከጣልያን ከደጃዝማችነት ማዕረግ ደርሶአል። አባ ተክለ ማርያም እሥረኞች ለሀገራቸው የሠሩትን እንደ ኃጢአት እያናዘዘ ብዙ ሰው አስፈጅቶአል። ሣህሉ ወልደገብርኤል ግራዝማች አጐናፍር የተባሉትን አርበኛ በአሰቃቂ ሁኔታ ከመግደሉም በላይ፤ ሰው በሲባጐ እያሠረ፣ ይበልጥ እንዲያጠብቀው ውሃ ያፈስስበት ነበር። ፊታውራሪ ተሰማ ከተማ አሥራ ሦስት ሰዎች ቤት ተዘግቶባቸው እንዲቃጠሉ አድርጓል። ወሩ በላይነህ በፊታውራሪ ኃይለሥላሴ የሚመራውን አርበኛ በማታለል አሲዞ አስፈጅቶአል። አሊ ዑመር ሦስት መቶ ሰማንያ ሦስት ሰው ሜንሶ ወንዝ ላይ አስፈጅቶአል። አበበ ዘገኑ በአርበኞች ላይ ብዙ ጉዳት አድርሶአል። አቶ ሰሙ ንጉሥ ለጠላት በሰጠው ረቂቅ ምሥጢር የራስነት ማዕረግ ተሰጥቶታል። ንዳው ጭንቅሎ እስከ ዕለተ ሞቱ አርበኞችን ሲፈጅ የኖረ ሲሆን፣ አፈወርቅ አፈቄሣር የተባለው በከንቱ አይደለም፤ በሰጠው አገልግሎት ነው።

ከዚህ በመቀጠል ደግሞ የክህደት ሥራዎችን ዓይነት እንመለከታለን። መሣፍንቱና መኳንንቱ ለጠላት ምሥጢር በማቀበል፣ የጦር ሥልት በማስጠናት፣ የአስተዳደር ምክር በመስጠት፤ የከዱት ጳጳሳት በመገዘት፣ መነኮሳትና ካህናቱ በከንቱ ስብከት ጠላትን ባያሌው ረድተዋል። ራሳቸው ለጣልያን ጦር፣ በተለይም ለባንዳው በመሪነት እየቆሙ ያዋጉ ብዙዎች ናቸው። በጣልያን አደባባይ ላይ እየተቀመጡ አርበኛ ተይዞ በቀረበ ጊዜ ፍርድ እያከበዱ ያስገደሉ አያሌ ናቸው። እንዲህ የሚያደርጉት ለጌታቸው ያላቸውን ታማኝነት በግብር ለማረጋገጥ ነበር። ከታዘዙት በላይ የጭካኔ ሥራ ያካሄዱ እጅግ ብዙ ናቸው። ግደሉ ሲባሉ ያሰቃያሉ። አሰቃይቶ በመተው ህይወቱን ለማትረፍ በሆነ ደግሞ አንድ ነገር ነው። እነሱ ግን አሰቃይተውም ይገድላሉ።

እነዚህ ሰዎች በዓላማ አንድ ናቸው። ፍላጐታቸው ጥቅምና ክብር ነው። ጣልያን ገንዘብ እንደ ልብ እያፈሰ ይሰጣል፤ ይሾማል፣ ይሸልማል። በመሆኑም ሠርቶ ማደር የማይችልና የማይፈልገው ከክህደት ሥራ ገባ። እንዲህ ባለ አቅሙ፤ እናት አገሩን እየሸጠ፣ የገዛ ወንድሙን እያጋለጠ፤ በላ።

ለመሆኑ እነዚህ ሰዎች ለክህደት ሥራቸው ምን ምክንያት ይኖራቸዋል? መቼም ለጥቅም፣ ለክብር ብለን ነው አይሉም። የሚደረድሩአቸው ሌሎች ምክንያቶች ነበሩአቸው። በደቡብ ከነበሩት፣ በዛ



ከተጠቀሱት ምክንያቶች ዋነኛው የጐሣ ልዩነትና የጥቅም ግጭት ነው። ነዋሪው ሕዝብ ነፍጠኛውን እንደ ጠላት ቆጠረው። ለዚህም የማይናቅ ምክንያት ነበረው። እምነትም አንድ የልዩነት ምንጭ ሆነ። ራያ ከጣልያን ጦር ጐን ቆሞ ታላቅ የሰለባ ዘመቻ ያካሄደው፣ በእምነት ምክንያት ጭምር እንጂ በጠላት ስለተደለለ ብቻ አልነበረም። ካቶሊኮች ደግሞ ወገን የመጣላቸው መሰላቸው። የግለሰብ ቂምም ሚና ነበረው። በግል ጉዳዩ ጠላቴ የሚለው ሰው አርበኛ ከሆነ፣ አይለቀኝም ብሎ እሱ ባንዳ ይሆናል። ሁሉም ሞኝነት ነበር።

የጣልያን ወረራ ለኢትዮጵያ ልማት ያስገኛል ብለው የሚያምኑና ይህንኑ የሚሰብኩም ነበሩ። ከሁሉም በላይ የተታለሉት እነዚህኞቹ ናቸው። ጣልያን ለሽንገላ ሲል ያደረገው አንዳንድ ነገር በሕዝብ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ቀላል ስለ አልነበረ ጭምር፣ እየተገደደ የዘመተው ገበሬ ፍርድ የለበትም። ከተርታው ህዝብ መካከል የወጡ ሰዎች ከፈጸሙት በደል ይልቅ፣ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ሹማምንትና መኳንንት የነበሩ የፈፀሙት ክህደት ይበልጥ ሊያስገርም ይገባል። ከዚህ ጋር ተጣምሮ መታየት ያለበት ነጥብ፣ የሚጐዱት ከጠላት ወገን የቆሙት ጭምር መሆናቸው ነበር። ባንዳም ቢሆኑ አርበኛ፣ ከጦር ሜዳ ከገቡ ሞት አይቀርም። ለሀገሩ ነፃነት፣ ለወገኑ ክብር የሞተ ሰማዕት ነው። ለባዕድ የሞተ፣ ለሆዱ እንጂ ሌላ ለምን ሞተ?

በአርበኝነትና በባንድነት የቆሰለውን ሠራዊት ቁጥር ማወቅ ቢቻል በጣም ጥሩ ነበር። ነገር ግን ይህንን በተመለከተ አስተማማኝ ማስረጃ የለም። ቢሆንም መሞከር አይከፋም። በጠላት ላይ ክንዳቸውን ያነሱ አርበኞች ጥቂት ናቸው። ቁጥራቸውም ከጊዜ ወደ ጊዜ፣ ከቦታ ቦታ ይለያያል። በጠቅላላው ሲታይ በ1928 ዓ.ም ከሚያዝያ እስከ ነሐሴ ባለው ጊዜ ውስጥ 40,000 ሠራዊት በአርበኝነት እንደተንቀሳቀሰ፤ በ1929 ዓ.ም ኃይሉ ቀንሶ ወደ 30,000 ዝቅ እንዳለ መገመት ይቻላል። ከዚያ በኋላ እንደገና አንሰራርቶ በ1930 ዓ.ም ወደ 80,000 ከፍ እንዳለ፤ በ1931 ዓ.ም ደግሞ እንደገና ተዳክሞ ወደ 60,000 ዝቅ እንዳለ፤ በ1932 ዓ.ም በእርቁም ጭምር ተመናምኖ ወደ 40,000 እንደ ወረደ ቢገመት እምብዛም ስህተት አይሆንም። የንጉሠ ነገሥቱ መመለስ ሲሰማም ባንዳ ተገልብጦ ከአርበኛ ጋር ተቀላቀለ። የድል አጥቢያ አርበኛ በዛ። በ1933 ዓ.ም ከጥር እስከ መጋቢት በነበረው ጊዜ 200,000 ሠራዊት በጣልያን ላይ እጁን ሳያነሣ አልቀረም።

የባንዳው ቁጥርም እንደዚሁ ከፍና ዝቅ ይላል። በ1928 በዋናው ጦርነት ጣልያን ከኢትዮጵያውያን 20,000 ያህል ሰው ከጐኑ ሳያሰልፍ

አልቀረም:: ጣልያን አገር እንደገባ *ሥራ* አድርጎ የያዘው ገበሬውን እየሰበከና እያስታጠቀ ማዝመት ሆነ:: በ1929 ዓ.ም የባንዳ ቁጥር 100,000 ሳይደርስ አልቀረም:: በ1930 ዓ.ም ጦርነቱ በቀላል እንደማያልቅ ለጣልያን ግልጽ ነበር:: በዚህ የተነሣ የባንዳ ምልመላውን በይበልጥ አጠናከረ:: እስከ 200,000 ሳያደርሰው አልቀረም:: የ1931 ዓ.ም በጣልያኖች ዘንድ *ሥጋት* የተቀሰቀሰበት ጊዜ ስለነበር፤ የባንዳን ኃይል ለማጠናከር ርምጃ ወስደው እያስገደዱ ገበሬ በማዝመት የባንዳ ሠራዊት አዘጋጁ:: በዚህ ዘመን የባንዳ ቁጥር እስከ 300,000 እንደደረሰ መገመት እምብዛም ስህተት አይሆንም:: ከዚህ ወዲያ አላደገም:: እየቀነሰ ሄደ:: በ1932 ዓ.ም ከ200,000 አልበለጠም:: በመጨረሻው የፍልሚያ ዘመን የባንዳ ቁጥር ይቀንስ እንጂ ከጦር ሜዳው አልወጣም:: እስከ መጋቢት ወር ድረስ 100,000 ያህል ባንዳ ለጠላት ሳይረዳ አልቀረም:: ከዚያ በኋላ ግን በፍጥነት ቀንሶአል:: ከሚያዝያ ወር በኋላ ከጣልያን ጎን የቆመው ከ20,000 ይበልጥ አይመስልም:: አንዳንዱ እስከ መጨረሻው ጊዜ ድረስ ከጣልያን ጎን ቆሞ የተዋጋ አለ:: በአምባለጌ፣ በወለጋ፣ በከፋና በኢሉባቡር፣ በመጨረሻም በጎንደር እስከመጨረሻው ለጣልያን የተዋጋለት ባንዳ ቁጥር ከ10,000 አያንስም::

አርበኛው የሚዋጋው ሚስቱን፣ ልጁን፣ ያለውም አሽከሩን እንደያዘ ነበር:: ስለዚህ ለአንድ አርበኛ ሦስት ቢያንስም ሁለት ጀሌ ይከተለዋል:: ከባንድነት ከድቶ የገባው ግን አብዛኛው ደረቅ ጦር ነበር:: ማለትም ጓዝ አልነበረውም:: ስለዚህ ከ240,000 እስከ 300,000 ሰዎች በጓዝነት፣ በጀሌነት ሳያገለግሉ አልቀሩም:: በዚህ የጓዝ ቡድን ውስጥ የቀድሞ ባሮችም ነበሩ:: በጣልያን ላይ ያላቸው ጥላቻና ለጌቶቻቸው የነበራቸው ታማኝነት፣ ከአርበኞቹ ዘመዶች በላይ ነበር:: ይህንን ሁኔታ እኔ ራሴ ያየሁ ስለሆነ፣ መመስከር ይገባኛል::

አርበኝነትን ከመሠረቱ ሰዎች አብዛኞች በዚያው በጦርነት ጊዜ አለቁ:: በሕይወት ቆይቶ ለሚያዝያ 24 ቀን 1933 ዓ.ም የበቃ እጅግ ጥቂት ነው:: በእኔ ግምት ከ10,000 አይበልጥም:: የሞተውን ወደ 78,500 ሰው ጨምሮ፤ 88,500 እሥረኛውንና ስደተኛውን ጨምሮ፤ 180,000 ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ሳያወላውል በዓላማው ጸንቶ የዜግነት ግዴታውን ተወጥቶአል ማለት ይቻላል::

የውስጥ አርበኞች *ሥራ* አርበኝነትን ረድቶአል:: መረጃ በመስጠት፣ ሲቻልም መሣሪያ በማቀበል፣ አንዳንድ ጊዜ መድኃኒት በመላክ በብዙ ደክመዋል:: እነ ወይዘሮ ሸዋረገድ ገድሌና ኬጆ ኃይሉ የሚጠቀሱ ናቸው:: ከዚህ ላይ መጠቀስ ያለበት ሌላው ነጥብ ደግሞ በቀዳማዊ ኃይለ



ሥላሴ ላይ ቅሬታ ባላቸው አርበኞች ላይ ጥቃት እንዲደርስ ያደረጉ ወገኖችም እንደነበሩ ነው:: የደጃዝማች ፍቅረ ማርያም አሟሟት ዱካ መጥፋት፣ የደጃዝማች ኃይሉና የባልደረቦቻቸው እልቂት ለዚህ አባባል ማስረጃ ሆነው ሊታዩ ይችላል:: በፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ ላይ ከመስከረም 7 ቀን 1933 ዓ.ም እስከ የካቲት 13 ቀን 1933 ዓ.ም ጣልያን የዘመተባቸውና በተለይም የባንዳ ናዳ የወረደባቸው በዚህ ዓይነት ዘዴ እንደነበር እውቅ ነው::

ከወልወል እስከ ጎንደር በተደረገውና ከ1927 እስከ 1934 ዓ.ም በቆየው የኢትዮጵያና የጣልያን ጦርነት ጊዜ፤ በኢትዮጵያውያን መካከል የተስተዋሉ የእምነትና የክህደት *ሥራዎች* ሲታዩ፣ አስገራሚ ገጽታ አላቸው:: የንጉሠ ነገሥቱ ሹማምንቶች፣ መኳንንቶች፣ ባለሙዋሎች ከጣልያን ጎን ቆሙ:: ለሀገሪትዋ የተዋጉላት፣ የሞቱላት፣ በንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ሞገስ አጥተው የታሠሩ፣ የተገረፉ ሆኑ:: ለአብነት ደጃዝማች አውራሪስ ዱሉ፣ ደጃዝማች ባልቻ እና ደጃዝማች በየነ ይጠቀሳሉ:: ሌላው ሕዝብ እንደ ልማዱ፣ እንደ ሥርዓቱ ኑሮውን ቀጠለ::

## <u>ማጣቀሻ ፅሑፎች</u>


1. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 53::
2. ተክለ ፃድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ፣ ከአጼ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ*፣ ገጽ 221::
3. ሞገስ ክፍሌ፣ *የሙሶሊኒ ምሥጢር*፣ ገጽ 70::
4. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 90-99::
5. ከርዕሰ ደብር ዕቀቦ እንድርያስ፣ አሥመራ የተነገረኝ::
6. ጳውሎስ ኞኞ፣ ገጽ 52::
7. ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ*፣ ገጽ 445::
8. *ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ 1ኛ መጽሐፍ*፣ ገጽ 245::
9. *ሙሉ ሰው ምትኩ፣ የአርበኞች ትግል ከፋሽስት ጋር*፣ ገጽ 25-26::
10. *ገሪማ ታፈረ፣ ጎንደሬ በጋሻው*፣ ገጽ 154.156::
11. Greenfield, *Ethiopia*, p.194-204.
12. ከበደ ተሰማ፣ ገጽ 447-449::
13. ተክለ ፃድቅ መኩሪያ፣ ገጽ 267::
14. ሰይፉ አበበ፣ *የታሪክ ቅርስ*፣ ገጽ 63 እና 184-185::
15. ሐዲስ ዓለማየሁ፣ *ትዝታ*፣ ገጽ 103-104::
16. *ገሪማ ታፈረ*፣ ገጽ 83-84::
17. Sabacchi, p.137 እና 155.

# ምዕራፍ አርባ ሰባት

## ግጥምና ቅኔ

የኢትዮጵያ ሕዝብ አስተያየቱን የሚገልጽባቸው ብዙ ባህላዊ መንገዶች አሉት። በቤተክርስቲያን ቅኔው ይፈሳል። በገጠር ሴቱ፣ ወንዱ ይዘፍናል። በአደባባይ ፉከራ ይካሄዳል። በመንገድ፣ በጉዞ ላይ ሽለላ፣ ቀረርቶ አለ። በመንደር እንጉርጉሮው አይቀርም። በክብረ በዓል፣ በሰርግና በድግስ ቤት አዝማሪ ግጥሙን ያንቆረቁራል። በመኳንንት ቤት በገና ደርዳሪ፤ በሀዘን ቤት ሙሾ የተለመደ ነበር።

በጦርነቱም ጊዜ እንደዚሁ ነበር። ቅኔዎቹ ሕይወትን በመንፈሳዊ አመለካከት ይገልፃሉ። ሴቶች ባሎቻቸውን በዘፈን ያደፋፍራሉ። ሲበረታ ያሞግሳሉ፤ ሲፈራ በነገር ይጐነጣሉ። ሠራዊቱም እየሸለለ ራሱን ያጽናናል። ሲያስፈልገውም አለቆቹን ይወቅሣል። አንዳንዱ በግልጽ ይናገራል። ሌላው በምሥጢር በነገር ይወጋል። በጠላት ጊዜ ይሰሙ የነበሩ ግጥሞች የማደፋፈሪያና ማበረታቻ፣ የትንቢት መናገሪያ፣ የተግሣጽና የምክር ዘይቤ ነበራቸው። በአለቆች ዘንድ ይደመጡ፣ በሕዝብም ዘንድ ይሰሙ ነበር። አንዳንዶቹን ቀጥሎ እንመለከታለን።

**የጠላት ወረራ እየተቃረበ ሲሄድ፤**

“አፈራ ደድሆ፣ አፈራ ደድሆ፣
የፈራነው ነገር መጣ ድሆ ድሆ” ተባለ።

**በጦርነት ወቅት፤**

“አህያ መጣች ተጭና ቋንጣ፣
ኃይለሥላሴ እጅህን አውጣ” አሉ።

**የአርበኝነት እንቅስቃሴ ሲጀመር ጀግናው፤**

“አልበላንም፣ አልጠጣንም፣ አልጠናም ክንዳችን፣
እንዲሁ እንሞታለን ለነፃነታችን” አለ።

**ጣልያን ድል ባረገ ጊዜ፤**

“በማይጨውስ ቢሆን መች ይገባ ነበር፣
በኦጋዴን ቢሆን መች ይገባ ነበር፣
በሰማይ ላይ ገባ ባላወቅነው አገር” ተባለ።

**የንጉሠ ነገሥቱ መሄድ በተሰማ ጊዜ፣**

“ፍርድ ለማግኘት ነው በዳኛ መግጠም፣
ዋቢ አናሳልፍም ሳንፈጣጠም” አለ።

**የየካ ደብረ ሣህል አበምኔት አለቃ በላይ፤**

“ተመልሰሽ ግቢ ተማሪ ቤት ቅኔ፣
ከወንዶቹ ጋራ መዋሌ ነው እኔ” ብለው ቀበና ሸፈቱ።



**ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ ጣልያን እንዲዘምሩ ቢያስገድዳቸው፤**

“የሀገሬ ልጆች በከንቱ አለቃችሁ፣
ጊዜው እንዳመጣ ባንድንሆን ብላችሁ” አሉ።

**ጣልያንና አርበኛ በተፋዘዙ ጊዜ፤**

“ወይ እነሱ አይመጡ፣ ወይ እኛ አንሻገር፣
መልካው ጦም አደረ የሁለት ፈሪ አገር” አለ።[1]

**ማመንታት በበዛ ጊዜ አንድ ሽላይ፤**

“እንሂድ አርበኞች ወርደን እናምሰው፣
ምን ይመክተናል ማተብ የሌለው ሰው” ብሎ ሸለለ።[2]

**ለእነ ደጃዝማች ኃይሉ ወልደመድኅን፤**

“የነአጅሬን እህል አልበላም እርሜ ነው፣
ያዘራው መትረየስ፣ ያበቀለው ደም ነው” ተብሎ ተለቀሰ።[3]

**ባንዳን ምን ማድረግ እንደሚሻል ግራ በገባ ጊዜ፤**

“በለው በምንሽር፣ በለው በምንሽር፣
እንዳይሄድ እንዳይቀር፣ እንዳይሞት እንዳይሽር” ተባለ።

**ደጃዝማች ኃይለሥላሴ ጉግሣ በከዳ ጊዜ፤**

“ምንኛ ይረግሙህ አቤ ዮሐንስ፣
የጽላተ ሙሴን ሥርዓት ስታፈርስ” ተባለ።[4]

**ለጣልያን የሚገባው በበዛ ጊዜ፤**

“ጐበዝ ይሙት፣ ጀግና ይሙት፣
- ፈሪ ይቁም ቢሻው፣
አተላ መሸከም ይችላል ትከሻው” ተብሎ ተሸለለ።

**ስለ ገንዘብ ወዳዶች፤**

“ለገንዘብ የሚሞት፣ ይቅር አይወለድ፣
አይበጅም ለሀገር፣ አይሆንም ለዘመድ” ተብሎ ተገጠመ።

**ጣልያን ራያን አዝምቶ ሸዋን ባሰለበ ጊዜ፤**

“ኢትዝክር ለነ አበባነ ዘትካት፣
ፍጡነ ይርከበነ ሣልከ እግዚኦ፣
እስመ ተመንደብነ ፈድደ” የሚለው ምስባክ ተሰበከ።

**የደብረ ታቦርን ሕዝብ ጣልያን በመትረየስ በፈጀ ጊዜ አንድ ሊቅ፤**

“ወአግባእከነ ድኅሬነ በ ፀርነ፣
ይብልዑነ ከመ አባግዕ፣
ወተማስጡነ ጸላእትነ፣
ወዘሮከነ ውስተ አሕዝበ፣
እስመ አህመምከነ በብሔርነ በብሔርነ ኢትዮጵያ፣
ወደፈነነ ጽላሎተ ሞት” አሉ።[5]

**አቡነ ጴጥሮስ በተገደሉ ጊዜ፤**

“የበጐች እረኛ ጴጥሮስ ሐዋርያን፣
ተኩላ ቢመጣበት ሊነጥቅ በጐቹን፣
ተኩላ ሲፈጃቸው ዓይኔ አያይም ብሎ፣
ከበጐች በፊት ሞተ ተከልሎ” ተባለላቸው::[6]

**ፊታውራሪ ኃይለሥላሴ ዘረፉ በተገደለ ጊዜ፤**
“በእገሌም በእገሌም አትዘክሩበት፣
ኃይለሥላሴ ነው በጋሻው ያራበት” ተብሎ ተገጠመ::

**የወንድምዋን ራስ ጣልያን ቆርጦ ያዞረባት ሴት፤**
“የፋሽስት ትምህርት ምን ያህል ከባድ ነው፣
የወንድሜን ራስ እንደዚህ ያዞረው” አለች::

**ሙሶሊኒ አርበኞች እንዲደመሰሱ ማዘዙ ሲሰማ፤**
“ጌታው ሙሶሊኒ ምን አቅበጠበጠው፣
አልነገረውም ወይ ከአድዋ ያመለጠው” ተባለ::[7]

**የደቡብ ጦር የጠላትን ማየል ባየ ጊዜ፤**
“ጠላት ከሚጠጣው የሀገሬን ውሃ፣
የእኔ ደም ይቀዳ በዱር በበረሃ” አለ::[8]

**የጥቁር አንበሳ ጦር የሚተምመው፤**
“በለው! በለው! አትለውም ወይ፣
ጥቁር አንበሳ አይደለህም ወይ?” እያለ ነበር::[9]

**ጥቁር አንበሳ ከወለጋ እንዲወጣ በተገደደ ጊዜ፤**
“እናት ኢትዮጵያ ውዲቱ ዉዲቱ፣
ላንቺ የማይረዳ ሳለ በሕይወቱ፣
በረከትሽን ይንሳው እስከ ዕለት ሞቱ::”[10]

**መከራ በጸና ጊዜ አርበኛው፤**
“ጠላትሽ ተዋርዶ ስምሽ እስኪከበር፣
እንሸከማለን የመከራ ቀንበር” አለ::[11]

**በነጮች ላይ ጥላቻ በተነሣ ጊዜ፤**
“እንግዲህ ባገሬ ነጭ ጤፍ አይብቀል፣
አረም ነው እያሉ ከሥሩ ነው መንቀል” ተባለ::[12]

**በእርቅም ጊዜ ሁኔታው ያላማረው ሰው፤**
“ሸዋ ሆድክን አትስጥ ያለሠረገላ፤
ባስፈለገህ ጊዜ ሽተት ወደ ቆላ::
አሁን ይሰጥና ዳቦ ለሁለት፣
የዛሬ ሣምንት አጋዴን ዝመት” ተብሎ ተገጠመ::[13]

**አለቃው ከጦር አጋፍጦት የሸሸበት ወታደር፤**
“የጭዋ አስተኛኘት እንደዚህ ነወይ?
ራስን ወደ ታች እግርን ወደ ላይ” አለ::[14]



**ጣልያን በተደናገጠ ጊዜ፤**
“ተጉዞ ተጉዞ ነጭ እንደ ደመና፣
መመለሻው ጠፋው ያገሩ ጐዳና” ተብሎ ተገጠመበት::[15]

**የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መመለስ ከመሰማቱ ቢያንስ ከአንድ ዓመት በፊት፤**
“አህያ መጣች ተጭና ጓሣ፣
ኃይለሥላሴ ሙቶ ተነሣ” ተባለ::

**ጃንሆይ ጐጃም መግባታቸው ከተሰማ በኋላ ጣልያን ለአቶ ተሰማ ደባልቀው ሹመት ሲሰጥ አዝማሪ፤**
“ማን አግኝቶ ያውቃል እንዲህ ያለ ሹመት፣
ከተሰማ በላይ ደጃዝማችነት” ብሎ አሽሟጠጠ::

**በጦርነቱ በወደቁ ጀግኖች ነጻነት ሲመለስ፤**
“የተዘራው ደምህ መቼ ከንቱ ቀረ፣
ነፃነት አፍርቶ ስምህ ተከበረ” ተባለላቸው::

**በጠላት ላይ ድል በተገኘ ጊዜ፤**
“ደሙን ያፈሰሰ ልቡ እየነደደ፣
በአርበኝነት ታጥቆ ጠላት ያስወገደ፣
ንጉሡን አገሩን ክብሩን የወደደ፣
ነፃነቱን ይዞ መልካም ተራመደ” የሚል የሰንደቅ ዓላማ መዝሙር ወጣ::

**ነፃነትን ባስመለሱ ጊዜ ለንጉሠ ነገሥቱ ብዙ ደጋግ ግጥም ተገጠመላቸው:: ከእነዚህም_አንዱ በከፊል፤**
“የይሁዳ አንበሣ አንተ ንጉሣችን፣
በድል መለስክልን ከሞት አገራችን፣
ሞት እንዳያገኘን ዘለዓለም ኑርልን::
አቸናፊው ንጉሥ የይሁዳ አንበሳ፣
መድፍህ የብስን አልፎ ጐጃም ላይ ቢያገሳ፣
እንኳን የሰው ወገን ደስ አለው እንስሳ” የሚል ነበር::[16]

**ባንዳ የንጉሠ ነገሥቱ ባለምዋል መሆን ሲጀምር አርበኛ፤**
“እናት ኢትዮጵያ ሞኝ ነሽ ተላላ፣
የሞተልሽ ሳለ የገደለሽ በላ” አለ::[17]

ንጉሠ ነገሥቱ ይህቺን ቃል ባለማድመጥ ተታለሉ::

## ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 119።
2. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 11።
3. ከአቶ ኃይለ ማርያም ወልደ ኪዳን የተገኘ።
4. ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ*፣ ገጽ 230።
5. ገሪማ ታፈረ፣ *ጐንደሬ በጋሻው*፣ ገጽ 151።
6. መኰንን እንዳልካቸው፣ *መጽሐፍ ማር ነው*፣ ገጽ 103።
7. ታደሰ ዘወልዴ፣ ገጽ 91።
8. ሰይፉ አባ ወሉ፣ *የታሪክ ቅርስ*፣ ገጽ 49።
9. ታደሰ ሜጫ፣ *ጥቁር አንበሳ*፣ ገጽ 72-73።
10. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 60።
11. ከግራዝማች ከበደ አርጋው ቁንጮ የተገኘ።
12. ታደሰ ዘወልዴ፣ ገጽ 493 እና 493።
13. ከግራዝማች ኃይሌ ዳርጌ የተገኘ።
14. ከሻለቃ ክፍሌ ደርሴ የተገኘ።
15. ገሪማ ታፈረ፣ ገጽ 160።
16. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 255 እና 258።
17. ዩፍታሔ ንጉሤ፣ የአማርኛ ሰዋሰው፣ መርሥዔ ሐዘን ወልደ ቂርቆስ።



# ምዕራፍ አርባ ስምንት
# የጣልያኖች ፖሊሲ

ኢትዮጵያን ድል ካደረገ በኋላ የጣልያን መንግሥት ለሀገሩ አዲስ ስም አወጣ። ሀገሩን የኢጣልያ ምሥራቅ አፍሪካ /አፍሪካ ኦሪየንታሌ ኢታሊያና/ አለው። ይህ ስም አጠራር ኢትዮጵያ የሚለውን ቃል ከምድር ገጽ ለማጥፋት ነበር። ለውጪዎች፣ ኢትዮጵያ የሚለው ስም ይከብዳቸዋል። ዓረብ ሀበሽ ይላል። ፈረንጅ አቢሲንያ ይላል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስሙ መጠቀሱ ይቀፋቸዋል፤ በተለይም ለእንግሊዞች። ሞሶሊኒ የሞከረው በዚሁ ስም አጠራር የተጨነቁትን ሁሉ ለመገላገል ነበር።

ደግሞም ልዩ፣ ልዩ አዋጅ አወጣ። ለሊብያ፣ ለኤርትራና ለሶማሊያ ጭምር በማስመሰል፣ ለሁሉም ቅኝ ግዛቶች ፖሊሲ ቀረጸ። ነገር ግን ዋና ዓላማው ኢትዮጵያ ነበረች። አንድ ሕግ ያወጣል፤ እሱ ሳይሠራ ሲቀር ሌላ ያስደግመው ገባ። በዚህ ዓይነት አንዱን ሕግ ሌላው እያፈረሰው፣ አንዱን ፖሊሲ ተከታዩ እየጣሰው ሄደ፤ ዝብርቅርቁ በዛ። ችኩሉ የጣልያን መንፈስ ከጊዜው አስቸኳይነት ጋር እየተጣመረ በጥድፊያ ላይ ጥድፊያን ተከተለ። በመሆኑም ዝግ ብሎ የሚራመደውን የኢትዮጵያን ሕዝብ አመለካከት ለመለወጥና ከእሱ ሥርዓት ውስጥ ለማስገባት አቃተው። ኢትዮጵያን ከእሱ ሥርዓት ማግባት ሲያቅተው፤ እሱ ራሱ ወደ ኢትዮጵያ ባህልና ሥርዓት መግባት ያዘ። ከዚህ ድምዳሜ የሚያደርሱትን ነገሮች ቀጥሎ እንመለከታለን።

ጣልያኖች ለጦርነት ቸኰሉ። በፖለቲካ ተፅዕኖ ቀጥለው ቢሆን ኖሮ ብዙ ጥቅም ያገኙ ነበር። ምክንያቱም በዚያን ጊዜ በነበረው ዓለም አቀፍ ሁኔታ ኃይላቸው ሚዛን አግኝቶ ስለነበር፣ ብዙ ተቀናቃኝ አልነበረባቸውም። የእንግሊዞችን ሽምግልና ተቀብለው ቢሆን ኖሮ፤ ቅጥያ ሊያገኙ ግዛትም ላያጡ ይችሉ ነበር። ኢትዮጵያም ይህንን ዓይነቱን ተፅዕኖ ለመቋቋም አቅም አታገኝም ነበር። የዓለም ኅብረተሰብም ጣልያንን ግፈኛ አድርጐ አይቆጥራትም ነበር። ኢኮኖሚዋ ተበላሽቶ አዘቅት አያወርዳትም ነበር። ምናልባትም በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ ከጀርመን ጐን እንድትቆም የሚያስገድዱአት የፖለቲካ ሁኔታዎች አይፈጠሩም ነበር። ምናልባትም የኢማኑኤል ንግሥና ወድቆ የሳቮይ ሥርወ መንግሥት አይነቀልም ነበር። እንኳን አልሆነ እንጂ፣ ያ ዓይነቱ ሁኔታ ለኢትዮጵያ ከጦርነቱም የከፋ ይሆንባት ነበር።

በጦርነቱ ጊዜና ድል ከአደረገችም በኋላ ጣልያን በኢትዮጵያውያን ላይ የጭካኔ ሥራ አካሄደች። ዓለም ያወገዘውን ዓይነት የአረመኔነት ግብር ሠራች።[1] በዚህ ምክንያት የዓለምን ሕዝብ ድጋፍ አጣች። ኢትዮጵያውያንን ከእልህ አስገብታ ጦርነቱ ከሽምቅ ፍልሚያ ውስጥ እንዲገባ አስገደደችው። በሌላ አነጋገር በውጭ አገር የሚካሄደውን የኢትዮጵያን የፖለቲካ አቅዋም

አጠናከረች። በሀገር ውስጥ ደግሞ የአርበኝነት ሥራ በገዛ ራስዋ ላይ አቋቋመች፣ አበረታች።

ጣልያን በሕዝቦች መካከል የዘር ልዩነት አነሳች። ኦሮሞውን፣ ትግሬውን፣ ጉራጌውን፣ ሱማሌውን፣ ወላይታውን ሌላውንም ከሰማንያ በላይ በሚሆነው ጐሣ መካከል የርስበርስ መጠላላት ሥራ ቀሰቀሰች። ዓላማዋ የቅኝ ግዛትን በምንም ሁኔታ የማይቀበለውን አማራውን ለማስጨረስ ነበር።[2] ነገር ግን ሳይሠራ ቀረ። የኢትዮጵያ ህዝብ በጐሣ ቢለያይም በሀገር ጉዳይ አንድ መሆኑን በግብር እያረጋገጠ ሲሄድ፣ የኢጣልያ ድካም መና ሆነ።

የዘር ልዩነትን በኢትዮጵያውያን መካከል እያራመደች፣ ጣልያናውያን ንጹሕ ደም ያላቸው ስለሆኑ ከሌላው ዘር ጋር እንዳይቀላቀሉ ከለከለች። በመኖሪያና በሥራ ቦታ፣ በመዝናኛና በአደባባዮች እንዳይቀላቀሉ አደረገች።[3] ይህ ድርጊት ኢትዮጵያውያን የራሳቸውን ጉዳይ በራሳቸው ዘዴ እንዲሠሩ ምቹ ሁኔታዎችን ፈጠረ። እንዲሁም በወቅቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ በእነሱ ላይ ያደረበትን ጥላቻ፣ ንቀት ይበልጥ አከረረው። የጣልያን የአስተዳደር ጉድለት ገሐድ ወጣ።

ሌላው በኢትዮጵያ ሕዝብ ልዩነት ለማነሳሳት የሞከረችበት መንገድ ኃይማኖት ነበር። በክርስቲያኑ ላይ እስላሙን ለማነሳሳት ልዩ ጥረት አደረገች። እስላሞች መጨቆናቸውን በመግለጽ ብዙ ወተወተች። በጣልያን አገር ከካቶሊክ ተከታዮች በስተቀር ሌላው የፖለቲካ ቦታ እንደሌለው እንዳልታወቀባት ሁሉ፣ በአፍዋ ይህንን ዓይነት የኃይማኖት ቁርሾ እየቀሰቀሰች፤ በቀኝ እጅዋ ጳጳሳት እየገደለች፣ አብያተ ክርስቲያናት እያቃጠለች፣ ካህናትንና መነኮሳትን እየፈጀች፤ በግራ እጅዋ ደግሞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን የሚያጠናክር የሚመስል ተራ ሙከራ አደረገች። ለጳጳሳት ሹመት ሰጠች፣ ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን በተመለከተ ሕግ አወጣች።[4] የእስክንድርያ ቤተክርስቲያን ድርጊቱን አወገዘች። ከባንዳና ከሥርዓቱ ተጠቃሚዎች በስተቀር፣ ሕዝብ አዳዲሶቹን ጳጳሳት እንደርኩሳን አድርጐ አያቸው። ይህም ሳይሠራ ቀረ።

ጣልያኖች መሬት ለመያዝና የእርሻ ሥራዎች ለማቋቋም ተጣደፉ። ጐንደር ዳባት ላይ፣ ሸዋ ሆለታ ላይ፣ አርሲ ጐንዴ ላይ፣ ሐረርጌ ሂርና ላይ ታላላቅ እርሻ አቋቋሙ። ብዙ ገንዘብ ወጭ አደረጉ። እሱም የተጠበቀውን ጥቅም ሳያስገኝ ቀረ። በኢትዮጵያውያን ገበሬዎች ዘንድ የመሬት ንጥቂያ መሆኑ በግብር ስለተረጋገጠ ተቃውሞን አጠናከረ።[5] እንደሌላው ሁሉ በዚህም ረገድ የተደረገው ሙከራ ውጤቱ መከራ ሆነ።

አስተዳደሩን በዘር ልዩነት ላይ በተመሠረተ አከፋፈል ቀየሰችው። ትግሬ ወደ አሥመራ ተከለለ፤ አማራ፣ ጐንደር፤ ሱማሌ፣ ሞቃድሾ፤ ኢሣና አፋር ሐረር፤ ኦሮሞ-ሲዳማ፣ ጂማ ሆነ። በነባሩ የአገር ስም የሚጠራው ሸዋ



ብቻ ሆነ። እሱንም ለመገንጣጠል ልዩ ጥረት ተደረገ። ይህም የተጠበቀውን ያህል ሳይረዳ ቀረ።

በመስከረም ወር 1930 ዓ.ም ጣልያኖች ፖሊሲአቸውን መለወጥ ጀመሩ። በግራዚያኒ ቦታ ዱክ ደ አዎስታ እንዲተካ ታሰበ። ከዓላማዎቹ አንዱ የጣልያን ንጉሣውያን ወገኖች አስተዳደር፣ ከፋሽስቶች የጭካኔ ሥራ የተለየ መሆኑን በግብር ማሳየት ነበር። ንጉሡ ኢማኑኤል ጦርነቱን እንዳልፈቀደ፣ ጳጳሱ መርዙን እንዳልባረከ፣ መሣፍንቱ በጦርነቱ እንዳልተሳተፉ ሁሉ!

ግራዚያኒ እንዲሻርና በምትኩ የአስተዳደር ችሎታ ያለው አንድ መሥፍን እንዲሾም፤ ሞሶሊኒ ለንጉሡ ለሣልሣዊ ኢማኑኤል ሃሳብ አቀረበ። ከሁኔታው አስፈሪነት የተነሣ የጣልያንን ዘውድ የሚያረክስ እንዳይሆንበት ቢሰጋም፤ ንጉሡ ከጳጉሜ 4 ቀን 1929 ዓ.ም ጀምሮ ሲያውጠነጥን የቆየውን ሃሳብ ስለተቀበለው ዱክ አሚዲዮ ደ አዎስታ ተሾመ። ታህሣሥ 17 ቀን 1930 ዓ.ም /ዲሰምበር 26 ቀን 1937/ አዲስ አበባ ገባ። መስፍኑ ከሞሶሊኒ የተሰጠውን መመሪያ በድጋሚ ለማስታወስ፦

1ኛ. ጣልያኖች ከቅኝ ግዛት ሰዎች መቀላቀላቸው ውርደት ስለሆነ ለጣልያን ንጹህ ዘር ጥበቃ እንዲያደርግ።

2ኛ. ስለጦርነቱ ሮም የሚደርሰው ሪፖርት የተጋነነ ስለሚመስል እርግጠኛውን እንዲያስታውቅ።

3ኛ. የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት በገንዘብ ረገድ ራሱን እንዲችል እንጂ ከጣልያን ሀገር ገንዘብ እንዳይጠይቅ።

4ኛ. በኃይማኖቶች ምክንያት የሚታየውን ችግር እንዲያቃልል።

5ኛ. አገረ ገዥዎች ሙሉ ሥልጣን እንዲኖራቸው እንዲያደርግ ነበር።

ነገር ግን ባዲሊዮ ተሸሮ የዱካ ደ አዎስታ መሾም በአርበኞች ስሜት ላይ አንዳች ልዩነት እንዳልፈጠረ ተመልክተናል።

እሱም አዲስ አበባ እንደገባ ሁኔታዎችን ለማሻሻል ሞከረ። ሕዝብን ለማረጋጋትና ጦርነቱም ሥርዓት እንዲይዝ ለማድረግ ሞከረ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለጣልያን ዓላማ እውነተኛ ትምህርት አግኝቶ ነበርና አዲሱ ሽንገላ ሳይቆነጥጥ፣ ሥር ሳዩዝ ቀረ።

በጣልያኖች ዘንድ ባለምዋልነት ለማግኘት ሌጦአቸውን ገልብጠው የነበሩትና፤ በእስክንድርያው ፓትርያርክ ከሹመታቸው እንዲሻሩ፣ ክህነታቸው እንዲፋቅና ከቅድስት ማርቆስ ቤተክርስቲያን የተለዩ እንዲሆኑ የተወሰነባቸው አቡነ አብርሃም ሞቱ። ዱክ ደ አዎስታ በዚህ አጋጣሚ በመጠቀም፣ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ አክብሮት የነበራቸውን የአዲስ ዓለሙ የሐዲስ መምህር፣ አለቃ እሸቱን ሊቀ ጳጳስ ሆነው እንዲመረጡ አደረገ። እሳቸውም ጳጉሜ 5 ቀን 1931 ዓ.ም በፒየሮፍራንክ ሰብሳቢነት በተካሄደ ጉባዔ

ተመርጠው፤ መስከረም 7 ቀን 1932 ዓ.ም ሥርዓተ ጵጵስና ተከበረላቸው። አቡነ ዮሐንስ ተባሉ።

ዱክ ደ አምስታ አሜደዮ ዲ ሳቮያ በሚል የማዕረግ ስም፤ ሐምሌ 21 ቀን 1934 ዓ.ም ስለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሕግ አወጣ። ሕጉም ስለሊቃውንት ጉባዔ፣ ስለ ሊቀ ጳጳሳት፣ ስለ ጳጳሳት፣ በጳጳሱ ስለሚታዘዙ ሹሞች፣ ስለ ቤተክህነት ዋና ፀሐፊ፣ ስለ እጨጌ፣ ስለ ሊቃነ ካህናት፣ ስለ መንፈሳዊ ምክር ጉባዔ፣ ስለ ሀገረ ስብከት አከፋፈል፣ ስለ ሀገረ ስብከት መሻሻል፣ ለጣልያን ንጉሥና ለወራሾች ስለመታዘዝ መሐላ፣ ስለ ቤተክርስቲያን ክብር፣ ስለ ቤተክርስቲያን ሥነ ሥርዓት፣ ስለ ልብሰ ተክህኖ፣ ለሊቀ ጳጳሳቱ ስለሚሰጠው ክብር፣ ለእጨጌው ስለሚሰጠው ክብር፣ ለየአውራጃው ጳጳሳት ስለሚሰጣቸው ክብር፣ ስለማተሚያ ቤትና ስለተማሪ ቤት፣ ስለዜና ቤተክርስቲያን ጋዜጣ፣ ስለ ኃይማኖት ትምህርት ደንብ፣ ስለ ኃይማኖት ትምህርት ቤት፣ ስለገንዘብ ሥራ አካሄድ፣ ስለ ገዳማት እና አብያተ ክርስቲያናት አለቆች፣ ስለ ሥልጣነ ክህነት አሰጣጥ፣ ስለአዳዲስ ቤተክርስቲያን ሥራ፣ ስለ ኢየሩሳሌም ገዳማት አለቆች አሿሿም፤ በጠቅላላው ሠላሳ ስድስት አንቀጽ ነበረው።

በደንቡ ውስጥ የኢጣልያ ሥራ በትክክል ተጠብቆአል። የአጠባበቁም ሥልት ለቤተክርስቲያኗ ለመጥቀም ሲባል የተደረገ እንዲመስል ጥንቃቄ ተደርጕአል። ቤተ ክርስቲያኒቱን ለመጥቀም እንዲመስል በአዋጁ ውስጥ የተዘበዘበው ነገር ረጅም ነው። ዝርዝሩን ከአዋጁ መመልከት ነው። እኛ ግን የጣልያን ሥልጣን ለመጠበቅ የተደረገውን ጥንቃቄ እንዳስሳለን።

አንቀጽ 2፡- በሊቃውንት ጉባዔ የሚቀመጡት አባላት ቁጥር በቄሣር እንደራሴ ይወሰናል፤

አንቀጽ 3፡- ዋና ፀሐፊው በቄሣር እንደራሴ ይሾማል፤

አንቀጽ 5፡- እጨጌው በቄሣር እንደራሴ ይሾማል፤

አንቀጽ 6፡- የመንፈሳዊ ምክር ቤት መማክርት በቄሣር እንደራሴ የሚሾሙ ናቸው፤

አንቀጽ 7፡- አሥሩ ሀገረ ስብከቶች ሸዋ፣ ኤርትራ፣ አማራ፣ ጐጃም፣ ወሎ፣ ወለጋ፣ ወላሞ፣ ሐረር፣ አዲስ አበባና ደብረ ሊባኖስ ናቸው፤

አንቀጽ 10፡-ጳጳሳት በሊቃነ ጳጳሳት ፈቃድ፣ በቄሣሩ እንደራሴ አዋጅ ይሾማሉ፤ ኤጴስ ቆጶሳት እንዲመረጡ የሚያዘው፣ ከተመረጡም በኋላ የሚሾመው የቄሣሩ እንደራሴ ነው፤

አንቀጽ 11፡- የቤተክርስቲያን ሹማምንት ሁሉ ሲሾሙና ሥራቸውን ሲረከቡ ለቄሣርና ለወራሾች ታማኝ ሊሆን ይምላሉ፤

አንቀጽ 13፡- የቤተክርስቲያኒቱ ሥርዓትና ደንብ የቄሣሩ እንደራሴ አይቶት ይወጣል፤



አንቀጽ 14፡- ልብሰ ተክህኖ የቄሣር እንደራሴ ከአየው በኋላ ይወጣል፤

አንቀጽ 20፡-የኃይማኖት ትምህርት ደንብ የቄሣሩ እንደራሴ አይቶ ይቀበለዋል፤

አንቀጽ 23፡- ስለገንዘብ አያያዝና ስለ ሥራ አካሄድ የተለየ ደንብ ይወጣል፤

አንቀጽ 27 እና 28፡- አገረ ገዥው የቤተክርስቲያን አለቃና የገዳም መምህር፣ አማካሪዎች ይሾማል፤

አንቀጽ 33፡- አዲስ ቤተክርስቲያን እንዲሠራ የሚፈቅድ አገረ ገዥው ነው፤

አንቀጽ 34፡- እየሩሳሌም ላሉ ገዳማት ሁሉ የቄሣሩ እንደራሴ መምህርን ይሾምላቸዋል፤ መባሉን ልብ እንበል።[6]

ይህ ሁኔታ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ተከታዮች ዘንድ ከፍተኛ ግንጋኄ ፈጠረ። የጣልያን ፍላጐት የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን በልዩ ልዩ ዘዴ ጐትቶ፤ ሮም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ሥር ለማስገባት ስለመሆኑ ጥርጣሬ አሳደረ። ለዚህም አራት ዋና ዋና ምክንያቶች ነበሩ። ከእነዚህ አንደኛው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንና በሮም ካቶሊክ መንበር መካከል የነበረው ታሪካዊ ግንኙነት ነበር። ሁለተኛ የሮም ካቶሊካዊ ሊቀ ጳጳስ አባ ፓየስ 11ኛ፣ ለኢትዮጵያ መደብደቢያ የተዘጋጀውን የጦር መሣሪያ መባረካቸው። የእስክንድርያ መንበረ ጵጵስና ከውግዘት የደረሰው፣ -የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ የነበሩት አቡነ ቄርሎስ ሮም ሄደው ከካቶሊኩ ሊቀ ጳጳስ ጋር ከተነጋገሩ በኋላ በመሆኑ ነው። አራተኛ ደግሞ አዲስ አበባ ላይ ስለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የወጣው ሕግ የጣልያንን የበላይነት ማጠናከሩ ነበሩ። ሁኔታውን በትክክል ለመረዳት እነዚህን አራት ነጥቦች አንድ በአንድ መመርመር ያስፈልጋል።

1ኛ. ከቀድሞ ጀምሮ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንና በሮም ካቶሊክ መንበር መካከል ከፍተኛ ቅራኔ አለ። ልዩነታቸው ለ/በፖለቲካ አመለካከት በቀላል የሚጠናቀቅ አይደለም። ዝርዝሩን ለማወቅ በአለቃ አያሌው ታምሩና በአባ አየለ ተክለሃይማኖት መካከል የተካሄደውን ክርክር ማጥናት ያስፈልጋል። ከዋና ዋናዎቹ አንዱ የክርስቶስ ልደት ሦስት ነው፣ ሁለት ነው የሚል ሲሆን፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በሁለት ልደት ታምናለች። የሮም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ይህንን አታምንም። ሌላው ክርክር በክርስቶስ ሰውነትና መለኮትነት ላይ የተመሠረተው ደግሞ፤ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ባህርይ መለኮትና ባሕርይ ትስብዕት ዳግመኛ በማይለያይ ሁኔታ አንድ ሆነዋል ትላለች። እምነትዋንም እውነተኛ /ኦርቶዶክስ/ ተዋህዶ ትለዋለች። የሮም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን በዚህም አታምንም። ሦስተኛው ክርክር ልለ ሥጋ ኢየሱስ ነው። የኢትዮጵያ

ቤተክርስቲያን በጊዜ ቅዳሴ ሕብስቱ ወደ ሥጋነት፣ ወይኑ ወደ ደምነት ይለወጣል ብላ ታምናለች። ስሙንም ሥጋ ኢየሱስ፣ ሥጋ ወደሙ ትለዋለች። የሮም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን በዚህም አታምንም። ከዚህ በተረፈ የሥልጣን ጉዳይም አለ። የሮም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ላይ ጥላዋን ለመጣል ትፈልጋለች። የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ደግሞ አጥብቃ ትከላከላለች።[7]

2ኛ. አባ ፓየስ 11ኛ ለኢትዮጵያውያን መፍጃ የተዘጋጀውን መርዝ ጋዝ፣ ቦምብ፣ መድፍና መትረየስ ቀርበላቸው በአደባባይ መባረካቸው ሌላው ጉዳይ ነው። ከዚህም ጋር ቀደም ብለው ወደ ኢትዮጵያ በመግባት ሚሲዮናውያን የሠሩት ደባ በኢትዮጵያውያን ዘንድ የታወቀ መሆኑ ነው። ይህ ገሀድ ስለሆነ ማስረጃ ማቅረብ አይጠይቅም። ከአድዋ ጀምሮ በገሀድ ሲታይ የኖረ ነው።[8] በአምስቱ ዓመት ወረራ የባሰ እንጂ የተሻለ አንዳች ነገር አልታየም።

3ኛ. የአቡነ ቄርሎስ ወደሮም እንዲሄዱ መገደድና፣ የእሳቸውም በሮም ካቶሊክ መንበረ ጵጵስና ባለሥልጣኖች ጋር ተነጋግረው ሳይስማሙ መቅረት ነው። እሳቸው ሳይስማሙ የቀሩት በሥልጣን ጥያቄ ጭምር እንጂ፣ በእምነት ልዩነት ብቻ አልነበረም። ቢሆንም ሊቀ ጳጳሱ ያልተቀበሉትን ነገር ካህናቱም፣ ምእመናኑም መቀበል አልቻሉም። በዚህ ላይ ደግሞ የመንበረ ማርቆስ ዘአለ እስክንድርያ ውግዘት ተጨመረ።[9]

4ኛ. ዋናው ጉዳይ ዱክ ደ አዎስታ ስለ ቤተክርስቲያን አስተዳደር ያወጣው አዋጅ ሆነ። እሱም ቀደም ብሎ በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ የተነገረ ስለሆነ መድገም አያስፈልግም።

ጣልያኖች ከዚህ ጠቃሚ ከሚመስል እርምጃ በአንጻሩ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አብያተ ክርስቲያናትን ማቃጠልና ማጥፋት ቀጠሉ። ለማርከስ፣ በየሄዱበት ጦራቸውን የሚያሠፍሩት ከቤተክርስቲያን ውስጥ ሆነ። ለማስረጃ ያህል በጉንደር ከተማ የሩፋኤልን ቤተመቅደስ የፈረስ ማሠሪያ አደረጉት። ቡልጋም ጊዮርጊስን እንደዚሁ አድርገዋል። ጦሩ ሲንቀሳቀስ ደግሞ አቃጥሎት ይሄዳል። በድምሩ 2,000 ቤተክርስቲያኖች አቃጠሉ። ከዚህም ጋር እጅግ ብዙ መጻህፍት፣ ንዋየ ቅድሳት፣ ቅርሳቅርሶች ዘረፉ፣ አጠፉ። የአርባዕቱ እንስሳን ቤተክርስቲያን አፍርሰው ማገዱት። የሠለስቱ ምዕትን ጽሕፈት ቤት አደረጉት። ፋሲለደስ ቤተክርስቲያንነቱ ቀረ።

በሦስተኛው አንጻር ደግሞ የራሳቸውን የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ለማስፋፋት ጥረት አደረጉ። በአዲስ አበባና በሌሎችም ከተሞች ቤተክርስቲያኖች ሠሩ። ይህ ሁኔታ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን እምነት ተከታዮችን አስቆጣ። የካቶሊክ እምነት ተከታይ የሆኑ ኢትዮጵያውያንንም አበሳጨ። ለምሣሌ በጉንደር አባ ካሣን ናላቸውን አዙሮ



አሳበዳቸው።[10] እስላሞችንም አስገነገነ። እንዲያውም ከክርስቲያኖች ጋር አቀራረባቸው።

ሌላው ችግር ቀደም ብሎ በብዙ ሽንገላ ከጉኑ እንዲቆሙ ያደረጋቸውን የኢትዮጵያ መሣፍንትና መኳንንት ማስተዳደር ሆነ። ለብዙዎች ደመወዝ ቢቆረጥላቸውና ባለምዋልነት ቢሰጣቸውም፣ የወገኖቻቸው እልቂትና ሰቆቃ፣ የጣልያኖች ቅጥፈት የኀሊና ዕረፍት እየነሣቸው ሄደ። በየአደባባዩ እየቆሙ በገዛ ሕዝባቸው መንጓጠጥ ሰለቻቸው። ምነው? ለምን? እያሉ መጠየቅ አመጡ። በአንዳንድ ጉዳይ አለመስማማታቸውን መግለጽ ጀመሩ። እነሱም በተራቸው ወደ እሥር ቤት ተጋዙ። ታላቁ ታማኝ ልዑል ራስ ኃይሉ ተክለሃይማኖትም አልቀረ። ምህረት እንደተደረገላቸው ማረጋገጫ የተሰጣቸው እነ ራስ ሥዩምና ራስ ጌታቸውም ከዚያው ገቡ። በዚህም በኩል የተደከመው ድካም መና ሆነ።

የጣልያኖች ሌላው ችግር በእነሱ ዘር፣ ማለትም፡- በጣልያናውያን፣ እና በኢትዮጵያውያን መካከል ያለው ግንኙነት የሚያሳስባቸው ሆነ። ጣልያናውያን ከኢትዮጵያውያን መደቀላቸው የዘር ሥጥመት እንደሚያመጣ አድርገው በተገነዘቡ ጊዜ፣ ጥቁርና ነጭ በምንም እንዳይገናኝ ሕግ አወጡ። ኢትዮጵያውያን ተቆጡ። ለነገሩ ጣልያኖች ሕጉን ሳያከብሩ ቀሩ፣ ሹማምንቱና ወታደሮቹ እንደየደረጃቸው ከኢትዮጵያ ሴቶች ጉያ አንወጣም አሉ። ከአሥር ሺህ የማያንስ ክልስ ተወለደ። ይህ ነገር ሊታገድ እንደማይችል በተረዱ ጊዜ፣ ሕጉን በሕግ ሳይሆን በአሠራር ሻሩት። ጣልያንና ሀበሻ ይበልጡኑ ተቀላቀሉ። ዝብርቅርቁ ወጣ።

ጣልያኖች በቀድሞው ሥርዓት በሕዝብ ላይ ከብዶ የነበረውን ነገር ማቃለል የሚያስችል እርምጃ መውሰድ ደጋፊ እንደ ሚያስገኝላቸው ቀደም ብለው በጥናት አረጋግጠው ነበርና፣ አገር እንደገቡ በዚህ ረገድ ፈጣን እርምጃ ወሰዱ። ባሪያ ያለምንም ጥያቄ ለዘለቄታ ነፃ ወጣ። ለጉልተኛ፣ ለመልከኛና ለሻለቃ ሁዳድ ማረስ፣ ማር መቅዳት ቀረ። በአማራው አገር ሲሦ ለአንጋሽ፣ ሲሦ ለቀዳሽ፣ ሲሦ ላራሽ የሚለው ሥርዓት ፈረሰ።

ነገር ግን ይህ ሥርዓት ተሸክሞት የነበረው አበሳ ወደ ጣልያን መንግሥት ወደራሱ ዞረ። ናላውንም አዞረው። ጣልያን ራሱ የሠራውን ሥርዓት ከመጋቢት 1931 ዓ.ም ጀምሮ በአዋጅ ከማፍረስና የቀድሞውን ሥርዓት እንደገና መልሶ ከመገንባት ገባ። ባለሪም አምሾ እንዳይቀበል፣ የመስቀል መሬቶች እንደ ቀድሞው እንዲሆኑ ተደረገ። አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ደመወዝ ይወጣላቸዋል ተባለ። የቤተክርስቲያን አለቆች ስለኃይማኖት ጉዳይ ዳኝነት እንዲያዩ ተፈቀደ። መሬት እንደ አገሩ ሕግና ልማድ የሕዝብ መሆኑን የጣልያን መንግሥት በአዋጅ አወቀ። ጭቃ አበል እንዲቀበል ተፈቀደ። ዳኝነትም፣ አፈርሳታም እንደ ጥንቱ ሆነ።[11] ይህ ሁኔታ በነባሩ

ሥርዓት ተጠቃሚ የነበሩትን ወገኖች እምብዛም ሲያስደስት፣ ሌሎች ደግሞ ተቃሎላቸው የነበረውን ሸክም መልሶ ስለ ቆለለባቸው ይበልጥ አስቆጣቸው።

በእነሱ አመለካከት ሽፍታ ከነበረው ጋር ያጋጠማቸውን ቅራኔ በንግግር ለመፍታት ሞከሩ። ከአርበኛው የቀረበላቸው የመደራደሪያ ነጥብ ከባድ ሆነ። ነገር ግን በገዛ እጃቸው የጀመሩት ስለሆነ በጉዳዩ መግፋት ግድ ሆነባቸው። አፈፃፀሙ በአርበኞች ጥያቄ ሳይሆን በጣልያን መንግሥት ችሮታ የተፈጸመ እንዲመስል እያደረጉ፣ አንዳንድ የእነሱን ጥቅም የሚቃረን ሥራ ሠሩ። እሥረኞች ተፈቱ። ቤታቸው፣ ንብረታቸው ተመለሰላቸው። የዳኝነት ሥራ ከኢትዮጵያውያን እጅ ተመልሶ ገባ። ጣልያናውያን ለሚኖሩበት ቤት ኪራይ ከመክፈል ገቡ። በቅኝ ግዛት ታሪክ ውስጥ አድርገውት የማያውቁትን ሹመት ለኢትዮጵያውያን ሰጡ። የሠራተኛን ደመወዝ ከፍ አደረጉ። ለአስተርጓሚ በወር ከ55-150 ሊሬ መክፈል ጀመሩ። ለአርበኛውም ደመወዝ መክፈል ስንቅ መስጠት ያዙ። ገንዘባቸውን በልዩ ልዩ መንገድ ረጩ። የኢትዮጵያውያንን ልብ በገንዘብ ለመግዛት የሚችሉ መስሎአቸው የነበረው ይኸ አመለካከት ለመጀመሪያው ጊዜ ጥቂት ቢያግዛቸውም፣ ሳያዛልቃቸው ቀረ።

ሌላው ሙከራቸው አንዳንድ የልማት ሥራዎች የሚያካሂዱት ኢትዮጵያን ለማሳደግ፣ ኢትዮጵያን ለማልማት እንደሆነ አድርጎ ማሳየት ነበር። ተሐድሶ ኢትዮጵያ በሚል ጋዜጣና የሮማ ብርሃን በሚል መጽሔታቸው ድልድይ፣ የመንገድ ሥራ ያሳዩ ጀመር። እሱን እየፈጁ መሬቲቱን የሚያለሙት ለማን ጥቅም እንደሆነ ለማወቅ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጊዜ አልወሰደበትም።

የባንዳ አስተዳደርም በበኩሉ ችግር ፈጠረ። በመጀመሪያ ደረጃ ገበሬ ከጦር ሜዳ ተፈጥሞ ወጣ። ባንዳም ይከዳ ጀመር፤ ያለውም ከልቡ የማይዋጋ ሆነ። በደመወዝ መንቀሳቀሱ ቀረ። የደንብ ልብስ አስፈለገው። ወጭው እየበዛ፣ አገልግሎቱ እየተቀነሰ፣ ታማኝነቱ እየቀዘቀዘ ሄደ። ለአርበኞች ደመወዝ መቆረጡ፣ ክብር መሰጠቱ፣ እንክብካቤ መደረጉ አስቆጨው።[12] ይህ አሠራር የአርበኛውን ልብ በማደንደንና የባንዳውን ቅስም በመስበር ጣልያንን ይበልጥ ጐዳው።

ባለቅኔ የሚቀኘው፣ አዝማሪ የሚያዘምረው፣ አልቃሽ የምታሞሸው ስለጣልያን ጭካኔ፣ ፈሪነት፣ አታላይነት ሆነ። በአንፃሩ ደግሞ የአርበኞችን ጀግንነት ያሞግሱ ጀመር። ጠንቋዩ፣ ትንቢት ተናጋሪው፣ ባህታዊው የሚናገረው ስለጣልያን በንኖ መጥፋት ሆነ። የጣልያን ፕሮፓጋንዳ በጋዜጣ መፃፉ፣ በመጽሔት መውጣቱ፣ በሬዲዮ መነገሩ አንዳች የማይፈይድ ሆነ። ጣልያኖች ከአለቃ እስከ ጭፍራ ግራ ገባቸው።

ሙሶሊኒ ከሂትለር ጐን መቆሙን በገለጸ ጊዜ፣ የሮማው ራስ ዞረ። ከሥልጣን የመውረዱ ጉዳይ ደግሞ አዲስ አበባ የነበሩትን ጣልያኖች



ስላስደነገጠ፣ በበርበራና በሱዳን በኩል ጦርነት ከፈቱ። የጦርነቱ ሚዛን ወዲያው በእነሱ በራሳቸው ላይ አዘነበለ። ከአጥቂነት ወደ ተከላካይነት ዞሩ። የሰሜን አፍሪካው ጦርነት፣ የሰዊዝ ካናል በእንግሊዞች መዘጋት፣ ኢትዮጵያ ላይ የፈሰሰውን ጣልያን ከእናት አገሩ ቆረጠው።

ዱክ ደ አዎስታ እና ናዚ ሁኔታውን በፖለቲካና በፈሊጥ ለመያዝ ሞከሩ። በኢትዮጵያ ባሕል መሠረት ሹመት ሰጡ። በደብረ ብርሃን አቶ ስሙ ንጉሥ፣ በጐንደር ደጃዝማች አያሌው ብሩ ራስ ተባሉ። ለብዙዎች የደጃዝማችነትና የፊታውራሪነት ማዕረግ ተሰጠ። ነገር ግን አንዳች አልጠቀመም።

ጣልያን ከውድቀት የደረሰችውና ኢትዮጵያን እንደ ቅኝ ግዛት ለመያዝ የተነሳችበትና የተዋደቀችለትን ግብ ያጣችው፣ በአብዛኛው የተሳሳተ ሕግ በማውጣትና የተሳሳተ ፖሊሲ በመከተል ጭምር ነው። እንደ አጀማመሯ፣ በኃይል ዝግጅትና በጦር አሰላለፍ ኢትዮጵያ ከምንዋም አትደርስም ነበር።



የጣልያን ምስራቅ አፍሪቃ አስተዳዳሪ ልዑል ደ ኤኦስታ።

ጣልያን፣ ኢትዮጵያን ለመያዝ የነበራት ጉጉት እጅግ ከፍተኛ ስለ መሆኑ፣ ሞሶሊኒ በምሥጢር ለባዶሊዮ በጻፈለት ደብዳቤ ብዙ ምክር ከሰጠው በኋላ "...የሆነው ሆኖ፣ ወይም ያለቀው አልቆ ድሉ የኛ መሆን አለበት" ማለቱ ያንኑ ያረጋግጣል።[13] ይህ ቁርጠኛነት ምንም ሳይበርድ እስከ መጨረሻው ድረስ ቀጠለ። የጣልያን ጦር ያስመሰልችት የኢትዮጵያን ሕዝብ እየፈጀና ራሱም እያለቀ እስከ መጨረሻው ተጋደለ። ነገር ግን ያ ሁሉ የጣልያኖች ድካም፣ በመሪዎቹ ደካማ አመለካከት መና ሆኖ ቀረ።

እርግጥ ዋናው ስህተታቸው፣ የአድዋ ውድቀታቸውን በመርሳት ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት ለመያዝ እንደገና መሞከራቸው ነው። ከዚህ



የጣልያን ምስራቅ አፍሪቃ አስተዳዳሪ ልዑል ደ ኤኦስታ።

ስህተታቸው ተምረው ወደፊት ኢትዮጵያን ከመተናኮል ይታቀቡ ይሆን? እንጃ!


**<u>ማጣቀሻ ፅሑፎች</u>**

1. *ገሪማ ታፈረ፣ ጐንደሬ በጋሻው፣* ገጽ 28፣ 35፣ 65፣ 72፣ 152፣ 175፣ 205፣ 206::
2. ዝኒ ከማሁ፣ገጽ 23-25::
3. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት፣* ገጽ 186-190::
4. *ገሪማ ታፈረ፣* ገጽ 83-102::
5. Alberto Sabacchi, *Ethioipia under Muossolini*, pp.101-114.
6. *ገሪማ ታፈረ፣* ገጽ 96-101::
7. አያሌው ታምሩ፣ *መች ተሰመደና ከተኩላ ዝምድና*::
8. ታደሰ ዘወልዴ፣ *የአባላሸኝ ዘመን፣* ገጽ 27-31::
9. *ገሪማ ታፈረ፣* ገጽ 83::
10. ዝኒ ከማሁ፣ገጽ 71-72::
11. ዝኒ ከማሁ፣ገጽ 223-225::
12. ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣* ገጽ 291-294::




# ምዕራፍ አርባ ዘጠኝ
# የኢጣልያ የምሥራቅ አፍሪካ አስተዳደር

በ1920 ዓ.ም አካባቢ ጣልያን በሊቢያ፣ በኤርትራ፣ በሶማሊያ ላይ የነበራት ይዞታ የተረጋገጠበት ጊዜ ነበር። እነዚህን አገሮች የያዘችበትን መንገድ ጥቂት መመርመር፣ ስለቅኝ አገር አያያዝ የነበራትን ሥልት ያስረዳል።

ከሁሉም ያስቸገራት ሊቢያን መያዝ ነበር። አገሩን ከቁጥጥር ሥር ማዋል የቻለችው ከብዙ ጦርነት በኋላ ነበር። ለጦርነቱም ከጣልያን አገር የሚጫነው ወታደር የማይበቃ ሆኖ፣ ከኤርትራና ከሶማሊያ ብዙ ወታደር እየቀጠረች ማጋዝ ነበረባት። ግራዚያኒም በጨካኝ ሥርዓት ሕዝብን መፍጀት የሚቻልበትን ዘዴ ያጠናው ከዚያ ነበር። ጣልያን ከዚህ ሁኔታ በኃይል ስለመጠቀም ልምድ አግኝታለች።

ኤርትራን ግን የያዘችው በአብዛኛው የሀገሩን ባለሥልጣኖች በመሸንገል ነው። መዋጋት የነበረባት ከትግራይ እየተወረወረ ከሚሄደው፣ በራስ አሉላ ከሚመራው ከኢትዮጵያ ጦር ጋር ብቻ ነበር። ምፅዋንም በነፃ በ1877 ዓ.ም የተረከበችው ከእንግሊዝ ነበር። ሰሜኑን ኤርትራን በዚህ ዓይነት እጅ ስታደርግ አሰብን ያገኘችው ደግሞ ቀደም ብላ በስምንት ሺህ ብር በመግዛት ነበር። የገዛችው ሩባቴና በተባለ አንድ የንግድ ኩባንያ ስም፣ ጁስፔ በተባለ ሚሲዮናዊ ደላላነት፣ ኢብራሂምና ሐሰን መሐመድ ከሚባሉ ሡልጣኖች ነው። ጣልያን ከኤርትራ አያያዝ ያገኘችው ትምህርት፣ አዝያ በሽንገላና በግዥ ብዙ ነገር ማግኘት እንደሚቻል ነው።[1]


ጣልያን ደቡብ ሶማሊያን የያዘችው ልዩ፣ ልዩ ሡልጣኖችን በመደለልና በገንዘብ በመግዛት ነው። ለአሥር ከረጢት ሩዝ የተለወጡ ደሴቶች መኖራቸው በታሪክ ተመዝግቦአል።[2] ጣልያን ከሶማልያ ያገኘችው ልምድ በየዓመቱ በሚከፈል ግብር መሰል አከፋፈል፣ አንድ የሆነን አገር እርስበርሱ ነጣጥሎ መግዛትና ቅኝ ግዛት መመሥረት እንደሚቻል ነው።

ጣልያን ኅዳር 26 ቀን 1929 ዓ.ም ወልወል ላይ ግጭት ያነሳችው፣ ከከባድ ትጥቅ ጋር እነኚህን የቅኝ አያያዝ ልምዶችዋን መነሻ አድርጋ ነው። እዚህ ግን ይኼ እስከ ኅዳር 1934 ዓ.ም፣ በድምሩ ስድስት ዓመት አስገብቶ፣ ጐንደር እጅ እንደሚያሰጣት አልጠረጠረችም ነበር። በዚህ ምዕራፍ የምንመለከተው ሌላው ነጥብ ይህ ጉዞዋ በአስተዳደር ዓይን ሲታይ ምን እንደሚመስል ነው።

ማርሻል ባዶሊዮ ሚያዝያ 27 ቀን 1928 ዓ.ም አዲስ አበባ ገብቶ፣ ግንቦት 1 ቀን 1928 ዓ.ም /ሜይ 9 ቀን 1936/ ኢትዮጵያን የኢጣልያ ቅኝ ግዛት የሚያደርጋት አዋጅ ሮም ወጣ። ሣልሣዊ ኢማኑኤል የኢትዮጵያ ንጉሠ

ነገሥት ተባለ። የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሥልጣን ለኢማኑኤልና ለልጅ ልጆቹ እንደተዛወረ ለዓለም ኅብረተሰብ ተገለጸ። ሰኔ 8 ቀን 1928 ዓ.ም /ጁን 15 ቀን 1936/ የኢጣልያ ምሥራቅ አፍሪካ ግዛትን የሚመሠር ት አዋጅ ወጣ። ይህም ኢትዮጵያን፣ ኤርትራንና ሶማሊያን የሚያጠቃልል ሆነ። የኢትዮጵያም ቅርጽ ከጂቡቲና ሰሜን ሶማልያ በስተቀር ጥንታዊ ይዘቱን አገኘ። ጣልያንም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩት ልዩ ልዩ ሕዝቦች ናቸው ብላ ታወራበት በነበረው አፍዋ፣ አንድ ሕዝብ ነው አለች።

በእነዚህ አዋጆች መሠረት ስድስት አስተዳደሮች ተመሠረቱ። ኤርትራ ትግራይን ጠቅልላ አሥመራ፣ ደቡብ ሶማሊያ ኦጋዴንን ጠቅልላ መቃድሾ እንዲሆኑ በማድረግ ሁለቱ የቅኝ ግዛት አገራት፣ የቅኝ አገር ሆነው የቆዩበትን፣ የአገልግሎት ዋጋቸውን ተከፋፈሉ። ቀጥሎ የተደለደሉት አማራው፣ ጐንደር፤ ሸዋ፣ አዲስ አበባ ሆነው ነበር። ወዲያውም አፋርና ኢሣ፣ ሐረር ሆኑ። በመጨረሻም ኦሮሞ- ሲዳማ ጂማ ሆነ። ከሸዋ በስተቀር በቀድሞ የሀገር ስም የተመደበ አልነበረም። ሁሉም በዘር ነበር። ይህም ሆን ተብሎ የተደረገ ነበር።



የጣልያን ምሥራቅ አፍሪካ አስተዳደር ካርታ።

በሮም ከተማ የኢጣልያ መንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለአዲሱ ቅኝ ግዛት በሚያመች ዓይነት ተዋቀሩ። የኢጣልያ ምሥራቅ አፍሪካ ሚኒስቴር ተቋቋመ፤ ሥልጣንም ተሰጠው። የመሥሪያ ቤቶቹ በአዲስ እቅድ መደራጀት መልካም ሆኖላቸው ሣለ፣ የአሠራር ችግር ተፈጠረ። በውጭ ጉዳይና በምሥራቅ አፍሪካ ሚኒስቴር፣ እንደዚሁም በጦር ሚኒስቴርና በገንዘብ ሚኒስቴር፣ በሌሎችም ሚኒስትሮች መካከል የሥራ መጓተት ተፈጠረ። የየበኩላቸውን ሥራ በሚመለከት እንደ እርሻ፣ ንግድና እንዱስትሪ ሚኒስቴር




ያሉ መሥሪያ ቤቶች እጃቸውን ለማስገባት ሞከሩ። የጥቅምና የሥልጣን፣ እሱንም ተከትሎ የሰው ፀባይ በልዩ ልዩ ጉዳዮች ገባ። ኢትዮጵያ ውስጥ የጦርነቱ መቀጠል ይህንን የሥራ ተጓተት አከረረው። በዓለም ማኅበር ጉባዔ የተነሳው ክርክር ጥልፍልፍ ችግር ፈጠረ። ችግሮች ደግሞ የሞሶሊኒን ጩኸት ፈርተው ንቅንቅ የማይሉ ሆኑ። የባለሥልጣኖች የርስበርስ መመቀኛኘትና ተቃርኖ ጠነነ። ሊሶና በሚባለው የአፍሪካ ጉዳይ ሚኒስትርና የኢትዮጵያ ገዥ በነበረው በግራዝያኒ መካከል የተነሣው ጡብ ብዙ ከአጪቃጨቀ በኋላ፤ ሊሶና ከሥራው ተባርሮ በቦታው ግራዝያኒ እስኪተካበት ድረስ ቀጠለ።[3]

አዲስ አበባ ላይ በነበሩ ባለሥልጣኖች ልዩ፣ ልዩ እርምጃዎች ተወሰዱ። ከድል በኋላ የቀጠለውን፣ አሳፋሪ የሆነባቸውን ጦርነት በቶሎ ለመጨረስ አጣዳፊ ሥራ ተያዘ። እሱውም፡- የጣልያንን ቅኝ ግዛት የሚቃወመውን ሁሉ መጨረስ፤ ሀገራቸውን ለመከላከል ይንቀሳቀሱ የነበሩ ኃይሎችን መደምሰስ ሆነ። ከግንቦት 1928 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 1931 ዓ.ም በቆየው በዚህ የኃይል ሥራ በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ተገደሉ፣ አካለ ጐደሎ ሆኑ፣ አሥር ቤት ታጐሩ። ይህ የኃይል አሠራሩ ግራዝያኒን ራሱን ወደ 350 ቦታ አቆሰለው። የኃይሉ ሥራ እንደ አላዋጣ ቁርጡ ሲታወቅ፣ የጣልያን አያያዝ ወደ ሰላምና መረጋጋት ዞረ። በጣልያን ከሀዲነት ከአድዋ ጀምሮ ልቡ የቆሰለው የኢትዮጵያ አርበኛ ይህንንም የማይቀበል ሆነ። ከጣልያን ከራሱ ባገኘው ሥንቅ ከህዳር እስከ መጋቢት 1932 ዓ.ም ያገገመው አርበኛ፣ በሚያዝያ ወር ያንኑ የቀድሞውን ጠዝጥዝ ጦርነቱን ቀጠለ።

ጣልያኖች አዲስ አበባ ሲገቡ፣ ከአገሩ ተወላጆች ጋር በመወዳጀት ተቀላቀሉ፣ በመዋደድ ተዋለዱ። ይህ ሁኔታ ለቅኝ ግዛት የማይመች ሆነ። የቅኝ ገገርውን የጣልያንን ንጹህ ደም መጠበቅ አስፈለገ። የዘር ልዩነት አዋጅም ወጣ። እንደ አዲስ አበባ፣ አሥመራ፣ ሞቃድሾ፣ ጐንደር፣ ሐረርና ድሬዳዋ ባሉ ከተሞች ነጭና ጥቁር የሚኖሩባቸው የከተማ ክልሎች ተለዩ። ቀደም ሲል እንደገለፅኩት በአዲስ አበባ ወሰኑ የፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ድልድይ ሆነ። ነገር ግን ነጩ ከጥቁሩ ተለይቶ መኖር አቃተው። ሰው ከሰው ጋር በሚኖረው ተፈጥሯዊና ሌላም ግንኙነት፣ ይኼው ቅርርብ ከተደነገገው ሕግ ውጭ ቀጠለ። ከፖሊሲው በተቃራኒ ግንኙነቱ ከጦር ወደ ሰላም የመዞሩ ሁኔታ፣ ለፖሊሲው መለወጥ አንዱ ምክንያት ሆነ። በጣልያን መንግሥትና በአርበኞች መካከል የተጀመረው ዕርቅ መፍረስ፣ ይህንን ትሥሥር ሳያፈርሰው ቀረ። ስለዚህ ከአሥር ሺህ ያላነሱ ክልሶች ተወለዱ።

በኢትዮጵያውያን መካከል በብሔረሰብ ስሜት ላይ የተተከለ ልዩነት ለመፍጠር የጣልያን መንግሥት ጥረት አደረገ። ወላይታን፣ አማራን ፍጅ ቢሉት፣ ሳይፈጅ ቀረ። ምክንያቱም ሸዋ፣ ጐንደር፣ ጐጃምና ወሎ ካልዘመትን፣ ከዚህ ያሉትን ባላባቶች ብንፈጅ ምን ውጤት ይገኛል በሚል




የጣልያን ምሥራቅ አፍሪካ አስተዳደር ካርታ።

ምክር በመስማማታቸው ነው። የሰላሌው ባላባት ደግሞ ሕዝቡ አንዳንድ ቁና ጤፍ አምጥቶ እንዲያቀላቅል ካደረገ በኋላ፤ እያንዳንዱ ሰው የራሱን ጤፍ መርጦ እንዲወስድ በማዘዝ የጣልያን ትዕዛዝ ሊፈፀም የሚችል አለመሆኑን አስገነዘቡ። ይህንን በመሳሰለ ዘዴ የኢትዮጵያ መሪዎች ስለአመከኑት፣ የጣልያን መንግሥት የተማመነበት ሕዝብን እርስ በርሱ የማጣላት ሥልት ከሸፈ።

ሌላው ጣልያን የተጠቀመበት ዘዴ የእምነት ልዩነትን ማክረር ነበር። ሥልቱ የእምነት እኩልነት የሚል እንዲሆን ተደረገ። በመጀመሪያ ለጦርነቱ ቡራኬ የሰጡት አባ ፔኦ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሥልጣን እንዲያገኙ ማድረግ ተሞከረ። የግብፁ ጳጳስ ሳይስማሙ ቀሩ። ሁለት ኢትዮጵያውያን ሊቃነ ጳጳሳት፤ አቡነ ጴጥሮስና አቡነ ሚካኤል፤ በዚህ ጥያቄ ላይ የሰማዕትነትን ጽዋ ተቀበሉ። አንድ ሊቀ ጳጳስ፣ አቡነ ይስሐቅ ከአሥር ቤት ገቡ። ከአራቱ ኢትዮጵያውያን ሊቃነ ጳጳሳት የቀሩት አንዱ፣ አባ አብርሃም ብቻቸውን ቢጮኹ እሚሰማቸው ጠፋ። ከዚያ ቀጥሎ እስላሙን በክርስቲያኑ ላይ ለማስነሳት ልዩ ጥረት ተደረገ። እሱም ውጤት ሳይሰጥ ቀረ። ይህ ስልት እንደገና ተለውጦ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንን በማጠናከር ሕዝቡን ለመሸንገል ተሞከረ፤ ግን አልሆነም።

ሌላው የኢትዮጵያን ሕዝብ ልቡና ማመሳቀያ መሣሪያ፣ መገናኛ ብዙሀን ነበር። የቄሣር መልእክተኛ የተባለ ሣምንታዊ ጋዜጣ፣ የሮም ብርሃን የተባለ ወርሐዊ መጽሔት ተቋቋመ። ተሐድሶ ኢትዮጵያ የምትባልም ነበረች። አንዳንድ የልማት ሥራዎችን፣ በተለይም መንገዶችንና ድልድዮችን በፎቶግራፍ የሚያሳዩ ነበሩ። ሮም፣ የኢትዮጵያ መንግሥት አምባሳደር የነበረው አቶ አፈወርቅ አፈቄሣር ተብሎ እንደጌቶቹ ተናገረ። በፓሪስ አምባሳደር የነበረው ብላታ ወልደማርያም አየለም እንደዚሁ። ነገር ግን ጣልያን አንዳች ውጤት አላገኙም።

የወጣቱን ልቡና ለመስለብ፣ የእስፖርት እንቅስቃሴ ተጠናከረ። አራዳ፣ ስድስት ኪሎ፣ እንጦጦ፣ ኮንሰላታና ቀበና የተባሉ ቡድኖች በአዲስ አበባ ከተማ ተቋቋሙ። የኢትዮጵያውያን ጨዋታ ተዘወተረ። በጋዜጣም ይወጣላቸው ጀመር። ወጣት ይድነቃቸው ተሰማንና ሌሎች ጥቂት መሰሎቻቸውን ለኢትየጵያ ከማበርከት በስተቀር፣ የኢጣልያንን ጉዳይ የሚተኩስ ውጤት ግን ከዛ አልተገኘም።

በሲዳማ ክፍለ አገር ለመኳንንት፣ ለሹማምንትና ለባላባት ልጆች ትምህርት ቤት ተሠራ ተብሎ በሠፊው ተወራ። አዲስ አበባ ጉለሌ በነበረው ፓሪን ቺፒዮ፣ አሁን የፖሊስ ክበብ በሆነው፣ ስድስት የመሣፍንት ልጆች ገብተው ይማሩ እንደነበር ይታወሳል። ነገር ግን አንዳች አልፈየደም።

በአማርኛ ቋንቋ ላይ ክርክር ተቀሰቀሰ። ፊደል ይቀነስ ተብሎ በአቶ ወልደ ሩፋኤል በቀረበ አስተያየት መነሻነት ክርክር ተካሄደ። በአቶ አማረ



አክሊሉ የተሰጠው መልስ "በዐይን ዋዛ" የሚል ሆነ። ከአቶ ወልደሥላሴ ሐሰን የተሰጠውም አስታራቂ ሃሳብ ውጤት አልሰጠም። ቀደም ብሎ በግራኝ መሐመድ አማካይነት በተካሄደው የቱርክ ወረራም ጊዜ እንደነበረው አማርኛ የመንግሥት የሥራ ቋንቋ መሆኑ ቀጠለ። ትዕዛዞችና ደንቦች የሚወጡት፣ ጋዜጦችና መጽሔቶች የሚታተሙት፣ ሬዲዮ የሚናገረው በእሱ እንደ ሆነ ቀጠለ።[4]

የራሳቸውን ገቢ ለመጨመር፣ ጣልያኖች በኢትዮጵያ ላይ የልማት ሥራዎች ለማካሔድ ታላቅ ሙከራ አደረጉ። ከልማት ሥራዎቹ ዋነኛው የመንገድ ሥራ ሆነ። በደሴ በኩል ወደ አዲስ አበባ የተሠራውን መንገድ እስከ አሥመራ ለማገናኘት፣ እንዲሁም ከአሥመራ ጎንደር ሥራ ቀጠለ። ከአዲስ አበባ ድሬዳዋ፣ ሐረር፣ ጅጅጋ፣ ቀብሪ ደሐር፣ እንዲሁም ከፈርፈር እስከ ሞቃድሾ መንገድ ተሠራ። ከሞቃድሾ ደሎ እስከ አርቤጉና ጥርጊያ መንገድ ተከፈተ። ከአዲስ አበባ እስከ ጂማ፤ ከአዲስ አበባ እስከ ጌራ፤ ከአዲስ አበባ እስከ ጉሐጽዮን፤ ከደብረ ማርቆስ እስከ ዓባይ እንዲሁም ከደብረ ማርቆስ እስከ ቡሬ፤ ከአሰብ እስከ ኮምቦልቻ፤ መንገድ ተሠራ። እንደ ጣልያን መንግሥት ሂሣብ በጠቅላላው 7.46 ሚሊዮን ሜትር ካሬ መንገድ ተሠርቶ አልቆአል። ከዚሁ ውስጥ 34,000 ካሬ ሜትር በአስፋልት ተነጥፎአል። አራት ታላላቅ ድልድዮችና 1504 አነስተኛ ድልድዮች ተሠርተዋል። መንገዶቹ የተሠሩትም በ17 ሚሊዮን የሥራ ቀናት ነው ተብሎአል።[5] ትናንሽ የገጠር ከተሞችም መንገድ ተከፍቶላቸዋል። ለነገሩ ይህ አሀዝ የተጋነነ ነው። የተባለውን ያህል ተሠርቷል ቢባል እንኳን፣ የታቀደለትን ግብ ከማሳካት አኳያ ግን፣ ውጤቱ ትንሽ ነው። ለኢጣልያ አልጠቀማትም እንጂ፣ ኢትዮጵያ ካገኘችው የጦር ካሣ አንዱ መንገድ ነው።

ሌላው የልማት ሥራ የተጀመረው በእርሻው መስክ ነበር። የዚህ ክፍል ልማት አላማ ባለብዙ ፈርጅ ነበር። መሬት የጠበበውን የጣልያን ገበሬ በኢትዮጵያ ላይ ሰፋፊ መሬት በመስጠት እንዲያርስ ለማድረግ፣ እንደዚሁም ባለሀብቶች በኮንሴሽን መሬት እየተረከቡ ሠፋፊ እርሻ እንዲያቋቁሙ፤ በዚህ ዓይነት በኢትዮጵያ ለሠፈረው የጣልያን ሠራዊት በቶሎ ምግብ እንዲያገኝና አልፎ ተርፎም ወደ ኢጣልያ እንዲጓዝ ነው። በዚህ ጉዳይ በከፍተኛ ደረጃ ስለታሰበበት፣ ስለ መሬት ይዞታ አንድ ጥናት ተካሄደ። ይህ ጥናት እንግሊዝ፣ ፈረንሣይ፣ ቤልጅግ፣ ጀርመን በቅኝ ግዛቶቻቸው ያቋቋሙትን የመሬት ይዞታ ሥርዓት በሠፊው ከዳሰሰና ከቀደምቶቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች፤ ማለትም፡- በሊቢያ፣ በኤርትራና በሶማልያ፤ የተተከለውን ሥርዓት ካጤነ በኋላ የሰጠው ምክር፡- "…የንጉሡን፣ የመኳንንቱንና አንገዛም ያሉትን ወገኖች መውረስ ይቻላል" የሚል ሆኖ፤ ለሌላውን ግን ለመውረስ ገንዘብ መክፈል እንደሚያስፈልግ የሚጠቁም ሆነ።[6] በዚህ መሠረት የንጉሠ ነገሥቱና የእነራስ ብሩ መሬት ተወረሰ። በጎንደር፣ ዋጅራት፣ ወገራና ፎገራ፤ በጐጃም፣

አቸፈር፤ በሐረር፣ ጨርጨር፤ በአርሲ፣ ገንዳ፤ በቦረና፣ ነገሌ፤ በከፋ፣ ቦንጋ፤ በሸዋ፣ ወላይታና ቢሾፍቱ፤ እንዲሁም በአዋሽ ሸለቆ ታላላቅ የእርሻ ሥራዎች ተጀመሩ::

ነገር ግን ከንጉሡና ከመኳንንቱ የተወሰደው መሬት አልበቃም:: ሌላ በርካታ መሬት አስፈለገ:: የተፈለገው ምን ያህል እንደሆነ የተገለጸ ነገር የለም:: ሕዝብ እንዳያስደነብር በምሥጢር መያዝ እንደነበረበት መገመት ይቻላል:: ቢሆንም አንዳንድ ምልክቶች አሉ:: ከዋጅራት 180,000፣ ከኦሮሞ-ሲዳማ 200,000 ሄክታር እንደነበር ታውቆአል:: ከዚህ በመነሳት ቢያንስ 300,000 ጋሻ፣ ማለት 1.2 ሚሊዮን ሄክታር ሳይከጀል እንዳልቀረ መገመት አምብዛም አያሳስትም::

ጉዳዩ በዕቅድ ደረጃ እንደዚህ ሆኖ ሳለ፣ በአፈፃፀም ችግር አስከተለ:: መሬት ማግኘት ቀላል አልሆነም:: ገበሬ ተገዥነትና ጭሰኝነት እንደሚቀርለት ተሰብኮ ነበርና፣ ከእነጭራሹ መሬቱን ልቀቅ ሲባል ተቃውሞ አነሳ:: ባለርስቱ ደግሞ ገንዘብ ተቀብሎ መልቀቅ አልፈለገም:: አንዳንዱም ገንዘቡን እየተቀበለ ጫካ ገባ:: ትልቅ ምስቅልቅል ተፈጠረ:: ለመሬት ማስለቀቂያ የሚከፈል ገንዘብ ማግኘት ለኢጣልያ መንግሥት ባለሥልጣኖች ቀላል አልነበረም:: የተገኘውም ጥቂት ገንዘብ በትክክል በሥራ ላይ ሲውል አልቻለም:: ለምሣሌ ሮም ያሉት ባለሥልጣኖች ለዚህ ጉዳይ 600 ሚሊዮን ሊሬ አወጣን ሲሉ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ማስረጃዎች የሚያመለክቱት 1,127,175 ሊሬ /18.8%/ እንደተከፈ ለ ነው:: ቀሪው 81.2% ተደለልና ተጓተት በበዛበትና ከሮም እስከ አዲስ አበባ፤ ከዚያም እስከ (ጠቅላይ) ግዛቶችና አውራጃዎች በተዘረጋው ቢሮ ውስጥ ሰጥሞ ቀርቶአል ማለት ነው::

መሬት እንደምንም ሲገኝ ደግሞ ገበሬ ጠፋ:: የጣልያን ገበሬ በየቀኑ መርዶ ወደሚመጣበት አገር መሄድ አልፈለገም:: ማምጣት የተቻለው 3,200 ገበሬዎች ብቻ ሆነ:: የግል ባለሀብቶችም ጥሪታቸውን ቁርጡ አልታወቀበት አገር ውስጥ መጣል አልፈለጉም:: እነዚህኑ ጥቂት ተብለው የተገመቱትን ገበሬዎች ማቋቋም ደግሞ ተጨማሪ ወጭ ጠየቀ:: ለዚህ ጉዳይ ደግሞ ሌላ 850 ሚሊዮን ሊሬ እንደተከፈለ የሮም ባለሥልጣኖች መዝግበዋል:: ስንቱ ለመጣው ገበሬ እንደ ደረሰ አልታወቀም:: ይህም ሁሉ ሆኖ እርሻዎቹ ውጤት አላሳዩም:: ደብረ ዘይት ከነበሩት ዲዮዲ ከተባሉ ሁለት ወንድማማች ገበሬዎች በስተቀር፣ ሌላው ሁሉ ከሠረ:: ሁለቱ ወንድማማቾችም ከአካባቢያቸው የኢትዮጵያ ገበሬዎች ለመስማማት ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ነበረባቸው::

በእነዚህ ጥልፍልፍ ችግሮች ስለተያዘ፣ የቅኝ ገዢው የግብርና ልማት ውጤት ሳይሰጥ ቀረ:: የምግብ እጥረት ተፈጠረ:: እንኳን ወደ ኢጣልያ መጫን፣ እዚህ ያለውን የጣልያን ሰፋሪ መመገብ ሳይቻል ቀረ:: በዓመት 100 ሺህ ቶን ይገኛል የተባለው፣ በዓመት 43 ሺህ ቶን ብቻ ሆነ:: ሌላውን፣



ቀሪውን በውጭ ምንዛሬ ጭምር እየተገዛ፣ ከጣልያን አገር ወደ ምሥራቅ አፍሪካ መጫን ግድ ሆነ::[7]

ሌላው የልማት መስክ የኢንዱስትሪ ይሆናል ተብሎ ነበር:: የግብርናውንም ሥራ ጨምሮ 40 ያህል ኩባንያዎች ገቡ:: የኢንዱስትሪው ዘርፍ፣ ከግብርናው የተሻለ ሳይሆን አልቀረም:: ምክንያቱ፡- በከተሞች አካባቢ የሚካሄድ ሥራ በመሆኑ፣ የፀጥታ ችግር ላያጋጥመው ይችላል:: በተረፈ ሁኔታው ተመሳሳይ ነው:: እንደ ሲሚንቶና የመጠጥ ፋብሪካ የመሳሰሉ ፋብሪካዎች ተከፈቱ:: ቢሆንም ወደ ጣልያን አገር ሊላክ የቻለ ያለ አይመስልም፤ ጥቅም ያስገኙም አይመስልም:: በተረፈ ግን ለብዙ ኢትዮጵያውያን የቴክኒክ ሙያ በማስጨበጥ ረገድ ታላቅ ጥቅም ተገኝቶአል:: ከዛን ጊዜ አንስቶ ኢትዮጵያውያን የቴክኒክ ዕውቀት ማግኘታቸው በየቦታው የሚታይ ስለሆነ፣ ማስረጃ የሚጠይቅ ጉዳይ አይሆንም::

የንግድ ሥራ በመጠኑ ስኬታማ ሳይሆን አልቀረም:: በተለይም የሆቴል ሥራ:: በወቅቱ 1,436 ጣልያናውያን በንግድ ሥራ መሠማራታቸው ተመዝግቦአል:: የንግድ ሥራ ከሕዝብ ጋር የጥቅም ግጭት ባለመፍጠሩ ብዙ ችግር አላስከተለም:: በአዲስ አበባና በሌሎችም ከተሞች ሆቴል ቤቶች ተቋቁመው ሥራ ቀጥለው ነበር:: በከተሞች ውስጥ በመሆናቸው፣ የጦርነቱ ወላፈን አልነካቸውም:: ቢሆንም ሻጭም፣ ገዥም ሆነው የቆሙት በአብዛኛው ጣልያናውያን ራሳቸው ስለነበሩ፣ ወደ ኢጣልያ የሚፈስስ ትርፍ የተገኘ አይመስልም::

ከመንገድ ቀጥሎ ጣልያኖች ጥሩ ሥራ የሠሩት በሕንፃ ረገድ ነው:: በአዲስ አበባ፣ በጐንደር፣ በሐረር፣ በድሬዳዋ፣ በጂማና በሌሎችም ከተሞች ጥሩ ጥሩና ጠንካራ ግንብ ቤቶች ሠሩ:: ለእነሱም ቢሆን ቦታ የማግኘቱ ጉዳይ ቀላል አልሆነላቸውም:: አብረውት የሚኖሩትን የከተማውን ሰው ቅር ላለማሰኘት የቦታ ግምት መክፈላቸው አልቀረም:: እሱንም ቢሆን ለኢትዮጵያ ጥለው ሄዱ እንጂ አልተጠቀሙበትም::

ኢጣልያ ለቅኝ ግዛት አስተዳደሯ እንዲጠቅማት በማሰብ፣ በኢትዮጵያ ላይ የልማት ሥራ ለማካሄድ ልዩ ልዩ ጥረት አድርጋ እንደነበር፣ ከላይ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች አስረጅዎች ናቸው:: ነገር ግን እራሷ ጥቅም አላገኘችባቸውም:: ጥቅም ሳታገኝ የቀረችባቸው ምክንያቶች በእያንዳንዱ የልማት ዘርፍ የተገለፀ በመሆኑ እንደገና መድገም አያስፈልግም:: ይህም ቢባል የደከመችበት የልማት ሥራ በከንቱ ፈስሶ አልቀረም:: ከጦርነቱ በኋላ ለኢትዮጵያ መከፈል ለነበረበት የጦር ካሣ (በከፊል) ማጣጫ ሆኗታል::

ሌላው የኢጣልያ ችግር የቢሮው ሥራ ነበር:: በድምሩ 1,725,320 ካሬ ኪሎ ሜትር ሥፋት ያለውን የምሥራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛት ማስተዳደር ቀላል አልሆነላትም:: ሰማንያ የሚሆኑ ኮሚሽነሮች፣ 260 ያህል አገረ ገዥዎች /ሬዚደንትስ/፣ 226 ምክትል አገረ ገዥዎች፤ ከነዚህም ጋር 2470

ከፍተኛ ችሎታ ያላቸው ሠራተኞች አስፈለጉ። ነገር ግን ከጣልያን አገር ማስመጣት የተቻለው 1350 ማለትም ግማሹን ሠራተኞች ያህል ብቻ ሆነ። የመካከለኛ ደረጃ እውቀት ያላቸው ሌሎች 2,157 ቢያስፈልጉም፤ እነዚህንም እንኳን በበቂ መጠን ማስመጣት አልተቻለም። የመጡት 85% ብቻ ነው። ከነዚሁ ሹማምንትና ሠራተኞች መካከል ቤተሰብ ያስመጡት እጅግ ጥቂት ስለነበሩ፣ ሥነ ልቡናቸው ከባባድ የመንግሥት ሥራ ተፅዕኖ መሸከም አላስቻላቸውም። በዚህ ላይ ደግሞ ፍቀረ ንዋይ አደረባቸው። ልምድና ችሎታ የሌላቸውም በረከቱ። ለነዚህ ሁሉ መኖሪያ ቤትና ቢሮ ማዘጋጀት፣ ነዋሪ ዕቃ ማደራጀት ግድ ሆነ።

ሥራውን ማካሄድ ግድ ስለሆነባቸው ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት የጦር መኰንኖቻቸው መካከል ችሎታ ያላቸውን እየመረጡ ለመደልደል ሞከሩ። በወቅቱ ከነበሩት 2000 መኮንኖች መካከል 79% ለውድድር ቀረቡ። ከእነዚህም 504ቱ የዩኒቨርስቲ ዲግሪ ያላቸው ነበሩ። በሌላ በኩል መኮንኖቹ እየመረጡ ባለው ቦታ ሁሉ መመደብ ጦሩን የሚያራቁት ሆነ። ጥቂቶቹን አዛውሮ ሌሎችን መተው ደግሞ፣ ቀሪዎቹን ቅር ማሰኘት ሆነ። በአነስተኛ ሥራዎች ኢትዮጵያውያንን መቅጠር ችግሩን በመጠኑ ቢያቃልልም፤ በምሥጢር አጠባበቅ ረገድ አስተማማኝነት አጣ። በዚህ ላይ በቂ ችሎታ ያላቸው አልተገኙም። ከአሉትም ጥቂት ኢትዮጵያውያን ባለሙያተኞች ውስጥ፣ ማናቸውም ለጣላት ለመሥራት ፈቃደኞች አልሆኑም። ስለዚህ የመንግሥቱ ሥራ አካሄድ ውስጡ ስምረት ሊያገኝ አልቻለም።

የቅኝ ግዛቱ ዋና ዓላማ ኢትዮጵያ ላይ ትርፍና ምርት አስገኚ ሥራዎችን በማካሄድ ለኢጣሊያ ጥቅም ለማግኘት ነበር። ነገር ግን ሁኔታው የተገላቢጦሽ ሆነ፤ ከኢትዮጵያ ገንዘብ ወይም የምግብ እህል ወይም ሌላ ዕቃ ወደ ኢጣልያ የሚያግዝ ሳይሆን፤ በየዕለቱ የሚካሄደው ሥራ መዋዕለ ንዋይ ከኢጣልያ ወደ ኢትዮጵያ የሚያስፈስስ ሆነ። ማገጃ ጠፋበት። በኢትዮጵያ ምክንያት በዓለም መንግሥታት ማኅበር ጉባዔ የተነሳው ንትርክ፣ የጣልያን መንግሥትን ጤና ነሳው። ኢትዮጵያ ውስጥ ጦርነቱ ቀጠለ። ተስፋ የተጣለባቸው የልማት ሥራዎች ሁሉ አንዳች ውጤት ሳይሰጡ ቀሩ። ወጭው አለመጠን እየበረከተ ሄደ።

በሌላ በኩል የምዝበራውን ነገር መቆጣጠሪያ ጠፋበት። የሮም አይሮፕላን ማረፊያ፣ ወደቦችና ባቡር ጣቢያዎች ከኢትዮጵያ በሚጋዙ ሣጥኖችና ሻንጣዎች ተጣበቡ። ማርሻል ባዶሊዮ ወደ ሀገሩ የገባው በ300 ሣጥን የታሸገ ዕቃ አግተልትሎ ነበር፤ ወርቅ ጭምር። የኢጣልያ የጉምሩክ ሠራተኞች እንደዚያ ያለ ጓዝ አይተው ስለማያውቁ፣ ጭንቅ ተፈጠረ። በሞሶሊኒ ልዩ ትዕዛዝ ሳይፈተሽ እንደታሸገ ገባ። ግራዚያኒም ነፃ 79 ሣጥን ይዞ ገባ። ሌሎችም ሹማምንቶች እንደዚሁ። ይህ ብቻም አልነበረም። ለባዶልዮ አንድ ሚሊዮን፣ ለግራዚያኒ ግማሽ ሚሊዮን ሊሬ በየዓመቱ



እንዲከፈላቸው ተወሰነ። በዚህ ላይ ደግሞ የሮም ባለሥልጣኖች ኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ ለመሥራት ከመንግሥት ጋር ውል ከሚዋዋሉት ኩባንያዎች ጋር የመደለል ሥራ ተጧጧፈ። ለምሣሌ ሲሶና በተባለው የአፍሪካ ጉዳይ ሚኒስትር ትዕዛዝ እስካሌራ በተባሉ ወንድማማቾች ላይ የቀረበባቸው ክስ፤ ከዲቦኖ ጋር በመስማማት ከኢጣልያ መንግሥት 50 ሚሊዮን ሊሬ ያለአግባብ ወስደዋል የሚል ነበር።

በዚህ ሁሉ ምክንያት የምሥራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛት ወጭ እየናረ ሄደ። የበጀት ድልድል የማይገድበው ሆነ። አዲስ አበባ ላለው የሣልሣዊ ኢማኑኤል እንደራሴ እስከ 5 ሚሊዮን፣ በውስጡ ላሉት አገረ ገዥዎች እስከ 2 ሚሊዮን ሊሬ በዓመት ከበጀት በላይ ለማዘዝ የሚያስችላቸው ሥልጣን ቢሰጣቸውም፣ ያም ሳይበቃ ቀረ። ለምሣሌ በ1929 ዓ.ም /1936-37/

ሀ. ጠቅላላው ከጣልያን አገር የሚገኘው የመንግሥት ገቢ 18,581 ቢሊዮን ሊሬ እንደሚሆን ተገመተ።

ለ. ለምሥራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛት ማስተዳደሪያ እንዲመደብ ከአፍሪካ ጉዳይ ሚኒስትር የተጠየቀው 5 ቢሊዮን ሊሬ ነበር።

ሐ. ነገር ግን ወጭ የተደረገው 19,136 ቢሊዮን ሊሬ ሆነ።

የሮም ባለሥልጣኖች በዚህ ሲደነቁ ለ1932 ዓ.ም /1939/ የበጀት ዘመን፣ በዱክ ደ አዎስታ የተጠየቀው በጀት 4.8 ቢሊዮን ሊሬ ሆነ። በገንዘብ እጦት ምክንያት ተቀንሶ 1.371 ቢሊዮን ሊሬ ብቻ ነበር።[8] በዚህ የተነሣ ኢጣልያ እጅግ የከበረ ዋጋ ያላቸውን ሥዕሎችዋን ከሙዚየም እያወጣች የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት ለውጭ አገር ሰዎች እስከ መሸጥ ደረሰች።[9]

የወታደሩ አስተዳደር ደግሞ ሌላ ራስ ምታት አመጣ። የአውሮፓ ኑሮ ምቾትና ልስላሴን ያዘወተረ ነው። የጣልያናውያን ኑሮም እንደዚሁ ነው። በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን ከተሞች የተለመደም ቢሆን የኑሮውን ዘይቤ በቀረቤታ ማየት አይከፋም። በአውሮፓ ምግብ ከመኝታ ሲነሱ ጀምሮ ተመልሶ እስኪተኙ በተደጋጋሚ ይካሄዳል። ጥዋት ቁርስ ደንብ ነው። ከብርቱካን ጭማቂ ጋር የእንቁላል ወይም የሥጋ ጥብስ በዳቦ ይቀርባል። ሻይ በወተት ይቀርባል። ረፋዱ ላይ ሻይ በብስኩት አለ። ምሣ ሁለትና ሦስት ዓይነት ሆኖ ፓስታ ይኖራል። ማዋዢጃው የወይን ጠጅ ነው። ቡናም አለ። ወደ ማታ ሻይ ከብስኩት ጋር አይቀርም። ማታ ራት ሾርባ ከለስላሳ ምግብ ጋር ይሆንና የአልኮል መጠጥ ይኖራል። በአንዳንድ ምሽት ዳንስ ጨዋታ ወይም ትያትርና ሲኒማ ይታያል። የልብስ ጉዳይ ደግሞ አለ። የቀን ልብስ የሚሞቅ፣ የማይሞቅ ሆኖ ሙሉ በውስጥ ልብስና ሸሚዝ፣ ከራባት አለው። ሲሆን ሦስት ካልተቻለም ሁለት መለወጫ ይኖራል። ለእግር ጫማ ከእሱም ጋር የእግር ሹራብ አለ። ለራስ ባርኔጣ ይደረጋል። በዚሁ ላይ ካፖርት ይኖራል። የሌሊት ልብስ ደግሞ ጥንድ አንሶላ ከነመለወጫ፣ በቂ ብርድ ልብስና ፍራሽ አለ። ሙሉ የሣሎን፣ የመኝታ ቤትና የምግብ ቤት ዕቃ አለ። ተከራይቶም እንኳን

ቢሆን በቂ መኖሪያ ቤት አይጠፋም። መኪና የግሉም እንኳን ባይሆን በሕዝብ ትራንስፖርት መጠቀም ይቻላል። በዚህ ሁሉ ላይ ቆንጆ ሚስት፣ ተወዳጅ ልጆች አሉ።

የኢጣልያ ጦር ወደ ኢትዮጵያ የተጓዘው በሰኔ 1927 ዓ.ም ነው። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ከላይ የተዘረዘረው ፀጋ ሁሉ በሞሶሊኒ ቅዥት ተጠቅልሎ ሮማ ቀረ። የጣልያን ወታደር ጨፍሮ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው፣ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ጦርነቱን ጨርሶ ወደ ሰላማዊ ኑሮው ሊመለስ ነው። ነገር ግን ጦርነቱ የማያልቅ ሆነ። በአደንቋሪው የሞሶሊኒ አሽቃባጮች ጩኸት እየተነተተ የጣልያን ወታደር ኢትዮጵያ ላይ በመዝመቱ ያገኘው መሞት፣ መቁሰል፣ በመዓልትና በሌሊት መንገላታት፣ መራብ፣ መጠማትና መታረዝ ብቻ ሆነ። ዋናውን፣ የ1928 ዓ.ም ጦርነት በሙሉ ልቡ በጀግንነት ተዋጋ። የ1929 ዓ.ም ጦርነት ስሜቱን ጠጥቶ በብርታት አካሄደ። በ1930 ዓ.ም ይቃለልልኛል ብሎ ሲጠብቅ፣ እንዲያውም ይባስ ሆነበት፤ ቢሆንም ቻለው። በ1931 ዓ.ም ግን ትዕግስቱም፣ ጉልበቱም፣ ፍላጐቱም ተቀነሰ። በ1932 ዓ.ም መዋጋቱን ተወ። ከአጥቂነት ይልቅ የተከላካይነትን ሚና መጫወት ጀመረ። እንዲያዉም የአርበኞች ኃይል በተራው እየከበደበት፣ ጥቃትም እየበዛበት ሄደ። የ1933 ዓ.ምቱ ወሳኙ ጦርነት ሲከፈት፣ የኢጣልያ ጦር ፍፁም በቅቶት መንቀሳቀስ ከማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር። የወታደሩን ቁጥር ከ240 ሺህ ወደ ግማሽ ሚሊዮን ከፍ ማድረግ፤ ወጭ ከማብዛትና የአስተዳደር ችግር ከማክበድ በስተቀር አንዳች ውጤት ሳይሰጥ ቀረ። ባለሥልጣኖቹ ለእርቅ የተጣደፉት በፖለቲካው ሁኔታ ተገድደው ብቻ አልነበረም። ይልቁንም በዚህ፣ በዚህ ሁሉ ምክንያት ተገድደው ነው።


## ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ*፣ ገጽ 54-57።
2. Pierre Petrides, *Boundary Questions Between Ethiopia and Somalia,* p.28-108.
3. Alberto Sabacchi, *Ethiopia under Mussolini* pp, 43-62.
4. የቄሣር መልእክተኛ ሁለት ጋዜጦች ከሚያዝያ 1 እስከ 14 ቀን 1932 ዓ.ም።
5. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 202።
6. Giuseppe Ziliotto, *Libri Fondiae Nelle Colonie*, pp. 316-331.
7. Sabacchi, pp. 95-114.
8. *Ibid.*, pp. 43,114.
9. Stanely Cooperman, *Benito Mussolini*, pp. 18-123.




# ምዕራፍ ሃምሣ
# የቅኝ ግዛት ወታደሮች ሚና

እንደማንኛውም የቅኝ ግዛት ጦርነት፣ የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት የተካሄደው በቅኝ ግዛት ወታደሮች ጭምር ነበር።

ኢጣልያ በጦርነቱ ጊዜ በኢትዮጵያ ላይ ስለአሰለፈችው ወታደር ብዛት የታሪክ ጸሐፊዎች ግምት ይለያያል። በኢትዮጵያ ላይ በቆየችበት ወቅት የነበራት ጦር ብዛት ደግሞ ከጊዜ ወደ ጊዜ ይለያያል። ቢሆንም አንዳንድ የታመኑ ነገሮች አሉ። ጄነራል ደቦኖ መስከረም 23 ቀን 1928 ዓ.ም የመረብን ወንዝ የተሻገረው 250,000 ወታደር አሰልፎ ነው። ከዚሁ ውስጥ 65,000 ኤርትራውያን ነበሩ። በደቡብ በኩል ደግሞ 33,000 የቅኝ ግዛት ወታደሮች ነበሩ። ቆይቶ ደግሞ 5,000 ያህል ሱማሌዎች ተጨመሩ። የጣልያናውያኑ ብዛት ግን አልተገለጸም። ሞሶሊኒ ሰኔ 3 ቀን 1932 ዓ.ም ከጀርመን ጐን የቆመው በኢትዮጵያ ላይ 350,000 ጦር አሳፍሮ ነው። እነዚህን አሀዞች ይዞ አንዳንድ ግምት መሥራት ብዙ አያሳስትም። ስለዚህ ከመጋቢት እስከ ሰኔ 1928 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ፤

| | በሰሜን ግንባር | በደቡብ ግንባር | ድምር | % |
|---|---|---|---|---|
| ጣልያናውያን | 180,000 | 11,000 | 191,000 | 64 |
| ሊቢያውያን | 10,000 | 8,000 | 18,000 | 6 |
| ኤርትራውያን | 60,000 | 5,000 | 65,000 | 22 |
| ሶማሊያውያን | - | 26,000 | 26,000[1] | 8 |
| ድምር | 250,000 | 50,000 | 300,000 | 100 |

ይህ ቁጥር ከ1928 ዓ.ም በኋላ አልቀነሰም፤ ጨመረ እንጂ። ከኢትዮጵያም ውስጥ እየተመለመሉ ባንዶች ገቡ። እስከ ጦርነቱ ፍፃሜ የነበረው የጣልያን ጦር በትክክል አልታወቅም። በግልጽ የሚታወቀው ጣልያኖች ከሀገር ውስጥ ባንዳ በብዛት እየመለመሉ ማሰለፋቸው ነው። የእሱም ቁጥር በትክክል አልታወቀም። ጠላት ገበሬም እያስገደደ ለጦርነት ያሰለፈበት ጊዜ ብዙ ነው። ነገር ግን እሱ ከቁጥር አይገባም። አዲስ ጦር ከጣልያን አገር አልመጣም። ከአለውም ብዙ ሰው ወደ ሲቪል ሥራ ተዛውሮአል። ይህም የቅኝ ግዛቱ ወታደር እንዲበረክት አድርጐአል። ጠቅላላው ጦር ከዚህ እንደሚከተለው ሳይሆን አልቀረም።

| | ከውጭ የገባ | ባንዳ | ድምር | የባንዳው % |
|---|---|---|---|---|
| በ1928 ዓ.ም /ከጥር-ነሐሴ/[2] | 220,000 | - | 250,000 | - |
| በ1929 ዓ.ም | 220,000 | 30000 | 250,000 | 12 |
| በ1930 ዓ.ም | 250,000 | 50000 | 300,000 | 17 |
| በ1931 ዓ.ም | 250,000 | 100000 | 350,000 | 28 |
| በ1932 ዓ.ም | 250,000 | 100000 | 350,000 | 28 |
| በ1933 ዓ.ም | 200,000 | 50000 | 250,000 | 20 |
| በ1934 ዓ.ም /ከመስከረም-ኅዳር/ | 30,000 | 10000 | 40,000 | 25 |

እነዚህ ወታደሮች የራሳቸው የሆነ የእዝ ሠንሠለት ነበራቸው፡፡ ከነጮች በታች ሆነው አመራር የሚሰጡት አለቆች ሹምባሽ ይባላሉ፡፡ ከሹምባሽ በታች ቡልቅባሾች፤ ከእነሱ በታች ደግሞ ሙንጣዞች አሉ፡፡ ይህ ስም አጠራር ከሊብያ ወታደሮች የተቀዳ ሳይሆን አልቀረም፡፡ ደመወዛቸው፣

| | |
|---|---|
| የቅኝ ግዛት ወታደር | 200 |
| ለሙንጣዝ | 225 |
| ለቡልቅባሽ | 250 |
| ለሹምባሽ | 300 ሊሬ በወር ነበር፡፡[3] |

የደረጃ እድገት የሚሰጠው የሥራ ውጤት እየተገመተና የአገልግሎት ዘመንም እየታየ ነበር፡፡ ነገር ግን የመኮንንነት ማዕረግ አይሰጣቸውም፡፡ የምክትል መቶ አለቅነት እንኳን፡፡ እስከ 1930 ዓ.ም ድረስ ወታደራዊ አገልግሎት ግዴታ ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ወድዶ ለተቀጠረ ብቻ ሆነ፡፡ ከኢትዮጵያ ውስጥ በተቀጠረ ባንዳና ከውጭ በመጣ ወታደር መካከል በደመወዝ አከፋፈል ረገድ ልዩነት አልተደረገም፡፡

በደመወዝ ላይ ደግሞ የወር ቀለብ ይሠፈር ነበር፡፡ የወር ቀለቡ ደግሞ በቂ ዱቄት፣ ሻይና ስካር፣ ጨው ይጨምራል፡፡ በጦርነት ጊዜ ለአንድ ቡልቅባሽ ሠራዊት በሣምንት አንድ በሬ ይሰጣል፡፡

በአሰላለፍ ረገድ አንድ ሙንጣዝ 10 ወታደር፣ አንድ ቡልቅባሽ 2 ሙንጣዝ፣ አንድ ሹምባሽ እስከ 12 ቡልቅባሽ ይይዛል፡፡ ወታደር የሚቀጠረው የአካል ብቃትና የመንፈስ ንቃት እየተመጠነ ነው፡፡ ሥነ-ሥርዓትን በተመለከተ ሰላማዊ ሰውን በተለይም ሴቶችን መድፈር ወንጀል ነው፤ ሌብነትና ውሸት ያስቀጣል፡፡ ከጦር ግንባር መሸሽ ያስገድላል፡፡ ትጥቅን በተመለከተ ለእያንዳንዱ የቅኝ ግዛት ወታደር አንድ ባለሳንጃ ምንሽር ጠመንጃ ከበቂ ጥይትና ከአራት የእጅ ቦምብ ጋር ይሰጠዋል፡፡ የጣልያኑ ወታደር



ባለሳንጃ አልቤን ጠመንጃ ከበቂ ጥይት ጋር፤ እንደዚሁም አራት የእጅ ቦምብ ይይዛል፡፡ እያንዳንዱ ሙንጣዝ አንድ አልቤን መትረየስ አለው፡፡ ለአንድ ሹምባሽ አንድ ውሃ መትረየስ አለው፡፡[4]

ኤርትራውያን የተዋጉት በጣልያን ወገን ብቻ ሆነው አልነበረም፡፡ ጥቂቶች ከኢትዮጵያም ጐን በመቆም ተዋግተዋል፡፡ ስድስት መቶ በበረና ግንባር ገቡ፡፡ ሌሎች 350 ከጥቁር አንበሳ ጦር ጋር ተሰለፉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ከየግንባሩ እየከዱ ከኢትዮጵያውያን ወንድሞቻቸው ጋር ተቀላቀሉ፡፡ እኔ በነበርኩበት የአርበኝነት ግንባር እንኳን 4 ነበሩ፡፡ መሪአቸው አቶ ምስጋናው በየነ ይባል ነበር፡፡ እሱም በዚያው በአርበኝነት ዘመን የባላምባራስነት ማዕረግ አገኘ፡፡ በርካታ ኤርትራውያን የቻሉትን ያህል እየተዋጉ ከሞት የተረፉት ወደ ኬንያ ተሰደዱ፡፡ የብላቴን ጌታ ሎሬንሶ ታእዛዝ፣ የአብርሃ ደቦጭና የሞገስ አስግዶም፣ እንደዚሁም የዘርዓይ ደረሰ ስም ከዚህ መጠቀስ አለበት፡፡ ሌሎችም በኢትዮጵያ ምክንያት በጣልያኖች እጅ በእሥራት የማቀቁ በግዞት የተንገላቱ ብዙ ናቸው፡፡[5]

ጣልያኖች በቅኝ ግዛት ወታደሮቻቸው፣ በተለይም በኤርትራውያን በደንብ ተጠቅመውባቸዋል፡፡ ንጉሠ ነገሥቱ ስለዚሁ ጉዳይ ሲገልጹ፣ "...በዚያም /በኢጣልያ/ በኩል ከእኛ ወታደሮች ጋራ በርትተው የሚዋጉት የኤርትራ ወታደሮች ነበሩ እንጂ ጥቁር ለባሾች ጣልያኖች ጥቂት ነበሩ፡፡ ጥቁር ሸሚዝ ለባሾች ጣልያኖች ግን የሚሰለፉት በጣም ርቀው በስተኋላ ስለነበር እነሱን ለማግኘት /ለመግደል/ ብዙ ችግር ነበር..." ብለዋል፡፡[6] ጀነራል ባዶሊዮ ደግሞ ስለኤርትራ ወታደሮቹ በሰጠው ሪፖርት "...አሁንም እንደገና መልሰው ጀግንነታቸውን፣ ታማኝነታቸውንና ከዓላማችን ጋር ያላቸውን ጽኑ ግንኙነት በተግባር ገለጹ..." ብሎአል፡፡ የሚያስለፉአቸውም በአልኮል መጠጥ እያሰከሩ ነበር፡፡[7]

እነኚህ የቅኝ ግዛት ወታደሮች አገልግሎታቸው መና አልቀረባቸውም፡፡ ከ1950 ዓ.ም ጀምሮ ከኢጣልያ መንግሥት የአገልግሎት ዋጋ ተከፍሏቸዋል፡፡ አሥመራ ባለው ቆንሲል በዚያን ጊዜ ይከፈል የነበረው፡- ለወታደር 70፣ ለሙንጣዝ 90፣ ለቡልቅባሽ 130፣ ለሹምባሽ 200 በወር ነበር፡፡ ከዚህም በስተቀር የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ተከፍሎአቸዋል፡፡ እግሩ ለተቀረጠ እስከ 80000 ብር እንደተከፈለ ተመዝግቦአል፡፡ የጤና እንክብካቤም ይደረግላቸዋል፡፡ በዚህም የተነሣ ለኢጣልያ መንግሥት በሰጡት አገልግሎት ይመኩበታል እንጂ፤ ብዙዎች እንደሚጠብቁት፤ የሚያዝኑበት ወይም የማይደሰቱበት ጉዳይ አይደለም፡፡ በኢትዮጵያም ወገን ሆነው የተዋጉት የኤርትራ ተወላጆች የድካማቸው ዋጋ አልቀረባቸውም፡፡ በመንግሥት ሥራም ከከፍተኛ ደረጃ የደረሱ አሉ፡፡ ሻሽመኔ ያለው የሥመጥር ሐማሴን የዚህ ውጤት ነው፡፡[8]

ከዚህ ታሪካዊ ሁኔታ አንዳንድ ትምህርት ሰጭ ግንዛቤዎችን መጨበጥ ይገባል፡፡ በታሪኩ ውስጥ እንደተገለጸው በኢትዮጵያ ላይ በ1928

ዓ.ም በሰሜንም በደቡብም ከተሰለፉበት ጦር እጅግ ቢያንስ 36%፤ ከዚያ ቀጥሎ እስከ ኅዳር 1934 ዓ.ም በቀጠለው ጦርነት ደግሞ ከ12% እስከ 28% የኤርትራ ተወላጆች ነበሩ። ሂደቱም በኢትዮጵያ ላይ ባለብዙ ፈርጅ ጉዳት አስከተለ። ከጉዳቶቹም ዋና ዋናዎቹ፡- መጀመሪያ ላይ የጦርነቱ ሚዛን ለጣልያን እንዲያደላ ማድረጉ፣ የአገሪቱን የሰው ኃይል መቀነሱ፣ የርስበርስ ተቃርኖ መፍጠሩ ናቸው።

## ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. Luigi Frusci, *In Somalia Sulfurs Meridiale*, pp,19-40.
2. በጦርነቱ 30,000 ከጥቅም ውጭ እንደሆነ ቢገመት።
3. ከኢትዮጵያ ውስጥ ለተቀጠረ ወታደር።
4. ከግራዝማች ሣህለ ንጋቱ ይማም የተነገረኝ።
5. ኃይሉ ገብረኢየሱስ፣ መድረክ መጽሔት፣ ገጽ 69-83።
6. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ፣ 1ኛ መጽሐፍ፣* ገጽ 22-30።
7. ሙሉሰው ምትኩ፣ *የአርበኞች ትግል ከፋሽስት ጋር፣* ገጽ 32-370።
8. Araya Habtay, *The Role of Eritrean Askaris In the Italo-Ethiopian War*, pp, 5-46።



# ምዕራፍ ሃምሣ አንድ
# የአውሮፓ ሁኔታና የኢትዮጵያ የዲፕሎማቲክ ሥልት

ኢጣልያ ኢትዮጵያን ለመውረር በተንቀሳቀሰች ጊዜ የዓለም ሁኔታ በመዋገርቅ ላይ ነበር። ከ1921 ዓ.ም /1929/ ጀምሮ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ድቀት ደርሶ ስለነበር የአውሮፓ አገሮች እምብዛም አላንሠራሩም። በፖለቲካም ረገድ ሞሶሊኒ በኢጣልያ፣ ሂትለር በጀርመን፣ ስታሊን በራሺያ ሕዝቦች በመጨፈር ላይ ነበሩ። ማለትም በኢጣልያ ፋሽዝም፣ በጀርመን ናዚዝም፣ በራሺያ ኮሚኒዝም ሠፍነው ነበር። በዚህ ላይ ደግሞ የጃፓኑ ጦረኛ ቡድን ተንቀሳቀሰ።

ሁሉም ዓላማ ነበራቸው። በሀገራቸው ውስጥ ያለውን ችግር ለማቃለል መሞከር ተራራ እንደ መግፋት ያለ ጠጣር ሆኖባቸዋል። ቀላል ሆኖ ያገኙት የሕዝቦቻቸውን ስሜት ወደ ባሕር ማዶ አሻግረው እንዲመለከቱና በርስበርስ ጥላቻ እንዲያያዙ ማድረግ ሆነ። ጣልያን በኢትዮጵያ ላይ አተኮረች። የንጉሡንና የጳጳሱን ሥልጣን መቀናቀን ያዘች። ጀርመን በመጀመሪያው የዓለም ጦርነት የደረሰባትን ውርደት መበቀል ፈለገች፤ የሰላሙን ውል በማፍረስ ያጣቻቸውን ነገሮች መልሳ ማግኘት ፈለገች። በሀገር ውስጥ ጉዳይ ደግሞ አይሁዶችን የሕዝብ ጠላት አደረገች። ራሺያ በአካባቢዋ ያሉትን ሀገሮች ጠቅልላ መያዝ ፈለገች። በሀገር ውስጥ ጉዳይ ደግሞ የቀድሞዎችን ነገሥታት ወገኖች አድሀርያን ብላ ለእርድ አቀረበች። ጃፓን በአዲሱ ቅርምት ከሩቅ ምሥራቅ አገሮች ደህና ድርሻ ለማግኘት ጓጓች። አሜሪካን ደግሞ ገለልተኛ ነበረች። ፕሬዚዳንት ዊልሰን በመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ፍፃሜ ላይ በአስታራቂነት መግባታቸው እንደኃጥአት ተቆጥሮ ለሁለተኛ ጊዜ የመመረጥ ዕድላቸውን ስለአጠሩባቸው፤ ፕሬዚዳንት ሩዝቬልት ተመሳሳይ ዕድል እንዳይደርስባቸው ሰግተዋል። የአውሮፓ ታናናሽ አገሮች የየራሳቸውን ሕልውና ከመጠበቅ ባሻገር አንዳች የማድረግ አቅም የላቸውም። ላቲን አሜሪካ አፍሪካና እስያ በቅኝ ግዛት ውስጥ ወድቀዋል።

የዓለም መንግሥታት ጉባኤ በቅርቡ የተቋቋመ ማኅበር ነው። መንግሥታትን የማግባባት፣ ሲጋጩ የማስታረቅ፣ ቅራኔዎችን ሰላማዊ በሆነ መንገድና በመንግሥታቱ በራሳቸው ፈቃድ ለመፍታት አቅም አልነበረውም። ዋና ዋናዎቹ ተዋንያን እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ራሽያ፣ ጣልያንና በመጠኑ አሜሪካን ናቸው። ከቀሩት አገሮች አንዳንዶቹ የአርጋጅ አርጋጅ ናቸው። አብዛኞቹ የትርዕይቱ ተመልካቾች ናቸው። ከአፍሪካ አገሮች የማህበሩ አባላት ኢትዮጵያና ላይቤሪያ ብቻ ናቸው። ላይቤሪያም የአሜሪካ ተቀጽላ ናት። በአጠቃላይ ሲታይ በወቅቱ የዓለም ማኅበር የመላላት ባሕርይ

ይታይበታል። ለዚህ አስተዋጽኦ ያደረጉት ነገሮች ደግሞ የእንግሊዝ ወላዋይነት፣ የፈረንሣይ ግድየለሽነት፣ የጀርመን ጦረኝነት፣ የአሜሪካን ገለልተኝነት፣ የራሺያ አለመረጋጋት፣ የኢጣልያ ቅኝ ግዛት ፍላጐትና የጃፓን ተስፋፊነት ነበሩ።

ይህም ሁሉ ሆኖ ከመጣባት ጠላት የዓለም ኅብረተሰብ እንዲታደጋት ኢትዮጵያ ውትወታዋን ቀጠለች። ንጉሠ ነገሥቱ በዓለም ማኅበር ላይ ጽኑ እምነት አደረባቸው። ብዙ እንዳይታመኑ የቀረቡላቸውን ምክሮች አልተቀበሉም። የጣልያን አያያዝ ለኢትዮጵያ አስጊ መሆኑን ግንቦት 8 ቀን 1927 ዓ.ም አስታወቁ። መልእክታቸው "...ኢጣልያ አገራችንን ለመውሰድ ያላትን ምኞት ...አላቋረጠችም። ...ይኸው ምኞትዋ... በሥራዋ እየተገለጸ መታየት ጀመረ። ...በወሰኖቻችን አቅራቢያ የጦር መሣሪያ በብዛት ማከማቸት ጀመረች።..." የሚሉ ኃይለ ቃላት ያዘለ ነበር። ኅዳር 26 ቀን 1927 ዓ.ም የተደረገው ግጭት ጠቡን አረጋገጠ። ስለዚህም ሁለቱም ወገኖች ሽማግሌዎች እንዲመርጡ ተወሰነ። ኢትዮጵያ አንድ ፈረንሳዊና አንድ አሜሪካዊ መረጠች። ኢጣልያ ሁለት የራስዋን ዜጐች መረጠች። ሽማግሌዎቹ "በወልወል ግጭት ኢትዮጵያም ኢጣልያም ኃላፊ ሊሆኑ አይችሉም" የሚል ሽፋፋ ውሣኔ ሰጡ።

እንግሊዝና ፈረንሣይ የእርቅ ሃሳብ አቀረቡ። የፈረንሣይ ሚና ከመናጆ ያለፈ አልነበረም። ዋናውን የነገር ድር ያጠነጠነችው እንግሊዝ ነበረች። መሳሪያዎቹ ሆርና ላቨል የተባሉት የሁለቱ አገሮች የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ነበሩ። የእርቁ ሃሳብ በየጊዜው ተለዋውጦአል። የተለዋወጠውም በኢትዮጵያ ላይ ይበልጥ ተፅዕኖ እያሣደረ ነበር። ለመጨረሻ ጊዜ የቀረበው ሃሳብ፣

1ኛ. ኢትዮጵያ አክሱምን ብቻ አስቀርታ እስከገባ ወንዝ ያለውን አገር ለኢጣልያ እንድትለቅ፤

2ኛ. የአውሣ መሬት ለኢጣልያ እንዲሆን፤

3ኛ. ከኦጋዴን እስከ ቆራሄ ያለውን አገር ለኢጣልያ እንድትሰጥ፣

4ኛ. እንግሊዝ በበርበራ በኩል የዘይላን የባሕር በር ለኢትዮጵያ እንድትሰጥ ነበር።[1]

የእርቁ ዓላማ ኢትዮጵያን ከጠቅላላ ጥፋት ለማዳን እንደሆነ ለማስመሰል ብዙ የነገር ሥራ ተካሄደ። የሀገርን አንድነት የሚነካ በመሆኑ በኢትዮጵያ በኩል ተቀባይነት ሳያገኝ ቀረ። በዚህ ረገድ ንጉሠ ነገሥቱ ምሥጋና ይገባቸዋል። አድዋ ላይቀርላቸው ኤርትራን ቆርሰው በመስጠት አፄ ምኒልክ የፈጸሙትን ስሕተት ሳይደግሙት ቀሩ።

በዓለም መንግሥታት ጉባኤ መወሰድ ከነበረባቸው እርምጃዎች አንዱ በአጥቂዋ በጣልያን መንግሥት ላይ የጦር መሣሪያና የኢኮኖሚ ማዕቀብ መጣል ነበር። ኢትዮጵያ ይህ እንዲደረግ ደጋግማ አሳሳበች። ማኅበሩ ለሁለቱም ሀገሮች መሣሪያ እንዳይሸጥ የሚከላከል ውሳኔ አሳለፈ። ኢጣልያ ራስዋ መሣሪያ በብዛት በመሥራት ላይ መሆንዋ እየታወቀ፤ ይህንን የመሰለ



ውሣኔ የተሰጠው ለኢትዮጵያ መሣሪያ እንዳይሸጥላት ለማገድ የተሠራ ደባ ነበር። እንግሊዝ ስዊዝ ካናልን ብትቆጣጠር ችግሩ ሊቃለል ሲችል አንዳች አላደረገችም። በኢኮኖሚም በኩል ማዕቀቡ የይስሙላ ነበርና አንዳች አልፈየደም።


ኢትዮጵያ በዚህ ዓይነት የነገር አሸክላ ተተብትባ ከጣልያን እጅ ወደቀች። የአውሮፓ መንግሥታት ተሽቀዳድመው ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ ያላትን ይዞታ አወቁ። የአሜሪካ፣ የሄይቲ፣ የራሺያና የሜክስኮ መንግሥታት እውቅና ሳይሰጡ የወረራው ዘመን አለፈ። ምስጋና የሚገባው ታላቅ የፖለቲካ ብስለት ነው። እንግሊዝ እስከ ሚያዝያ 1931 ዓ.ም ተግደርድራ ከዚያ በኋላ አወቀች። የፈረንሣይ መንግስት በጀርመን እስከተወረረበት ቀን እውቅና ሳይሰጥ ቆየ። በኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩ ሚሲዮኖችና ሚሲዮናውያን ሁሉ ሌጦአቸውን ገልብጠው ከጣልያን ጋር ተስማሙ። አብዛኞቹ ቀድሞውንም የጣልያን ሰላይ ስለነበሩ አፈፃፀሙ ሥምረት አገኙ። የስዊድን ሚስዮን ብቻ ሚስዮኑን ዘግቶ ከሀገር ወጣ።

ኢትዮጵያ ድል በመሆንዋ የዲፕሎማቲኩ ትግል አላቋረጠም። ከኢትየጵያ ከወጡ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ ከኢየሩሳሌም ግንቦት 11 ቀን 1928 ዓ.ም ለዓለም መንግሥታት ማኅበር ቀጣዩን አቤቱታ አቀረቡ። አቤቱታውም "...የኢትዮጵያ ሕዝብ ፈጽሞ...ታይቶ፣ ተሰምቶ በማያውቅና በማይመዛዘን፣ ከሰው የተፈጥሮ ባሕርይ የተላለፈ የግፍ ጦርነት እንዳያልቅ..."በሚል ኃይል ሰቆቃውን ከገለጸ በኋላ፤ ኢጣልያ የውል ግዴታዎችን ጥሳ ገዥ ነኝ የምትለውንና ግዛት ማስፋፋትዋን ማኅበሩ እንዳያውቅላት የሚጠይቅ ነበር። ነገር ግን አንዳች ፋይዳ አላስገኘም።

በአውሮፓ ጋዜጦች ነፃነት እንዳላቸው፤ ነገር ግን ይህ ነፃነት የኢትዮጵያን ጉዳይ በእውነተኛ መልኩ ለመግለጽ አስችሎአቸው ·አያውቅም። የሮም ካቶሊክ ሊቀ ጳጳስ በኢትዮጵያ ላይ እንዲፈስ የተዘጋጀውን የመርዝ ጋዝና ሌላውን መሣሪያ ሁሉ ባርከው ጦርነቱን ሲፈቅዱ፤ ከስዊዲኑ ጋዜጣ ከአሌክሳንድሪያ በስተቀር አንዳች እንዳልተነፈሱ ሁሉ፤ ጣልያን በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ስለሚያካሄደው ጭፍጨፋ አንዳች አልተናገሩም። እንዲያውም የዓለምን ጆሮ የሚያደነቁሩት የጣልያን ወረራ እንደተቃና አዘውትረው በመግለጽ ነበር።

ንጉሠ ነገሥቱ ከለንደን ወደ ጄኔቭ በመሄድ ሰኔ 23 ቀን 1928 ዓ.ም የኢትዮጵያን አቤቱታ ለዓለም መንግሥታት ማኅበር አቀረቡ። ንግግር ያደረጉት በአማርኛ ቋንቋ ነበር። ንግግራቸው ወዲያው በእንግሊዝኛና በፈረንሣይኛ ቋንቋ እየተተረጐመ ለጉባዔው ተሰማ። ንጉሠ ነገሥቱ በዚህ ንግግራቸው በኢትዮጵያ የተካሄደውን በደልና በሕዝብ ላይ የደረሰውን እልቂት ለጉባዔው በቂ በሆነ አገላለጽ አስረዱ። ኢጣልያ በአይሮፕላኖችዋ ላይ የኢፕሪት መርዝ የሚረጭ መኪና አዘጋጅታ፤ ሰፊ በሆነ አገር ላይ ሞት

የሚያመጣ ረቂቅ ዝናም እንዳወረደችበት ገለጹ። ዋና የጦር መሣሪያ ያደረገችውም ይህንኑ እንደሆነ አስታወቁ። የመርዙ ዝናም የዘነበበትን ውሃ የጠጡ፣ መርዙ የነካውን ምግብ የተመገቡ ሰዎችም ከብቶችም በታላቅ ሥቃይ እንደአለቁ አስታወቁ።



ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በጄኔቭ ታሪካዊውን ንግግር ሲያደርጉ።


መስከረም 23 ቀን 1928 ዓ.ም ጄኔቭ የተቀመጠው የአሥራ ሦስት አገሮች ኮሚቴ "የኢጣልያ መንግሥት የማኅበሩን ውል ቃል ማፍረሱንና አጥቂ መሆኑን" እንደ አረጋገጠ ለጉባዔው አስታወሱ። ማኅበሩ "...ከሕግ ተላልፎ የሚሠራ ሥራ እንዲፈረስ፣ በማኅበሩ የተጻፈው ቃል ሁሉ እንዲፈጸም እናደርጋለን" ተብሎ በጥቅምት ወር 1928 ዓ.ም ቃል ገብቶላቸው የነበረውን ጠቀሱ። መሣሪያ እንዳይገዙ መከልከላቸውን አወሱ። በማኅበሩ ደንብ "መንግሥታት እየተባበሩ በመረዳዳት ጸጥታ እንዳይጠፋ ያደርጋሉ የተባለው የአፈጻጸሙ ትርጓሜ ምን ይሆን?" ብለው ጠየቁ። መልስ የሰጠ አልነበረም። በመጨረሻም "...ከእግዚአብሔር መንግሥት በስተቀር የፍጡር መንግሥት ሁሉ አንዱ ከአንዱ አይበልጥም ...እግዚአብሔርና ታሪክ ለምትሰጡት ፍርድ ምስክር ሆነው ይመለከታሉ..." አሉ። የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ በኃይል የተደረገባቸውን ነገር አለመቀበላቸውን፤ ሥርዓት እንዲሰፍን፣ የመንግሥታት ማኅበር ውል እንዲከበር፣ የሚገባቸው ሥልጣንና ግዛት እንዲመለስላቸው የሚቻላቸውን ሁሉ እንደሚያደርጉ ገለጹ። በኢትዮጵያ የደረሰባት በሌሎች ታናናሽ መንግሥታት እንደሚደርስ አስጠንቅቀው "...የኢትዮጵያ ነፃነት እንዳይጠፋ፣ ግዛትዋም እንዲከበር ምን ዓይነት ዕርዳታ ለማድረግ አስባችኋል?" ብለው በመጠየቅ ንግግራቸውን ደመደሙ።[2]



የንጉሠ ነገሥቱ ንግግር የዓለምን ሕዝብ ኅሊና በዘበዘ። በዓለም ጋዜጦችም ተስተጋባ። እውነትን የያዘና ለትክክለኛ ፍርድ የቀረበ ነበር። ለታናናሽም ለታላላቅም መንግሥታት ምክር የሰጠ ነበር። ነገር ግን የዓለም መንግሥታት አላደመጡም። ጆሮዎቻቸው በጸም ተሞልተው ነበርና።

ሙሶሊኒ የኃይል ሥራ ኢትዮጵያን ለመግዛት እንደ አላስቻለው፤ የዲፕሎማሲውም ጉዳይ እንደከበደው በተገነዘበ ጊዜ ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ጋር የምሥጢር ንግግር ከፈተ። ለንደን ተጽዕኖ እንዲያደርግባቸው፣ ፓሪስ ያለው አምባሳደሩ ንጉሠ ነገሥቱ ሥልጣናቸውን ለመልቀቅ እንደተስማሙ አድርጐ አወራ። መሐመድ ኢክሪም ሪዛ የሚባል የግብፅ መሥፍንና አባ ሣይሪል ሲ.ማርቲንጊል የተባለ የካቶሊክ ሊቀ ጳጳሱን በመወከል ከጉዳይ ገቡ። የሙሶሊኒ ሃሳብ መኖሪያ ቤት ገዝቶ በመስጠት እና አሥር ሚሊዮን ሊሬ /አንድ ሚሊዮን ፓውንድ/ በመክፈል የሥልጣን መልቀቂያ ውል አስፈርሞ ለመገላገል ነበር።[3] ነገር ግን ንጉሠ ነገሥቱ አልተበገሩም። "እኔ ሳገሬና ለሕዝቤ ፍርድ ለመጠየቅ መጣሁ እንጂ፣ ሀገሬን ለመሸጥ አይደለም። የኢትዮጵያ ታሪክ በኢትዮጵያውያን ደም በተነከረ ጊዜ አያድፍም" አሉ። የእንግሊዝ ሊቀ ጳጳስ ሐውስ ኦፍ ሎርድስ በሚባለው ምክር ቤት ግንቦት 18 ቀን 1929 ዓ.ም ተገኝተው የንጉሠ ነገሥቱን ሃሳብ በመደገፍ ንግግር አደረጉ። ምክር ቤቱም የኢጣልያን ይዞታ ሳያውቅ ቀረ።[4] በዚህ አደራረግ ንጉሠ ነገሥቱ ኢትዮጵያን ከውርደት፣ ኢትዮጵያውያንን ከጥፋት አዳኑ።

ጣልያን ከጀርመን ጋር ወዳጅነትዋን ቀጠለች። ሁለቱ አገሮች በነገሥታት ይተዳደሩ በነበረ ጊዜ ተቀናቃኝነትና ለጠላትነት የሚያበቃ የጥቅም ግጭት ነበሩአቸው። ነገር ግን ፋሺዝምና ናዚዝም ከሰፈኑ በኋላ ከሚያጋጩአቸው ይልቅ የሚያፋቅሩአቸው ጉዳዮች በረከቱ። ለሂትለር ኢጣልያ በመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ጊዜ በጀርመን ላይ ክፈጸመችው ክህደት ይልቅ፣ በመጭው ጦርነት የምትሰጠው ድጋፍ የሚበልጥ ሆኖ ታየው። ክህደት ለጣልያን የባህርይ ጉዳይ መሆኑን አልተገነዘበም። ሙሶሊኒና ሂትለር ስለዚህ ክህደት ቀደም ብሎ በሕዝብ መንፈስ ሠርጾ የነበረውን ስሜት ለመፋቅ ልዩ ጥረት አደረጉ። ሥልጣን በመያዝ ሙሶሊኒ ይቀድመው ነበርና ሂትለር ክብር ሰጠው። ጀርመንን እንዲጐበኝ ጋበዘው። በዚህም መሰረት ሙሶሊኒ መስከረም 14 ቀን 1930 ዓ.ም /ሴፕቴምበር 24 ቀን 1938/ በርሊን ሄደ። ሁለቱ መሪዎች ሦስት ሚሊዮን የጀርመን ወታደር በተሰለፈበት አደባባይ ላይ ቆመው ንግግር አደረጉ። ሙሶሊኒ በመካከላቸው የተገኘው የአንድ አብዮታዊ ሕዝብ መሪ በመሆኑ እንደሆነና፤ የፋሽስትን አብዮት ከናዚ አብዮት ጋር በጥብቅ እንዲቆራኝ ለማድረግ መሆኑን ገለጸ። ብዛታቸው እስከ አንድ መቶ አሥራ አምስት ሚሊዮን የሚደርሰው የጣልያንና የጀርመን ሕዝቦች ጠላቶቻቸውን አሸንፈው ዓለምን በአዲስ ሕግ ማስተዳደር እንደሚችሉ አስገነዘቡ። ሕዝቡም አመነ።



ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በጄኔቭ ታሪካዊውን ንግግር ሲያደርጉ።

ሞሶሊኒ ብድር ለመመለስ ሂትለርን ጋበዘው። ሂትለር ደግሞ ሚያዝያ 24 ቀን 1930 ዓ.ም /ሜይ 2 ቀን 1938/ ኢጣልያን ለመጐብኘት ሮም ገባ። ነገር ግን የሮሙ ጉብኝት እንደ በርሊኑ ለሁለቱ ወንበዴዎች መፈንጫ ነፃ አልተለቀቀም። የኢጣልያ ንጉሥ ቫልሣዊ ኢማኑኤል በርዕሰ ብሔርነቱ ሂትለርን ተቀብሎ ኩይሪርሊ በተባለው ቤተ መንግሥቱ አስተናገደው። ሙሶሊኒ በገዛ ግብዣው ሁለተኛ ሰው ሆነ። በገዛ ዳቦዬ ልብ ልቡን አጣሁት እንዲሉ። ሂትለርን ለማነጋገር የቻለው በጉብኝቱ መጨረሻ ጊዜ ብቻ ነበር።[5] ሆኖም ጉብኝቱ ዓላማውን አልሳተም። በሁለቱ መንግሥታት መካከል ትብብር እንዲፈጠር የሚጠይቁ ብዙ ጉዳዮች በንግግሩ ወቅት ተከሰቱ። በጀርመን በኩል በቬርሳይ ቤተ መንግሥት በአንደኛው የዓለም ጦርነት በድል አድራጊዎቹ መንግሥታት አስገዳጅነት የተፈረመው ውል እንዲፈርስ ከፍተኛ ፍላጐት ነበር። ይህ ውል የኢጣልያን የግዛት ማስፋፋት ጥማት አላረካም ነበርና በመፍረሱ መስማማት አላዳገተም።

የቬርሣይ ስምምነት የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት አክትሞ የተዘጋበት የመሆኑን ያህል፣ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት የተከፈተበት ቁልፍ ስለሆነ ዝርዝሩን መመልከት ብልህነት ይሆናል። ይህ ውል ከባድ የጦር ካሣ በጀርመን ላይ ጣለ። አከፋፈሉም በገንዘብ እንዲሆን ተደረገ። ይህ ሁኔታ የጀርመንን ኢኮኖሚ ገደል ለቀቀው። የጀርመንን ሕዝብ አስመርሮ የሂትለር መሣሪያ እንዲሆን አደረገው። ዳንዚንግ የተባለችውን ከተማ ከጀርመን ወደ ፖላንድ አዞሩአት። በአፍሪካም የነበሩት የጀርመን ቅኝ ግዛቶች ነፃነት በማግኘት ፈንታ፣ ከጀርመን ተነጥቀው ታንዛንያና ናምቢያ ለእንግሊዝ፣ ቤኒንና ቶጐ ለፈረንሣይ ተሰጡ። የእነዚህ ሁኔታዎች መስተካከል ለጀርመን አስፈላጊ ነበር። በጣልያን በኩል ደግሞ አልባኒያ ወደ ኢጣልያ አለመጠቃለልዋ፣ ናይሥና ሣቮይ የተባሉት ግዛቶች በፈረንሣይ እጅ መቆየታቸው ቁጭት ፈጠረ። ለዚህ ሁሉ ቅሬታ መቅረፊያና ሁለቱ መንግሥታት ለሚያደርጉት ትብብር መነሻው፣ ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ ያላትን ገዥነት ጀርመን የማወቅዋ ጉዳይ ሆነ። ስለዚህ የኢጣልያ ንጉሥ ስለሙሶሊኒና ሂትለር ስምምነት አንዳች ለማለት አልቻለም።

ሁኔታው አስፈሪ ሆነ። እንግሊዞች ጣልያንን ማባበል ያዙ። ሃሳባቸው ሊሆን ከእነሱ እንድትሆን፣ ካልሆነም ገለልተኛ እንድትሆን ነው። በዚህም መሰረት ሚያዝያ 8 ቀን 1931 ዓ.ም ስምምነት ተፈራረሙ። ግብፅም ከስምምነቱ ገባች። መታረቂያዋ ኢትዮጵያ ነበረች። እንግሊዝና ግብፅ የሱዳን ጥምር ገዥዎች እንደሆኑ፣ ሱዳን ደግሞ ከኢጣልያ የምሥራቅ አፍሪቃ ቅኝ ግዛት አዋሳኝ እንደሆነች በውሉ ተንጸባረቀ። ዋናው ጉዳይ "እንግሊዝ በዓለም መንግሥታት ማኅበር ላይ የኢትዮጵያን ሁኔታ ትጨርሳለች" የሚለው ቃል ነበር። እውነትም እንግሊዝ ኢጣልያ ኢትዮጵያን በመያዝዋ ረገድ፣



መንግሥታት የየበኩላቸውን እርምጃ ቢወስዱ እንደማትቃወም በማኅበሩ ጉባዔ ላይ አስታወቀች። እርስዋ ራስዋም የኢትዮጵያን በኢጣልያ መያዝ አወቀች።[6]

ነገር ግን የኢጣልያ፣ የጀርመንና የጃፓን ወዳጅነት ዳበረ። ወደ ጓደኝነትም ፈጥኖ ተሸጋገረ። ሙሶሊኒ በኢትዮጵያ ላይ ያለውን ይዞታ ካላወቁለት፣ ማናቸውንም የዓለም ማኅበር የሚያቀርበውን ሃሳብ እንደማይቀበል አስታወቀ። ጀርመን ከስብሰባዎች መቅረት አብዝታ ነበርና፣ ጀርመን በማትካፈልበት በማናቸውም ስብሰባ ኢጣልያ እንዳትገኝ አደረገ። በወቅቱ በእስፔን ሀገር ጦርነት በመካሄድ ላይ ስለነበር፣ ጣልቃ መግባት ወደ አዲስ ሁከት ያመራል አለ። ጃፓን በቻይና ላይ በምትፈጽመው ሁሉ ኢጣልያ እንደምትደግፋት አስታወቀ። እነዚህን ሃሳቦቹን ጽፎና ፈርሞ በሕዝብ መገናኛ እንዲገለጹ አደረገ።[7] እንዲሁ እንዲሁ ብለው ሦስቱ መንግሥታት ማለትም ጣልያን፣ ጀርመንና ጃፓን የዓለም ማኅበርን ከነጭራሹ ለቅቀው ወጡ።

ሂትለር የጦር ክንዱን አንስቶ ታናናሽ ሀገሮችን የመዋጥ ሥራውን ነሐሴ 25 ቀን 1931 ዓ.ም /ሴፕተምበር 1 ቀን 1938/ ጀመረ። ኢትዮጵያ ጣልያንን የተቋቋመችትን ሩቡን ያህል የተቋቋመ የለም። መሪዎቹም አንድ በአንድ እየበረሩ እንግሊዝ አገር ገቡ እንጂ ለዓለም ማኅበር ስሞታ አላቀረቡም። ለንደን በየዕለቱ በአይሮፕላንና በበራሪ ፈንጂዎች ትደበደብ ጀመር። ዓለሙ ተናወጠ። ሙሶሊኒ ከማንኛው ወገን እንደሚሆን ጨነቀው።

ጀርመን መላውን አውሮፓን ከያዘችና ለንደንን በአይሮፕላን አንጀትዋ እስኪርስ በመደብደብ እንግሊዝን ከአስደነገጠች በኋላ፣ ጦርነቱ እንዲቆምና የሰላም ስምምነት እንዲደረግ ጠየቀች። ይህ ጥያቄ ተቀባይነት አግኝቶ ቢሆን ኖሮ፣ የዓለም ካርታና የፖለቲካ አቅጣጫ ይለወጥ ነበር። ነገር ግን እንግሊዝ ጥቃትዋን ጠጥታ አይደረገም አለች። "ድል እስከምናገኝ ድረስ ጦርነቱ ይቀጥላል እንጂ አይቆምም" አለች። ቆራጥ መንግሥትና ጠንካራ ሕዝብ እንዲህ ነው። እንደ አለችውም ጦርነቱ ቀጠለ። ዓለም አሁን ያለበትን ገጽታ የያዘበት በር ተከፈተ። የኢትዮጵያም ነፃነት አብሮ ተስፋ ፈነጠቀ።

ጀርመን እያየለ ሲሄድ በፈረንሣይ አገር በማርሻል ፔቴ የሚመራ መንግሥት ተቋቋመ። አዲሱ መንግሥት ከጀርመን መንግሥት ጋር ስምምነት ተፈራረመ። በዚህ ስምምነት መሠረት የፈረንሣይ የምድር፣ የባሕርና የአየር ኃይል፣ ወደቦችም ጭምር በጀርመን እጅ ሆኑ።

ከእንግሊዝ ወይም ከጀርመን መሆኑን ሙሶሊኒ በገሐድ እንዲያስታውቅ ሂትለር አስጨነቀው። አሥራ አራቱ ሚኒስትሮች ከሁለት ተከፈሉ። ሰባቱ፣ እማቹን ከንትቺያኖን ጨምሮ፣ ከእንግሊዝ እንሁን አሉ። ሌሎች ሰባት ከጀርመን መሆንን መረጡ። ስለዚህ ሙሶሊኒ ራሱ መወሰን ግድ ሆነበት። ምክንያቶቹ ጀርመን ጐረቤታችን ነው፣ የርዕዮተ ዓለም ጓደኛችን ነው፣ በትግላችን ሁሉ ደግፎናል፣ የኃይል ሚዛን አግኝቶአል። በቅርቡ ደግሞ የአውቶማቲክንም ምሥጢር ያገኛል የሚሉ ነበሩ። ተቃዋሚዎች ሚኒስትሮች

ተቃውሞአቸውን ስለአጠነከሩበት ሰባቱንም፣ አማቹን ጭምር፣ አስገደላቸው። ልጁ ተናድዳ ሄዳ በባልዋ እጅ የነበሩትን ምሥጢሮች በስዊስ በኩል አሣልፋ ለእንግሊዞች ሰጠችበት።[8] በዚህ ዓይነት ኢጣልያ ከጀርመን ጐን ለመቆም ስለወሰነች፤ ይህ ውል ለእሷም የሚጸና ሆነና የጅቡቲ ወደብና እስከ አዲስ አበባ ያለው የባቡር ሐዲድ ጭምር ከኢጣልያ እጅ ገባ።[9] የጀርመንና የጣልያን ጠላት የሆነ አገር ዜጋ ይባረር የሚል ሕግ ስለወጣ፣ ፓሪስ የነበረው የኢትዮጵያ ኢምባሲ ተዘጋ። ሠራተኞቹም በማርሴይ በኩል ወጡ።[10]

ኢጣልያ ከጀርመን ጐን መቆምዋን ስትገልጽ እንግሊዝ ፈጣን እርምጃ ወሰደች። ጦርነቱን ከአውሮፖ ወደ አፍሪካ አዞረችው። ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ከሱንደን ካርቱም አምጥታ በጐጃም በኩል ጐጃም እንዲገቡ አደረገች። የምሥራቅ አፍሪካ ጦር ከሞቃድሾና ከበርበራ ተነስቶ አዲስ አበባ እንዲገባ አሰለፈች። ሌላ ጦር ከካርቱም በከረን አልፎ አሥመራ በመግባት ቀይ ባሕርን እጅዋ ለማድረግ ተነሣች።

አሜሪካን ገለልተኝነትዋን አጠበቀች። ከጦርነቱ ለመግባት አልከጀለችም። በፕሬዚዳንት ዊልሰን የደረሰው እንዳይደርስባቸው ስለሰጉ ፕሬዚዳንት ሩዝቬልት አንዳች ከማድረግ ይቆጠቡ እንጂ፤ የጦርነቱን ባሕርይ ለሕዝባቸው ከማስረዳት አልቦዘኑም። ለነፃነታቸው የሚዋጉትን ሕዝቦች መርዳት እንደሚገባ በማስረዳት ቅስቀሳ አደረጉ። ያዳመጣቸው ግን የለም። አዲሱ የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስተር ሰር አንቶኒ ኤደን ስለጦርነቱ ለአሜሪካን ምክር ቤት ንግግር ቢያደርጉም፤ የጦር መሣሪያ ዕርዳታ ከማግኘት በስተቀር ሕዝቡን ወደ ጦርነቱ ለማስገባት አልቻሉም። ጦርነቱ ለአሜሪካንም ጤና እንደማይሰጥ የተናገሩት ትንቢት እስኪደርስ በትዕግስት መጠበቅ ነበረባቸው።

የአውሮፓና የአሜሪካ ሁኔታ በእንዲህ እንዳለ ከሩቅ ምሥራቅ ጐርናና ድምጽ ተሰማ። የጃፓን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በጥር ወር 1933 ዓ.ም ባደረገው ንግግር "...አሜሪካ ጃፓንን ስለምትረዳ በጃፓንና በአሜሪካ መካከል ሰላምና ፍቅር ሊኖር አይችልም..." አለ። ከፓስፊክ ውቅያኖስ ምዕራቡ ክፍል በጃፓን ሥልጣን ሥር ሊሆን እንደሚገባ አስታወቀ። የአሜሪካን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርም ወዲያው መልስ ሰጡ። "ከጃፓን ጋር ሰላም አይገኝም..." አሉ። ኢትዮጵያን ያቃጠላት እሳት ኢትዮጵያን መልሶ እንደሚፈውሳት ትንቢት ተናገሩ።[11] በዚያን ሰዓት ኢትዮጵያን ነፃ ለማውጣት ጦርነቱ በአራቱም የሀገሪቱ ማዕዘን ተቀጣጥሎ ነበርና ትንቢታቸው እውን ነበር። ጃፓን ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ፐርል የተባለውን የአሜሪካን ወደብ በድንገት በአይሮፕላን ደብድባ፤ በአሜሪካን የባህር ኃይል ላይ ከፍተኛ ጉዳት አደረሰች። አሜሪካንም ከጦርነቱ ሰተት ብላ ገባች።

ኢትዮጵያ ከነገር አሽክላ ሳትወድቅ በኢጣልያ ከደረሰባት ወረራ ነፃ ወጣች። አውሮፖ የኢትዮጵያን ነፃነት በሀፍረት መልሶ አወቀ። ቀዳማዊ



ኃይለሥላሴ በጀኔቫ የተናገሩት ትንቢት በትክክል ተፈፀመ። አድላዊ ዳኛ የሚደርስበትን ፍዳ ተቀበለ። ሙሶሊኒ ወልወል ባቀጣጠለው እሳት መላው ዓለም ተጠበሰ።

## <u>ማጣቀሻ ፅሑፎች</u>


1. ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ*፣ ገጽ 211።
2. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ 1ኛ መጽሐፍ*፣ ገጽ 178-182፣ ገጽ 253-264።
3. Alberto Sabacchi, *Ethiopia under Mussolin*, pp. 221-126.
4. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ 2ኛ መጽሐፍ*፣ ገጽ 81-93።
5. Stanley Cooperman, *Mussolini*, pp.109-110.
6. ሕይወት ኀዳሩ፣ *ያቺ ቀን ተረሣች*፣ ገጽ 73።
7. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 326-349።
8. Mussolini's Twilight.
9. ሕይወት ኀዳሩ፣ ገጽ 354-362።
10. አክሊሉ ሀብተወልድ ለመርማሪ ኮሚሽን ያቀረቡት ጽሑፍ፣ ገጽ 12-16።
11. ሕይወት ኀዳሩ፣ ገጽ 389-396።

# ምዕራፍ ሃምሣ ሁለት
# የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የድል ጉዞ

የኢጣልያ የፖለቲካ አቅዋም እያጠራጠራቸው በሄደ ቁጥር፤ እንግሊዞች የመጠባበቂያ ዕቅድ ማዘጋጀት ያዙ። ካይሮ በነበራቸው ጦር ዕዝ ውስጥ ቢያስፈልግ የጣልያንን የቅኝ ግዛት ማፈራረስ የሚቻልበት ጉዳይ ጥናት ተደረገበት። አንዱ በሊቢያ በኩል ሲሆን፣ ሌላው በምሥራቅ አፍሪካ ላይ ያተኮረ ነበር። ከምሥራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛት አገሮች፣ ዋናዋ ኢትዮጵያ ሆነች።

በዚህ ጥናት በብርቱ ከታሰበባቸው ጉዳዮች አንዱ የመሪ ጉዳይ ነበር። ፈረንሣዮች መጠነኛ ቅሬታ ቢያሳዩም ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መሪነት ሌላ ተወዳዳሪ ሳይገኝለት ቀረ። ራስ አበበን ለመደገፍ ቢሞከር በኢትዮጵያ ውስጥ የርስበርስ ጦርነት የሚቀሰቅስ ሆነ። ስለዚህ ጣልያን ከጀርመን ጐን ከቆመች ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ይዞ ኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ከመክፈት በስተቀር ሌላ አማራጭ ሳይገኝ ቀረ።

እንግሊዞች በዚህ ላይ እንደአሉ፣ ሙሶሊኒ ሰኔ 3 ቀን 1932 ዓ.ም ከሂትለር ጐን ለመቆም ወሰነ። ወጥመዳቸው ስለያዘላቸው እንግሊዞች ፈጣን እርምጃ ወሰዱ። በእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥ የኢትዮጵያ ጉዳይ ኃላፊ የነበረው ሚስተር ቶሚ ቶምሶን፣ ንጉሠ ነገሥቱ ባለሥልጣኖችን የሚያነጋግሩበት መንገድ አዘጋጀ። በታላቁ ምዕራባዊ ሆቴል ንግግር ከተደረገ በኋላ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ሱዳን የሚሄዱበት መንገድ ተቀየሰ።

ንጉሠ ነገሥቱ ኢትዮጵያን ነፃ የማውጣት ጉዞአቸውን ለመጀመር ከእንግሊዝ አገር ሰኔ 17 ቀን 1932 ዓ.ም /ጁን 24 ቀን 1940/ ከሌሊቱ በ4 ሰዓት ከለንደን ተነሱ። ጉዞአቸው የጦርም የነገርም ሆነባቸው። ጉዞው በአይሮፕላን ሆኖ በረራው በምሥጢር ነበር። አይሮፕላን ነጂው እንኳን ከሚሄድበት አገር በስተቀር ስለመንገደኞቹ የሚያውቀው ነገር አልነበረውም። አይሮፕላኑም በውሃ ላይ ተንሳፋፊ ነበር። አይሮፕላኑ በፈረንሣይ አየር ላይ አቋርጦ ማልታ ደሴት ላይ ማረፍ ነበረበት። የጀርመን አይሮፕላኖች የፈረንሣይ አገርን፣ የጣልያን አይሮፕላኖች ደግሞ የሜዲቴራኒያን ባህርን አየር በመቆጣጠር ላይ ነበሩ። በተአምር አንዳቸውም ሳያዩአቸው ቀርተው ማልታ ደሴት ላይ አረፉ። ሌላው አስገራሚ ነገር የማልታ አይሮፕላን ማረፊያ ከጥቂት ጊዜ በፊት በጣልያን አይሮፕላኖች ተደብድቦ መገኘቱ ነው። በቶሎ ነዳጅ ሞልተው በረራቸውን ወደ ግብፅ ቀጠሉ። በማግስቱ ከቀትር በኋላ እስክንድርያ ገቡ። ነገር ግን በግብፅ የነበሩ ባለሥልጣኖችን ለማነጋገር ሁኔታው አላመቸም። በማግስቱ የበረራው ጉዞአቸውን ቀጥለው ሰኔ 19 ቀን



ከሱዳንና ከግብፅ ጠረፍ ላይ ከምትገኝ ዋዲ ሐይፋ ከተባለች ትንሽ ከተማ ገቡ።

የንጉሠ ነገሥቱ ጉዞ በምሥጢር በመሆኑ ባለሥልጣኖች አይሮፕላኑ ከእስክንድሪያ እስኪነሳ አልተገለጸላቸውም ነበር። በሰሙ ጊዜ ደነገጡ። አንቀበልም ለማለት ቃጣቸው። ግልጹ ምክንያታቸው ከኢጣልያ ምሥራቅ አፍሪካ ጋር ያጋጨናል የሚል ሲሆን፤ ንጉሠ ነገሥቱን ያለመቀበል ሌላ ምሥጢር ሳይኖርበት አልቀረም። ከእንግሊዝ አገር ይዞአቸው ከመጣው ቡድን ጋር ንግግር ተደርጐ ከስምምነት እስኪደረስ ድረስ ንጉሠ ነገሥቱ ዋዲ ሐይፋ መቆየት ነበረባቸው።

ከዚያ እንደ አሉ እንግሊዞች አንድ ዓይነት ውል እንዲፈርሙላቸው ለማድረግ ከጀሉ። ጠርጣራው ንጉሠ ነገሥት ከመኳንንቶቻቸው ጋር መክረው እንደሚፈርሙ ገለጹ። መኳንንቱን ከየአሉበት ሰብስበው አመጡላቸው፤ ካርቱም ከተማም አስገቡአቸው። ካርቱም ሲደርሱ ደግሞ ስለ ጦር እንጂ ስለ ፖለቲካ ጉዳይ የማይነጋገሩ ሆኑ። ኬንያ ያለው ስደተኛ አንዋጋም ብሏል አሉዋቸው። ከለንደን ጌታ ሎሬንዞ ታዕዛዝን ልከው ችግር አለመኖሩን አረጋገጡ። እንግሊዞች በደቡብ ኢትዮጵያ ብጥብጥ ለማስነሣት ያዘጋጁትን ብሮክ ላህርስት በተባለ ኰሎኔል የሚመራ አንድ ቡድን አንቀሳቀሱ። ንጉሠ ነገሥቱ እንዲያነጋግሩት ቢጠየቁ አላደርገውም አሉ። ንግግር በተለይ ስለ ጦርነቱ ጉዳይ ብቻ እንዲሆን፣ የፖለቲካ ጉዳይ ንግግር የሚደረገው አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ እንዲሆን አደረጉ። እነዚህ ሥራዎች ኢትዮጵያን ከእንግሊዝ የነገር ጭንጉት አላቀቁአት።

ንጉሠ ነገሥቱ የመጀመሪያውን የጦር አመራር በዋዲ ሐይፋ ሰጡ። የመጀመሪያው ዙር ንግግር ሰኔ 21 ቀን 1932 ዓ.ም ተጀመረ። እንግሊዞች በእጃቸው ያለው መሣሪያ እጅግ አነስተኛ መሆኑን ገለጹ። ሊገኝ የሚችለው 176,000 ጠመንጃ፣ 4 ሞርታሮች፣ 400 መትረየስ፣ 60 ጸረ ታንክና 45 ከጣልያኖች የተማረኩ ታንኮች እንደሆኑ ተገለጸ። ይህ አካሄድ በአንድ ወገን የተስፋ ጭላንጭል አሳይቶ በሌላ ወገን ይህንን በመሰለ ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታ ንጉሠ ነገሥቱን አንዳች ውል ለማስፈረም ሳይሆን አልቀረም። ነገር ግን ንጉሠ ነገሥቱ ከዚች ወጥመድ አልወደቁም። በእየሩሳሌም፣ በጁቡቲ፣ በከሰላ፣ በኬንያና በሌሎችም በታዎች የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች በቅድሚያ እንዲመጡላቸው ጠየቁ። ይሆንላቸው መስሎአቸው እንግሊዞች ጥያቄአቸውን ፈጸሙላቸው። እሳቸውንም ሰኔ 25 ቀን በመኪና ወደ ካርቱም ወስደው ከካርቱም ሃያ ስምንት ማይልስ ከሚርቅ በነጭ ዓባይ አጠገብ ከምትገኝ ደቦል አውልያ ከምትባል ቦታ እንዲቆዩ አደረጉ።

ንጉሠ ነገሥቱ ሱዳን እንደገቡ የመጀመሪያው ሥራ መምጣታቸው በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ እንዲታወቅ ማድረግ ሆነ። በዚህ ጉዳይ እንግሊዞች ተባበሩ። ንጉሠ ነገሥቱም በካርቱም ሬዲዮ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ

መልእክት አስተላለፉ። የመጀመሪያው ቃል "ይህ የምትሰሙት የእኔ የንጉሠ ነገሥታችሁ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ድምፅ ነው..." በማለት ጀምሮ፣ የተመኙትን ዕርዳታ አግኝተው የደረሱለት መሆኑን የሚያበሥር ነበር። በተጨማሪም የእንግሊዝና የፈረንሣይ አይሮፕላኖች በኢትዮጵያ አየር ላይ እንደሚያንዣብቡ ገልጸው፣ የጣልያን እግረኛ ወታደር ከኢትዮጵያ ጀግኖች እንደማያልፍ አስረዱ። ባንዶችን በተመለከተ "...ከእንግዲህ ወዲህ የጣልያን መሣሪያ በመሆን አገራችሁን የምትበድሉ ለዘራችሁ ከታሪካችሁ የማይፋቅ እርግማን ታቆያላችሁ..." አሉ።

በሐምሌ 1 ቀን 1932 የመጀመሪያው አዋጅ ተጽፎ በአይሮፕላን ተበተነ። አዋጁ ብዙ ታላላቅ ጉዳዮችን ያካተተ ሆኖ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ሹማምንት፣ ለኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች፣ ለኤርትራውያንና ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተላለፈ ነበር። አጠቃላይ ይዘቱ "...የምሕረት ፊቱን ወደ እኛ ስለመለሰ እግዚአብሔርን እናመሰግናለን..." ይልና ለእያንዳንዱ ወገን መመሪያ ይሰጣል። "...በአፋችሁም ለጠላት መሣሪያ አትሁኑ። ...ስለ ሀገራችሁ ጥቅም በሥራ በርቱ። ...ከመረብ ወዲያ ወይም ወዲህ ያላችሁ ሁሉ ከኢትዮጵያውያን ወንድሞቻችሁ ጋር ተባበሩ። ...ነፃና ሀብታም በሆነች በአንዲት ኢትዮጵያ ውስጥ ነፃነት፣ እኩልነት፣ አንድነትና እውቀት ያለው ሕዝብ ሆናችሁ እንድትኖሩበት እንፈልጋለን። ...የጣልያንን ጦር ለመደምሰስና የኢትዮጵያን ሙሉ ነፃነት መልሶ ለማቋቋም ነው እንጂ፣ እንግሊዞች በአገራችን የሚፈልጉብን ነገር የለም..." የሚል ነበር። በመጨረሻም የኢትዮጵያ ሕዝብ እንግሊዞችን በወዳጅነት እንዲቀበላቸው አደራ ነበረበት።

እንግሊዞች ከኢትዮጵያውያን ጋር በመሆን "ባንዲራችን" የሚል ሣምንታዊ ጋዜጣ በሱዳን አቋቋሙ። ከንጉሠ ነገሥቱ አዋጅ ጋር በተከታታይ እየታተመ በአይሮፕላን ተበተነ። አይሮፕላን ቢወድቅ ለነጂዎቹ መታወቂያ እንዲሆናቸው የተለየ ቅጂ በአይሮፕላኖቹ ውስጥ ለዘወትር እንዲቀመጥ ተደረገ። አዋጁ በትግርኛም ተተርጉሞ ተበተነ። ባንዲራችን የተባለው ጋዜጣ ለሃያ ስምንት ሣምንታት በተከታታይ ታትሞ ተበተነ። አዋጁና እነዚህ ጽሑፎች በብዛት መበተናቸው የኢትዮጵያን ህዝብ ለአዲስ ትግል ቀሰቀሰው።

ወደ ኢትዮጵያ ስለሚደረገው ጉዞ ምክር ሐምሌ 5 ቀን 1932 ዓ.ም በኢትዮጵያውያን መካከል፣ በንጉሠ ነገሥቱ ሰብሳቢነት ተጀመረ። የወቅቱ አዲስ ነገር፣ የፈረንሣይ በጀርመን እጅ መውደቅ ነበር። በስብሰባው ላይ እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ /ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ/፣ ፊታውራሪ ብሩ ወልደገብርኤል፣ ደጃዝማች አበበ ዳምጠው፣ ደጃዝማች /ራስ/ አደፍርሰው፣ አቶ /ፀሐፊ ታዕዛዝ/ ወልደጊዮርጊስ ወልደዮሐንስና አቶ /ብላቴን ጌታ/ ሎሬንዞ ታዕዛዝ ተገኝተው ነበር። አቶ /ብላቴን ጌታ/ ሎሬንዞ ታዕዛዝ ኢትዮጵያ ውስጥ በቆዩበት ጊዜ የተገነዘቡትን ካሳወቁና ቀደም ብሎ ከገባው የእንግሊዝ ጦር መሪ በኰሎኔል /ብርጋዲየር ጄነራል/ ሳንድፎርድ ሐምሌ 4 ቀን የተፃፈው ቃል



ከተሰማ በኋላ፣ በጉዳዩ ከእንግሊዝ ባለሥልጣኖች ጋር ንግግር እንዲደረግ ተወሰነ። አሁን ግን ጊዜው የተለወጠ ነገር ስለአመጣ በጥቂት ሆኖ ሔዶ መርምሮ እንዲመጣ ተቆርጦአል፣ በማለት ስብሰባውን ደመደሙ።[1]

ከእንግሊዙ የሱዳን አገረ ገዥ፣ ከሰር እስቲዋርት ሲመስ ጋር በቆይታ፣ በተለይ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ሐምሌ 6 ቀን ንግግር አደረጉ። ንግግሩ እንግሊዞች እንደፈለጉት በፖለቲካ ጉዳይ ላይ ሳይሆን፣ ንጉሠ ነገሥቱ ባቀረቡት የጦር ጉዳይ አተኮረ። ስለጦርነቱ በተደረገው ንግግር ከእንግሊዞቹ ወገን የቀረበው መግለጫ ቀደም ብሎ በዋዲ ሐይፋ የተነገረውን መልሶ የሚያስተጋባ ከመሆኑ ጋር፣ የጣልያንንም የኃይል አቅዋም ያስረዳ ነበር። በጣልያን በኩል 900,000 ወታደር እንደ ተሰለፈ፣ ከዚሁ ውስጥ የሚበዛው ነጭ ሲሆን፣ የሠለጠኑም ባንዶች ከጠላት ጐን የተሠለፉ መሆናቸውን የሚያስረዳ ነበር። በመሣሪያም ረገድ 200 አይሮፕላኖች እንደአሉና ጣቢያቸውም አዲስ አበባ፣ አሥመራ፣ ጉርአ፣ ጐንደርና ድሬዳዋ እንደሆነ ተገለጸ። የእንግሊዝ አይሮፕላኖች በጐንደርና በጐጃም ለሚገኙ አርበኞች ድጋፍ ለመስጠት ቦታ እንደሚርቃቸው ተነገረ። በሱዳንና በኢጣልያ ምሥራቅ አፍሪቃ ግዛት መካከል ያለውን 1200 ኪሎሜትር የወሰን ድንበር የሚጠብቁ 4,500 ሱዳናውያን ወታደሮች እንደ አሉ፣ የእንግሊዝ ወታደሮች 2,500 ብቻ እንደሆኑ ተገለጸ። ጄነራሉ ከሱዳን ወደ ኢትዮጵያ ስለሚገባው ጦር የሰጡት መግለጫ ቀድሞ በሠፊው ተዘጋጅቶ ነበር።

ከእንግሊዝ የሚገኘው ዕርዳታ 18,000 ጠመንጃ ብቻ መሆኑ በቁጥር ከታወቀ በኋላ፣ የኢትዮጵያ መኳንንት በንጉሠ ነገሥቱ ሰብሳቢነት ሐምሌ 7 ቀን ስብሰባ አደረጉ። አቶ /ብላቴን ጌታ/ ሎሬንዞ ታዕዛዝ "...ዓለም በጦርነት ስለተበጠበጠና ለእንግሊዝም ቢሆን ፍፃሜው ያልታወቀ ስለሆነ፣ የቀረን እዚህ ሆነን ከመጥፋት በአገራችን በኢትዮጵያ ገብቶ መሞት ነው..." ሲሉ ያቀረቡት ሃሳብ ተደግፎ ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት ተወሰነ።[2] አንድ የኢትዮጵያና የእንግሊዝ ጥምር ቡድን ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ ተመደበ። በኢትዮጵያ በኩል አዛዥ /ደጃዝማች/ ከበደ ተሰማ ተመረጡ። በእንግሊዝ ወገን ኮሎኔል/ብርጋዴየር/ ሣንድፎርድ ሆኑ። እነሱም ፈጣን ዝግጅት ካደረጉ በኋላ ተንቀሳቅሰው መጠነኛ ጦር በመያዝ የሱዳንን ጠረፍ አቋርጠው ሐምሌ 25 ቀን 1932 ኢትዮጵያ ምድር ገቡ።

ሌላው ሥራ በውጭ አገር ያለውን የኢትዮጵያ ስደተኛ ማሰባሰብና ፈጣን ሥልጠና ሰጥቶ ለጦርነት ማሰለፍ ሆነ። ስደተኞቹን ማስመጣት ቀላል አልሆነም። ካይሮ ከሚገኘው የእንግሊዝ ጦር አዛዥ ጄነራል ትዕዛዝ ማስተላለፍ አስፈለገ። ያም ተደርጐ ከኬንያ የእንግሊዝ ባለሥልጣኖች ተቃውሞ ተነሣ። በአንድ ወገን ስደተኞቹ ለንጉሠ ነገሥቱ መዋጋት እንፈልግም ብለዋል ተባለ። በሌላ ወገን ደግሞ እንደምርኮኛ የሚቆጠሩ ስለሆነ እንደገና ከጦር ግንባር እንዳይገቡ የዓለም መንግሥታት ሕግ ይከላከላል

የሚል ሆነ። በመጨረሻ ደግሞ አንዋጋም ያሉት ኤርትራውያን ስደተኞች ናቸው ተባሉ። አቶ /ብላቴን ሎሬንዞ ታዕዛዝ ተልከው ጥቅምት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ሲ ደርሱ ሁሉም ነገር ተለወጠ። አንዱም ወገን አንዋጋም አለማለቱ ስለተረጋገጠ አቶ /ብላቴን ጌታ/ ሎሬንሶ ታዕዛዝ ስደተኞቹ ከንጉሠ ነገሥቱ መጠራታቸውን ብቻ ኅዳር 3 ቀን ለኤርትራውያን ነገሩ። በኤርትራውያን መካከል ደስታ ሆነ። "...ለንጉሣችን ገብተን እንዳንዋጋ ከለከላችሁን፤ እንደ እንስሳም አሠራችሁን..." በማለት ብሶታቸውን ገለጹ። በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ጦር ግንባር 546 ኤርትራውያን ተሠለፉ።[3]

በምሥጢር ቁጥር 101 ወደ ኢትዮጵያ የተላከው ጦር ነሐሴ 14 ቀን ሠራቆ ደረሰ። ከዚያም በገደሪፍ፣ በደይካ፣ በወዲያ፣ በስኡል በጀምበርጌ ማሕደረ ሥላሴ ገባ። ከዚያም ጳጉሜን 4 ቀን 1932 ዓ.ም አቸፈር ገብቶ የጐጃምን አርበኞች ማስተባበር ያዘ።

የጣልያን መንግሥት በሱዳንና በሰሜን ሶማልያ ግንባር ጦር ከፈተ። አይሎም ጋላበትንና ከሰላን፣ እንደዚሁም በርባራን ያዘ። እነዚህን ቦታዎች መጠበቅ አስፈላጊ መሆኑ የኢትዮጵያ የጦር መኰንኖች አቅርበውት የነበረውን አስተያየት፤ የእንግሊዝ የጦር መኰንኖች ቦታዎቹ ለጦርነቱ አስፈላጊ አይደሉም በማለት የደረሱበት ድምዳሜ ትክክል አለመሆኑ ታወቀ። ጣልያኖች በአውሮፓ ጦር በመቀስቀስ አልባንያን ያዙ። በሰሜን አፍሪካም ቢሊብያ ጦር አንቀሳቅሰው ከግብፅ ግዛት እስከ 150 ኪሎ ሜትር ድረስ ገብተው ያዙ። ይህ ሁኔታ እንግሊዝን በማስቆጣት የኢትዮጵያን ነፃነት ዕድል ከፍ አደረገው።[4]

የእንግሊዝ መንግሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ እንደ ገና ተቀባይነት የሚያገኙ አልመሰለውም ነበር። አመለካከታቸውን ሕዝባቸው ይቀበላቸው አይቀበላቸው፣ አርበኞች ይደግፉአቸው አይደግፉአቸው አይታወቅም የሚል አዝማሚያ የተከተለ ነበር። ዕርዳታም የሚሰጡአቸው እየመጠኑ ሆነ። ነገር ግን የንጉሠ ነገሥቱ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ብቻ ሳይሆን ተፈላጊነትም እንደ አላቸው በማስረጃ ተረጋገጠ። በአርበኞች መካከል "ንጉሠ ነገሥታችንን አምጡልን" የሚለው ወገን በዛ። ራስ ውብነህ ተሰማ የነጭ የነጭ ጣልያን ምን አለኝ ብለው ንግግር ሰብረው መውጣታቸው አንዱ ማስረጃ ነው።[5] ንጉሠ ነገሥቱም እንዲህ የማሰኘቱን ነገር በውስጥ አርበኞቻቸው በኩል ሳያካሄዱ አልቀሩም።

ጣልያኖች ደግሞ የተቃውሞ መቀስቀሻ ፕሮፓጋንዳቸውን አጠናከሩ። የጣልያን ፕሮፓጋንዳ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ወደ ሥልጣን ከተመለሱ ከእኛ ጋር የተባበረውን ሁሉ ይፈጃሉ። ጣልያኖች የፈጁት ሕዝብ ንጉሠ ነገሥቱ በመጡ ጊዜ ከሚፈጁት ጋር ሲመዛዘን ኢምንት እንደሚሆን የሚያስገነዝብ ሆነ። ንጉሠ ነገሥቱ የምህረት አዋጅ እንዲያወጡ ቢጠየቁ፤ ይህንን የመሰለ አዋጅ ከኢትዮጵያ ውጭ ባሉበት ጊዜ መስጠት አግባብ እንደማይሆን ገለጹ።[6] ጣልያኖች የእሳቸው ቃል በማስመሰል አንዳንድ ሹመት እንደሰጡ እያደረጉ



በአይሮፕላን አስበተኑ። ዓላማቸው እየተጠናከረ የመጣባቸውን የአርበኛውን አንድነት ለመበተን ነበር። ነገር ግን አድማጭ ሳያገኙ ቀሩ። የንጉሠ ነገሥቱ አቅዋም ይበልጡን ተጠናከረ።

መስከረም 17 ቀን 1933 እንደ ኢትዮጵያ ሥርዓት ከካርቱም የመስቀል የደመራ በዓል ተከበረ። ይህ የደመራ በዓል ከሌሎች ሁሉ የተለየ ነበር። የተለየ የሆነውም በሰው አገር የተደረገ ከመሆኑም በስተቀር ከኢትዮጵያ አርበኞች የንጉሠ ነገሥቱን በሕይወት መኖርና መምጣት በዓይናቸው አይተው እንዲያረጋግጡ ተልከው የተገኙበትና ከስደተኛውም የሚበዛው የተሰበሰበበት በመሆኑ ነበር። አጨኔ ገብረው ባርከው ንጉሠ ነገሥቱ ደመራውን ባቀጣጠሉ ጊዜ በዚያ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ልብ በሀገራቸው እንደገና በአዲስ ጋይ ነደደ።[7]

ነገር በእንዲህ እንደ አለ በካይሮ የእንግሊዝ ጦር አዛዥ የነበሩት ጄነራል ሚሸል ወደ ካርቱም መጡ። ንጉሠ ነገሥቱ የኢትዮጵያን ጉዳይ የሚዘረዝር ሰፊ ማስታወሻ አቀረቡላቸው። የማስታወሻው ይዘት በሦስት መልክ ይጠቃለላል። የመጀመሪያው ክፍል የተደረገላቸው ዕርዳታ በቂ አለመሆኑን ይዘረዝርና "...ይህንን ሁሉ መናገሬ ሲንሴር ካላቦራሲዮን እንደ ጐደለብኝ ለማስረዳት ነው።..." ይላል። ሁለተኛው ክፍል ደግሞ የታንክና የአይሮፕላን መምቻ መሣሪያ እንደሚያስፈልጋቸው ያስረዳል። ሦስተኛው የእሳቸውን ዓላማ የሚገልጽ ሆኖ "...የጦር ሠፈር አቁሜ ስለጦሩ የሚያስፈልገውን ነገር በቶሎ እያጣደፍሁ ማደራጀት እፈልጋለሁ። መንግሥታትንም ለማቆም ቆርጫለሁ..." የሚል ነበር። ነገር ግን ጄነራሉ የሰጡት መልስ ፀረ-ታንክም ሆነ፣ ፀረ-አይሮፕላን መሣሪያ ለኢትዮጵያ እንደማይገኝ የሚያስረዳ ሆነ። የሰጡትም ምክንያት "...ግብፅን፣ ሱዳንን፣ ካርቱምን፣ ኬንያን መጠበቅ አለብኝ..." የሚልና ፍሬ ቢስ ሐተታም የበዛበት ነበር።[8]

የንጉሠ ነገሥቱ ማስታወሻ የእንግሊዝ ባለሥልጣኖችን ቀሰቀሰ። አንድ ከፍተኛ ቡድን ጥቅምት 20 ቀን 1933 ዓ.ም ካርቱም ገባ። ቡድኑ የሚመራው በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በሰር አንቶኒ ኤደን ሆኖ ሰር አርቺቫልድን፣ ፊልድ ማርሻል ስመትስን፣ ሚስተር ሚካኤል ራይትን፤ ከፖለቲካ ሰዎች እንደዚሁም ከከፍተኛ የጦር መኰንኖች ለፍተናንት ጄነራል ደኮንሰንን፣ ሌፍተናንት ጄነራል ካኒንግሐምንና ሌሎችንም የጨመረ ነበር። በሦስት ተከታታይ ቀን ጉባዔ ለጦርነቱ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ከተመረመሩ በኋላ ከበጐ ውሣኔ ላይ ተደረሰ። ውሣኔውም፣

1ኛ. በጄነራል ፕላት የሚመራው ጦር በሰሜን በኩል ኤርትራ እንዲገባ፣

2ኛ. በጄነራል ካኒንግሐም የሚመራው ከደቡብ ኢትዮጵያ እንዲዘምት፣

3ኛ. በንጉሠ ነገሥቱ የሚመራው አነስተኛ ጦር በኢትዮጵያ አርበኞችና ስደተኞች እየታገዘ በጐጃም እንዲገባ ነበር።

የእንግሊዝ ባለሥልጣኖች ለንጉሠ ነገሥቱ ከፍተኛ ዕርዳታ እንደሚደረግላቸው ቃል ገቡ። ከዚህ ላይ መጠቀስ የሚገባው ጉዳይ ሰር አንቶኒ ኤደን ኢትዮጵያ በተወረረች ጊዜ እንግሊዝ ሳትረዳት በመቅረትዋ፤ ከሚስተር ማክሚላን ጋር የረዳት ሚኒስትርነት ሥራቸውን ለቅቀው የነበሩ የኢትዮጵያ ወዳጅ መሆናቸው ነው። ወደ ካርቱም የመጡትም ቀደም ብለው ጥቅምት 18 ቀን 1933 ዓ.ም /ኦክቶበር 29 ቀን 1940/ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን መሪነት ማወቃቸውን ይፋ አድርገው ነበር።[9]

በዚህ ስምምነት መሠረት ሌላው የኢትዮጵያ ወዳጅ ሻለቃ አርዴ ዊንጌት /ጄነራል/ የንጉሠ ነገሥቱ የፖለቲካና የጦር አማካሪ ሆነው በጥቅምት ወር መጨረሻ ካርቱም ገቡ።[10] ውስጠ አዋቂ በመምሰል ራሳቸውን የእንግሊዝ የጦር አዛዥ እንጂ የኢትዮጵያ አማካሪ አድርገው መመልከት የተጠየፉት የኮሎኔል ሳንድፎርድ ጉዳይ በዚህ አከተመ።[11] ወታደር የማሠልጠኑ ሥራ ሰባ በተባለ ቦታ በዚያው በጥቅምት ወር ተጀመረ። ከሞት የተረፉት እንደ እነ ሻለቃ /ጄነራል/ ዓቢይ አበበ፣ ሻለቃ /ጄነራል/ መርዕድ መንገሻ፣ ሻለቃ /ጄነራል/ ነጋ ኃይለሥላሴ ያሉት የኢትዮጵያ የጦር መኰንኖች በማሠልጠኑ ረገድ ጥሩ ሚና ተጫወቱ። የተሰጠውም ሥልጠና በጐጃም በኩል ሠብሮ ለመግባት የተዘጋጀውን ዕቅድ ከግብ ለማድረስ አስቻለ።

ሁኔታዎች መፍታታትና መሻሻል ሲጀምሩ ከእንግሊዞች ወገን ሌላ የነገር አሽክላ ተዘረጋ። እሱም የበሮክለሀርስት ዕቅድ ነበር። የዚህ ኰሎኔል ሃሳብ ከእንግሊዝ ጐን ቆማችሁ ጣልያንን ከወጋችሁ ከኢትዮጵያ ገዥዎች ነፃ እናደርጋችሁአለን በሚል የመደለያ ቃል በደቡብ የኢትዮጵያን ብሔራዊ አንድነት ለመበታተን የተዘጋጀ ዕቅድ ነበር። ንጉሠ ነገሥቱ ይህንን ሃሳብ አልቀበልም፤ ሰውየውንም አላነጋግርም ብለው እምቢ አሉ። ካርቱም ከተሰበሰቡት አባላት አንዳንዶቹንም ቢያሳምን፣ ብሮክለሀርስት ሃሳቡ ሳይሳካለት ቀረ።

የእንግሊዝ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ካርቱም ድረስ መጥተው ከንጉሠ ነገሥቱ ተነጋግረው የጦር ዕቅድ ከተነደፈም በኋላ፤ የእንግሊዞች አቅዋም ኢትዮጵያን በተመለከተ ግልጽ አልነበረም። ለማስረጃ ያህል ጠቅላይ ሚኒስትር ሰር ዊንስተን ቸርቸል ታህሣሥ 13 ቀን 1933 ዓ.ም /ዴሴምበር 23 ቀን 1940/ ለኢጣልያ ሕዝብ በሬዲዮ ያስተላለፉትን ቃል እንመለከታለን። እሳቸውም አጥፊው ሙሶሊኒ መሆኑን ሲዘረዝሩ ኢትዮጵያ የዓለም መንግሥታት ማኅበር አባል እንድትሆን ስትጠይቅ እንግሊዞች አይሆንም ማለታቸውን፤ ሙሶሊኒ ስለደገፋት አባል ለመሆን መቻልዋን ከገለጹ በኋላ "...የኢትዮጵያ ጭቅጭቅ አሁን ኢጣልያና ብሪታንያ በሞት አፋፍ ላይ ከደረሱበት ሁኔታ ጋር ሲተያይ የቱን ያህል ነው?" የሚል ጥያቄ ያዘለ ነበር።



ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጉዳዩን በጥያቄ ብቻ አልተውትም። "በኢትዮጵያ ምክንያት የተነሳው ጠብ በመካከላችን ለተቀጣጠለው እሳት በቂ ምክንያት ያለመሆኑንና የማይደገፍ መሆኑን እገልፃለሁ። ቃሌም የሚቆይ ነው" ከሚል ድምዳሜ ላይ አደረሱት። ነገር ግን ጣልያን ከተሸጐጠችበት ከጀርመን ብብት ውስጥ መውጣት ስለአልቻለች፤ የተጠበቀውና የተጠየቀው እርቅ ሳይገኝ ቀርቶ የኢትዮጵያን ነፃነት ያዘዘው ጦርነት ቀጠለ።

ከእንግሊዝ ባለሥልጣኖች ከእነ ሰር አንቶኒ ኤደን ጋር በተደረገው ስምምነት መሠረት ጦርነቱ በሦስት ገጽ በአንድ ጊዜ በጥር ወር 1933 ዓ.ም ተከፈተ። ዓላማው የጣልያን ጦር በሁሉም ቦታ ቀስፎ በመያዝ መደምሰስ ነበር። ሙሶሊኒ በ1928 ዓ.ም በኢትዮጵያ የሠራው የጦር ሥልት ዙሮ በእሱ በራሱ ላይ መጣበት። በዚህ ምዕራፍ በተለይ በንጉሠ ነገሥቱ በሚመራው የጦር ግንባር የተደረገውን እንመለከታለን።

በሰባ የኢትዮጵያ ጊዜያዊ የጦር ትምህርት ቤት የተሰጠው አስቸኳይ ሥልጠና እንደተጠናቀቀ ሠራዊቱ በየጦር ግንባሩ ተደለደለ። ዋናው የጦር ግንባር ንጉሠ ነገሥቱ የሚሰለፉበት የጐጃም ግንባር ነበር። ሌላው ግንባር የጐንደሩ ሲሆን፣ ሌላ ሦስተኛ አነስተኛ ግንባር በአሶሣ በኩል ሆነ። ድልድሉ በፍጥነት ተጠናቀቀ። ጦሩም በንጉሠ ነገሥቱ ፊት በሰልፍ እያለፈ እንቅስቃሴ አደረገ። በተገኘው ዓይነት ትራንስፖርት ወደ ኢትዮጵያ ከተጠጋ በኋላ በእግር ተጓዘ። የበረሃው ጉዞ ከባድ ነበር። የአንዱን ቡድን ሁኔታ ማየት ትንሽ ፍንጭ ይሰጣል። ሦስት ቀን የሚወስድ ውሃ የሌለበት የእግር ጉዞ ማድረግ ነበረበት። በቂ ኮዳ አልነበረም። ሎሚ በብዛት መያዝ ግድ ሆነ። ሎሚውን ለመያዝ ታማኝ ሰው ሲፈለግ አቶ ጌታሁን ተሰማ ተመረጡ። ተገቢውን ጥንቃቄ አድርገው ለእያንዳንዱ ለሚገባው ሳይቀር የሚያስፈልገውን በማድረግ ቡድኑ በሰላምና በደህና አደገኛውን ቦታ እንዲሻገር አደረጉ።[12] ጦሩ በዚህ ዓይነት ተጉዞ ጐጃም ምድር ለመቆናጠጥ ተዘጋጀ።

ዝግጅቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ስለጦርነቱ አከፋፈት ንጉሠ ነገሥቱ ከጄነራል ፕላት ተገናኝተው ተነጋገሩ። ንግግሩ ያተኮረው የንጉሠ ነገሥቱ የጦር ሠፈር በለያ ስለመሆኑ፣ በስንቅና ትጥቅ አቀራረብና ፊታውራሪ /ራስ/ ብሩ ወደ ቤጌምድር በሚሄዱበት ሁኔታ ላይ ነበር። የልዑል አልጋ ወራሽ አስፋው ወሰንና የልዑል መኰንን ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር አብሮ መሄድ እንግሊዞችን አሳሰበ። ግን መሆን ነበረበት። የኤርስኪንና የብሮክለሐርስት ጉዳይ ከጄነራል ዊቨል እንደገና በቴሌግራም መጠየቁ ተነገረ። ነገር ግን ንጉሠ ነገሥቱ በቀድሞው ውሣኔአቸው ጸኑ። የእነዚህ ሁለት ሰዎች ተልዕኮ "...ለሁለቱ አገሮች የሚሆን አይደለም..." በማለት ደመደሙ።[13]

ንጉሠ ነገሥቱ ከካርቱም በአይሮፕላን እስከሮሰሪስ መጡ። ከዚያም የኢትዮጵያ ጠረፍ በሆነ የሱዳን ምድር ላይ አረፉ። ሠራዊታቸውን መርተው ከኢትዮጵያ ምድር በእግር ገብተው፤ ኦሜድላ በተባለች ቦታ የኢትዮጵያን

ሰንደቅ ዓላማ ጥር 12 ቀን 1933 ዓ.ም ተከሉ። ወዲያው ወርቃዊው የምሕረት አዋጅ በንጉሠ ነገሥቱ በቃላቿው ተነብቦ በጽሑፍ ተበተነ። ይህ አዋጅ ወርቃዊ የተባለው ብወርቅ ቀለም በመጻፉ ብቻ አልነበረም። ለበደሉ ሁሉ ሙሉ ምሕረት ሰጥቶ ኢትዮጵያውያንን እርስበርሳቸው ያስታረቀ በመሆኑ እንጂ። የአዋጁ ፍሬ ነገር "...አገርህንና ወገንህን የበደልህ ሁሉ ባለፈው ጥፋትህ ምሬሐለሁ። ...በመጣው ጠላታችን ላይ ከዳር እስከ ዳር ክንድህን አንሳ ከኢትዮጵያ ጠርገህ አስወጣው..." የሚል ነበር። ይህ አዋጅ በባንዳ ልቡና የነበረውን ሥጋት ፍቆ በኢትዮጵያ ሕዝብ የመተባበር ስሜት እንደገና ፈጠረ። እንግሊዞችንም አረካ።

ከሱዳን ወደ ምዕራብ ኢትዮጵያ ከገባው ጦር አንዱ ክፍል በአሶሣ በኩል ዘምቶ ኩርሙክንና ጊዜንን ያዘ። ኃይሉ መጠነኛ ስለነበር ይህንን ጠባብ አካባቢ ከመያዝ በስተቀር ወደ ውስጥ ገብቶ ለጊዜው በጠላት ላይ ጉዳት አላደረሰም። ቢሆንም የኢትዮጵያ ጦር ከአዲስ አበባ ወለጋ በገባ ጊዜ ብዙ እገዛ አድርጐአል። በጦሩም ውስጥ የቤልጅግ መኰንኖች የኰንጐና የዛየር ተወላጆችም ነበሩበት።[14]

በንጉሠ ነገሥቱ የሚመራው ጦር ጉዞውን ቀጠለ። ከኦሜድላ እስከ ቤላያ የነበረው ጉዞ እጅግ ከባድ ነበር። ቀደም ብሎ በተደገረ ጥናት 25,000 የጭነት ከብት እንደሚያስፈልግ ተገምቶ ነበር። ነገር ግን ሊገኝ የተቻለው 15,000 ብቻ ሆነ። ይህ ደግሞ ጉዞውን አከበደው። በዚህ ላይ በአገር ውስጥ የተገኘው እርካብ ጫማ አላስገባ ስለአለ የፈረንጅ እርካብ እንዲላክ ወደ ካርቱም የተላለፈው ቃል እንደ መሞካሽት ተቆጠረ። አስቸጋሪውን መንገድ ፈጽሞ ቢልያ ገባ። የንጉሠ ነገሥቱ ጊዜያዊ የጦር ሠፈር ከዚያ ሆነ።

ንጉሠ ነገሥቱ ኢትዮጵያ ምድር እንደረገጡ፣ ባንዲራችን በሚባለው በካርቱም በፊት በአቶ /ፕሮፌሰር/ ታምራት አማኑኤል፣ በኋላ ደገሞ በአቶ /ብላታ/ ሢራክ ኅሩይ እየታተመ በአይሮፕላን ይበተን በነበረው ጋዜጣ ወሬው (ዜናው) ተዛመተ። ጐጃም ቀደም ብሎ ገብቶ በአዛዥ /ደጃዝማች/ ከበደ ተሰማና በሻለቃ ዊንጌት /ጄነራል/ የሚመራው ጦር በጣልያኖች ላይ ጥቃቱን አጠናከረው። የጐጃም አርበኞች እርስበርሳቸው ትብበር እየፈጠሩ በየደረሰበት ጠዘጠዙት። ስለአርበኛው እንግሊዞች የነበራቸውን ንቀት ትተው "አርበኛ፣ ማለትም ፓትርዮት" ይሉት ጀመር። በጦር ጓደኝነቱ ተማመኑ።[15] ይህም ሆኖ እንግሊዞች ሥራ ማጓተታቸውና በነገር መጐንተላቸው አልቀረም።

በዚህ ላይ ደግሞ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ኢትዮጵያ ከገቡ በኋላ፤ ካርቱም ላይ የእንግሊዝ የምሥራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛቶች አስተዳደር ባለሥልጣኖች ኢትዮጵያ አስተዳደርዋ እንደምን ይሆናል? የሚል ጥያቄ አንስተው መነጋገራቸውና ከጠላት የተወሰዱ የቅኝ ግዛቶች አስተዳደር ሥር እንደተመደበች በምሥጢር ተሰማ። ነገር ግን ውሣኔውን ለንጉሠ ነገሥቱ ሊናገር የተላከው ብርጋዴር /ጄነራል/ ላሽ ፈርቶ ሳይናገር ወደ ሱዳን



ተመለሰ።[16] በአንድ በኩል ይህ ጉዳይ ከእነ ብሮክለሐረስት አስተሳሰብ ጋር ተደምሮ በኢትዮጵያ ወገን ታላቅ ስጋት ሲቀሰቅስ፤ በሌላ ወገን ደግሞ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሰር አንቶኒ ኤደን ጥር 27 ቀን 1933 ዓ.ም /ፌብሪዋሪ 4 ቀን 1941/ ለንደን ለሐውስ ኦፍ ኮመንስ ያሰሙት ንግግር ለኢትጵያ ተስፋ የሚሰጥ ሆነ። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አነጋገር በቀና መንፈስ ላይ የተመሠረተ ሆኖ የኢትዮጵያን ነፃነት በተመለከተ "የግርማዊ የእንግሊዝ ንጉሥ መንግሥት በነፃነት የኢትዮጵያ መንግሥት እንደገና ተነስቶ እንዲታይ ይፈቅዳል። ለዙፋኑም የአፄ ኃይለሥላሴን ጥያቄ ያውቅላቸዋል።...የእንግሊዝ መንግሥት በኢትዮጵያ የመሬት ፍላጐት የሌለው መሆኑን ራሱ ያረጋግጣል..." የሚል ነበር። ነገር ግን ከማድመጥ በስተቀር በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ቃል ምክር ቤቱ አልተነጋገረበትም። ስለዚህ የእንግሊዝ አቅዋም ገና ግልጽ አልነበረም።

የሆነ ሆኖ ጦርነቱ እየተቃና ሄደ። የጣልያን ጦር አዛዥ ናዚ በአይሮፕላን ከጐንደር ደብረ ማርቆስ በመብረርና የጦር መኰንኖች ሹምሽር በማድረግ ያዘጋጀውን ያህል ሳይመለከት ቀረ። ቡሬ፣ እንጀባራ፣ ፍኖተ ሰላም፣ ማንኩሣ፣ ጂጋ፣ ደንበጫ የነበረው ወደ ደብረ ማርቆስ የዳንግላው ወደ ባሕር ዳር ሄደ። በአጭር ጊዜ ውስጥ አለፋ ጣቁሣ፣ አቸፈር፣ ዘጌ፣ ደብረ ማይ፣ መሸንቲና አዴት የነበረው ሌላውም ሁሉ ተከተለ።[17]

እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ /ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ/ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ኦሜድላ ገቡ። ኢትዮጵያ መሬት ሲገቡ በመስቀላቸው ግራና ቀኝ እየባረኩ የእግር ጉዞ ቀጠሉ። እንኳን በመኪና በበቅሎም አልተቀመጡ። እግራቸው የቻለውን ያህል ሙሉ ቀን እየሄዱ፤ አንዳንድ ግዜም ጦሩን እየቀደሙ እየተጓዙ ከመሬት እንደተኙ ደብረ ማርቆስ ደረሱ። ከዚያም በዚሁ ዓይነት ደብረ ሊባኖስ ገቡ።[18]

የንጉሠ ነገሥቱ ጊዚያዊ የጦር ሠፈር ከቢልያ ወደ ቡሬ ተዛወረ። ቡሬ ላይ ማረፊያ ሜዳ ተሠርቶ የአየር መገናኛ ተከፈተ። ቀደም ብሎ በታሰበው መሠረት ፊታውራሪ /ራስ/ ብሩ ወልደ ገብርኤል ከፊል ጦር ይዘው በባህር ዳር በኩል ወደ በጌምድር ተሻገሩ። ዋናው ጦር ከአርበኛው ጋር ተቀላቅሎ ወደ ደብረ ማርቆስ የሚጓዘውን የጣልያን ጦር ማባረር ቀጠለ። ከዚያ በኋላ ጠንካራ ጦርነት የተደረገው ጨረቃ በተባለው ቦታ ነው። ከጨረቃ ውጊያ በኋላ ሌላ ከባድ ውጊያ ሳያጋጥም ጦሩ ደብረ ማርቆስ አካባቢ ደረሰ። ጣልያኖች ከተማይቱን ለራስ ኃይሉ ትተው ሸዋ ተሻገሩ። እሳቸውም ሳያንገራግሩ ከተማይቱን ለአዛዥ /ደጃዝማች/ ከበደ ስለአስረከቡ ንጉሠ ነገሥቱ በሰላም መጋቢት 28 ቀን 1933 ዓ.ም ወደ ማታ ደብረ ማርቆስ ገቡ።

በኢትዮጵያና በእንግሊዝ ወታደሮች መካከል የነበረው ትብብር በጣም ጥሩ ነበር። መተባበር ብቻ ሳይሆን ከመተማመንም ደርሰው ነበር። ለማስረጃ የአንድ መኰንን ታሪክ መጥቀስ ይገባል። አንድ መቶ አለቃ የተቀመጠበት

ፈረስ በጥይት ሲመታ እግሩ ላይ ስለወደቀበት ከቁርጭምጭሚት እስከ መሐል አጥንቱ ደቀቀ። ከጉልበቱ ሎሚ በስተቀር የዳነ የለም። የሀኪምና እርዳታ ሊያገኝ ስለአልቻለ በኢትዮጵያዊ ወጌሻ ለመረዳት መፍቀዱን በጽሑፍ አረጋገጠ። አቶ ገብረሚካኤል የተባለ ወጌሻ አሽቶ በማለሚያ አስሮ አዳነው። መቶ አለቃው ራሱ ከጻፈውና አለቃው በወቅቱ ካስተላለፈው ሪፖርት በስተቀር መቶ አለቃው መቁሰሉን የሚያመለክት ምልክት እስኪጠፋ ድረስ ፈጽሞ ዳነ።[19]

የንጉሠ ነገሥቱ ደብረ ማርቆስ መግባታቸው፣ የጦር ሠፈር ከዚያ መደረጉ ታላቅ ነገር ሆነ። ራስ ኃይሉም ሳያንገራግሩ ለንጉሡ መግባታቸው ቀላል አልነበረም። የሸዋና የጐጃም አርበኛ አካባቢውን ከጠላት ይዞታ በቶሎ አስለቅቆ በር ለመክፈት ይችል ስለነበር፣ ከደብረ ማርቆስ እስከ አዲስ አበባ የሚደረገው ጉዞ ከዓባይ ድልድይ ሥራ አለመፈጸም  በስተቀር ሌላ አስጊ የጦር ችግር አልነበረበትም። ያውም ቢሆን በአይሮፕላን ሊበርሩ ስለሚችሉ መጋቢት 29 ቀን 1933 አዲስ አበባ መግባት ይችሉ ነበር። ነገር ግን እንደዚህ አልሆነም። ንጉሠ ነገሥቱ ከገዛ መናገሻ ከተማቸው እንዳይገቡ ታገዱ።

ንጉሠ ነገሥቱ ደብረ ማርቆስ ገብተው በአደባባይ ላይ ለተሰበሰበው ሕዝብ የደስታ መግለጫ ንግግር በማድረግ ላይ እንደ አሉ ለኰሎኔል ዊንጌት /ጄነራል/ ከካርቱም ቴሌግራም ደረሰ። ቴሌግራሙ በጄነራል ካኒንግሀም የሚመራው የምሥራቅ ነፃ አውጭ ጦር በዚያው ቀን አዲስ አበባ መግባቱን የሚያበስርና ለጊዜው ማንኛውም እንቅስቃሴ እንዲቆም የሚያዝ ነበር። ዊንጌት ይህ መልእክት እንደደረሰው ንጉሠ ነገሥቱ ወደ አዲስ አበባ የሚሄዱበት አይሮፕላን እንዲላክለት ወዲያው ጥያቄ አቀረበ። ነገር ግን ጥያቄው በካርቱም የእንግሊዝ ባለሥልጣኖች ዘንድ ተቀባይነት አለማግኘቱ ተገለጸለት። ውሣኔውን የሚቃወም መልእክት መልሶ ቢያስተላልፍ፣ እንዲያውም ንጉሠ ነገሥቱን በአሉበት ቦታ እንዲያቆይ የማያወላዳ ትዕዛዝ ከጥብቅ ማስጠንቀቂያ ጋር ተላከለት። ከጄነራል ካኒንግሀምም እንደዚሁ የተሰጠው ምክንያት "አዲስ አበባ ውስጥ 25,000 ነጮች ስለአሉ አገሩ እስኪረጋጋ መቆየት አለባቸው" የሚል ነበር።[20]

ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ደብረ ማርቆስ በመጓዝ ላይ ሳሉ ጄነራል ላቫ ኢትዮጵያ ከጠላት ከተወሰዱ ቅኝ ግዛት አስተዳዳር ውስጥ መመደብዋን ለመንግር መጥቶ፣ መልእክቱን ለመንገር ሳይደፍር ወደ ካርቱም መመለሱን ቀደም አድርገን ገልጸናል። ላቫ የካርቱም ውሣኔ ሳይነገር የተመለሰው፣ ንጉሠ ነገሥቱ ይህንን የመሰለውን ነገር እንደ ስድብ ስለሚቆጥሩት፣ ፈጽሞ እንደማይቀበሉት ከብርጋዲየር ሳንድፎርድ በቁርጥ ስለተነገረው ነበር።

ለዊንጌት የደረሰው መልእክት ከላቫ ተልእኮ ጋር ተደምሮ አዲስ ሥጋት ፈጠረ። በንጉሠ ነገሥቱና በመኳንንቶቻቸው ዘንድ ምክር ተመከረ።



ምክሩ የጦርም የአስተዳደርም ሆነ። በምክሩ መሠረት ንጉሠ ነገሥቱ በደብረ ማርቆስ አደባባይ የአርበኞችን ሰልፍ ሲመለከቱ ዋሉ። ሰልፉም እጅግ ስለደመቀ ባንዳም ተሳተፈበት። በጦር ረገድ የንጉሠ ነገሥቱ ጦር በደጀንና በጉሐ ጽዮን በኩል እንዲያልፍ፣ በሻለቃ /ራስ/መሥፍን ስለሺ የሚመራው ጦር በደራ ተሻግሮ ወደ መርሐቤቴ እንዲዘልቅ፣ በአዛዥ /ደጃዝማች/ ከበደ የሚመራው ጦር ወደ ግንደበረት እንዲሻገር፣ ሞጣ ላይ ተቋርጦ የቀረውን የጠላት ጦር ልጅ /ራስ ቢትወደድ/ አንዳርጋቸው መሣይና ልጅ /ዋግሹም/ ወሰን ኃይሉ በአካባቢው ከሚገኙ አርበኞች ጋር ምሽጉን እንዲሠብሩ ተወሰነ። እንደዚሁም ተደረገ።[21]

አስተዳደርን በተመለከተ በደጃዝማች /ራስ ቢትወደድ/ መኰንን እንዳልካቸው መሪነት አንድ ቡድን ወደ አዲስ አበባ በአይሮፕላን ተልኮ የመግቢያውን ፕሮግራም እንዲያዘጋጅና ፀጥታውን እንዲያስተካክል ተደረገ። በልዑል መኰንን ኃይለሥላሴ የሚመራ ሌላ ቡድን ደግሞ በአይሮፕላን ወደ ሐረር ተላከ። ከዚህም በስተቀር ቀደም ብሎ የካቲት 27 ቀን 1933 ዓ.ም ተጀምረው ሲታሰብባቸው የቆዩ ሁለት ጉዳዮች ላይ ተመከረ። ከእነዚህም አንደኛው የባንዳን አስተዳደር ጉዳይ የሚመለከት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ከእንግሊዝ መንግሥት ስለሚጠየቀው ዕርዳታ ነበር።

ስለ ባንዶች የተደረገው ምክር "...ባንዶቹ ከሹመት፣ ከማዕረግ እንዳይወርዱ ይመኛሉ..." በሚለው ጥያቄ ላይ አተኮረ። "ባንዶችን መማርና መተዳደሪያ ደንብ መስጠት ይሻላል" የሚል ሃሳብ በአንድ ወገን፣ "አስታራቂ ሃሳብ እስከሚቀርብ ወደ አርበኞች ይላክ" የሚል ሃሳብ በሁለተኛ ወገን፣ "መንግስት ተረጋግጦ እስኪቆም ዝም ማለት ይሻላል" የሚል በሦስተኛ ወገን ቀረበ። በአዋጅ የገባ፣ ጣልያኖች ቢክዱት የገባ፣ በተለይ ተጽፎለት የገባና ደም የተቃባ ባንዳ ተለይቶ እንዲታወቅ ተወስኖ እንደነበር ይታወሳል። ንጉሠ ነገሥቱ ደብረ ማርቆስ በቆዩበት ጊዜ ይህ ነጥብ አንድ የምክር ጉዳይ ሆነ። እስከ ጦርነቱ ፍፃሜ ድረስ የሚያገለግል ጊዜያዊ መተዳደሪያ ተበጀ።[22] ስለሆነም ከእንግሊዞች ስለሚጠየቀው ዕርዳታ በዚህ ወቅት ከአንድ ውሣኔ ላይ ለመድረስ ሁኔታው አመች አልነበረም።

ንጉሡ አዲስ አበባ የሚገቡት ሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም እንዲሆን ተወሰነ። ከዚህ ውሣኔ ላይ የተደረሰው የኢትዮጵያ ሞትም ትንሣዔም በአንድ ቀን በተከታዩ ትውልድ እንዲከበር ታስቦ እንደነበር ማጤን ይገባል። ይህንን የመሰለ ዝግጅት ከተደረገ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ ከደብረ ማርቆስ ወደ አዲስ አበባ ሚያዝያ 21 ቀን 1933 ዓ.ም ተንቀሳቀሱ። እንግሊዞች ደብረ ማርቆስ እንዲቆዩ ያደረጉት ለጤና አለመሆኑን ተገንዝበውት ነበርና፣ ጉዞአቸው በጥቃቅን ምክንያት የሚታገድ አልሆነም። ኰሎኔል ዊንጌትም ከእንግሊዝ የጦር አለቆች ይልቅ የንጉሠ ነገሥቱን ሃሳብ ደገፈ። የዓባይን ወንዝ ከበርሜልና ከብረታ ብረት በተሠራ መሸጋገሪያ ተሻግረው ፍቼ ደረሱ።

ንጉሠ ነገሥቱ ጥዋት ከፍቼ ከተማ ተነስተው እንጦጦ ደረሱ። ከዚያ ጀምሮ የሸዋ አርበኛ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ሊብሮ ከመጣው ጦር ጋር መንገዱ ግራና ቀኝ ተሠልፎ ነበር። ሕዝቡም በነቂስ ወጥቶ በመንገዱ ግራና ቀኝ በመሆን በደስታ በእልልታ፣ በሆታ ተቀበላቸው። ከደስታ ብዛት የሚያለቅሰው ይበዛ ነበር።

ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት ተጉዘው እኩለ ቀን ላይ ደረሱ። ደርሰውም መኳንንቶቻቸውና የአርበኞች መሪዎች፣ የእንግሊዝ የጦር ሹማምንቶች በተገኙበት የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ሰቀሉ። ሰንደቅ ዓላማ በሚሰቀሉበት ጊዜ 21 ጊዜ መድፍ ተተኮሰ። ያ የኢትዮጵያ ትንሣዔ የተከበረበት ቀን ሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም ነበር። ከሚያዝያ 27 ቀን 1928 ዓ.ም ሞት ተነሣች።

ከዚህ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ በዚያ ለተሰበሰበው ሕዝብ ንግግር አደረጉ። ጀኔቭ ለዓለም መንግሥታት ማኅበር ሰኔ 23 ቀን 1928 ዓ.ም ከአደረጉት ንግግር ቀጥሎ ታላቁ ንግግር ይህ ነበር። እሳቸውም "የሰማይ መላእክት፣ የምድር ሠራዊት ሊያስቡትና ሊያውቁት ይቻላቸው ባልነበረ በዚህ በዛሬው ቀን ቸር እግዚአብሔር በመካከላችሁ ለመገኘት ስለአበቃኝ በሰው አፍ የሚነገር ምስጋና የሚበቃ አይደለም..." በማለት ንግግራቸውን ጀመሩ። አያይዘውም "...ይህ ቀን ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ የአዲስ ታሪክ ዘመን መክፈቻ...ነው..." አሉ። በሀገሪቱ ላይ የደረሰውን መከራ፣ የአድዋን ጦርነት ጠቀሱ። በጣልያን ላይ የዓለም መንግሥታት ማኅበር እንደፈረደበት አወሱ። አገር የሚለማበትን፣ ሕዝብ የሚበለጽግበትን፣ ንግድ ትምህርትና ጥበብ የሚስፋፋበትን፣ የሕዝባችን ሕይወትና ሀብቱ የሚጠበቅበትን፣ ያገር አስተዳደርም ባዲሱ ሥልጣኔ ተለውጦ ፍፁም የሚሆንበትን ሥርዓት እንዲሚመሠርቱ አስታወቁ። "...በአዲሷ ኢትዮጵያ ከእንግዲህ ወዲያ የማትነጣጠሉ፣ በሕግ ፊት ትክክለኛነትና ነፃነት ያላችሁ ሕዝቦች እንድትሆኑ እንፈልጋለን።..." አሉ። ለእንግሊዝ መንግሥት ታላቅ ምስጋና አቀረቡ። ከዚያም ከቤተመንግሥታቸው ገቡ።

አዲሱ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት በዚህ ቀን ቆመ። ንጉሠ ነገሥቱ ታላቅ አክብሮት አገኙ። የሚቃወሙአቸው ጭምር በፖለቲካ ጥበባቸውና በአመራር ችሎታቸው አደነቁአቸው።


**<u>ማጣቀሻ ፅሑፎች</u>**

1. George Steer, *Sealed and Delivered*, pp.16-31, 90-101, 232-233.
2. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ 2ኛ መጽሐፍ*፣ ገጽ 190-215።
3. ኃይሉ ገብረኢየሱስ፣ *መድረክ*፣ ገጽ 69-75።
4. የድል መታሰቢያ፣ ገጽ 70።





5. ገሪማ ታፈረ፣ *ጐንደሬ በጋሻው*፣ ገጽ 232።
6. Steer, p.121.
7. ገሪማ ታፈረ፣ ገጽ 240-250።
8. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ ገጽ 218-223።
9. Alberto Sabacchi, *Ethiopia under Mussolini*, p 217.
10. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ ገጽ 250-253።
11. ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ* ገጽ 217።
12. ፊታውራሪ ስለሺ ዘረፉ ያጫወቱኝ።
13. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ ገጽ 254-269፣ 271።
14. Steer, pp. 121-136.
15. ሕይወት ኀዳሩ፣ *ያቺ ቀን ተረሣች*፣ ገጽ 71፣ 400።
16. Leonard Mosely, *Haile Selassie*, p.267.
17. Steer, pp.129-148.
18. ከደጃዝማች አስፋው ሺህ አምጥ የተነገረኝ።
19. ከአቶ ገብረሚካኤል ከራሱ የተነገረኝ።
20. Mosley, pp.266-208.
21. ከበደ ተሰማ፣ ገጽ 409-416።
22. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ ገጽ 291-306፡